# አስራት ለጴንጤው

# ታቦት ለኦርቶዶክስ

# መሃመድ ለእስላሙ

# ክርስቶስ ለእኔ

DECEMBER 2009

ከዶክተር ናይክ ካሳዬ

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው

ፈቃድ ማሳተም ወይም ማባዛት በሕግ

የተከለከለ ነው።

All rights reserved

Printed in the U.S.A



| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | 4 |
| እስላም ብሆን ኖሮ ክርስትያን መሆን አልችልም ነበር | 9 |
| የዔድን የሞት ጠረን | 53 |
| የሲኦል አሮማ | 91 |
| ሕገ ሕይወት በሕገ ሃጥያት | 108 |
| የደራሲው ዓምድ | 124 |

# መግቢያ

የትናንትናን ውሎና ገጠመኝ በእውቅና ወይም በመረዳት ካላለፍነው፣ ህልውናችን የዛሬን ውበት ሊያደንቅ አይችልም።

ትናንት ተመልሶ ባይመጣም ለዛሬ ግን ጥላ እንደሆነ እናምናለን። ዛሬ ለትናንትናው አስተዋፆ ባያደርግም፣ የትናንትናውን ተቃውሟዊ ወይም ድጋፋዊ ገጠመኝ ለዛሬው ክንውን ሕልዋት ሊሆን አይችልም።

የትናንት የሆነው ሁሉ በትናንትና ገፅታው እንደሚያልፍ ሁሉ፣ የትናንትም ፀሐይ ዛሬ ልናያት አንችልም። ሆኖም ግን የትናንትናዋ ፀሐይ ለዛሬው አየር ንብረት ትልማዊ መልዕክት የላትም ማለት አይደለም።

የፍጥረት ሁሉ ህልውናና ስብዕና በፍጥረቱ የመለኪያ ሚዛን የሚለካው በትናንትና እና በዛሬ ብቃት ሲሆን፣ መለኮታዊ ሚዛን ግን ዘወትር የሚመዘነው በዛሬ ሕልውና ብቻ ነው።



የዛሬ ህልውናችን ብቻውን የመለኮታዊነት መመዘኛ ከሆነ፣ የትናንትናው ማንነታችን ግን ለዛሬው ህይወታችን ማመሳከሪያው መሆኑን አንዘንጋ።

ትናንት በጨለማ እራቱን የተመገበ ሰው ዛሬ በብርሃን የመመገብን እድል ቢያገኝ፣ የሚመገበውን ምግብ በእውቅናና በደስታ እንደሚመገበው እናምናለን።

የዚህም መጽሐፍ ቀንድያ መልዕክት የሚያተኩረው "ዛሬ ትክክል ነን" ብለን የምናምንበትንና የፀናንበትን ማንነትና <u>ሃይማኖታዊ ክልል</u> በትናንትና ሚዛን መዝነን ለመመልከት ነው።

ክርስትያኑ ትክክል መሆኑን እንዴት ሊያሳምነኝ ይችላል? ክርስትያኑ "ሃጥያተኛ ነህ" ብሎ ስለወቀሰኝና ስለከሰሰኝ ትክክል ነው ማለት ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ "እንዲህ ይላል" ስለተባልኩ ብቻ በቀላሉ ክርስትያን እሆናለሁ ማለት ነውን?

**እስላም ብሆን ኖሮ የዚህ <u>የመጨረሻ</u> ትውልድ የክርስትና መንገድና ሕይወት እኔን ክርስትያን ማድረግ አይችልም ነበር!!!** ምክንያቱም ይህ "ክርስትያኑ" ትውልድ በድንቅ የተጨበጠና በመለኮትነት የተመዘነ እውነት፣ በሕይወት የተለካና የታየ ኑሮ የለውም። ይህ

ክሴ ግን ሁሉንም ክርስትያን እንደማይጨምር ሳልገልጥ ለማለፍ አልሻም።

ስለ አንድ ጉዳይ አንብበን ስለተረዳን ወይም ሰዎች ስለገለጡልን የጉዳዩ እውነትነት ፀናዊ ሆኗል ማለት አይደለም። የማንኛውም ጉዳይ ፅናት መለኪያው ስሩ፣ አመጣጡና የምንጩ ታማኝነት ነው።

ለምሳሌ፣ በየትኛውም የአለም ዳርቻ ብንጓዝና በየትኛውም የሃይማኖት ወጀብ ብንዘፈቅም፣ አንድ እና አንድ ዘወትር ሁለት መሆኑን አንክድም።

የተማረ ያልተማረ፣ የታወረ ያልታወረ፣ የሚሰማ የማይሰማ፣ ተራ ሰው አልያም ሊቃውንት ብንሆን አንድና አንድ ዘወትር ሁለት መሆኑን መለወጥ አንችልም። ይህ የማይለወጥ፣ የማይካድ፣ የተጨበጠና የተረጋገጠ እውነት ነው። ምክንያቱም የውርሳዊ ምንጩ ታማኝነትና አስረጋጭነት የሚያወላዳ ስላልሆነ ብቻ ነው።

ክርስትያኑ ወገን ሁሉ የሚያምንበትና ኑሮው የሚለካበት አንድ የህይወት መጽሐፍ ቢኖረውም፣ የእርስ በእርስ ልዩነታችንና የግጭታችን መንስኤ



የመጽሐፉ ትርጉማዊ ሚዛንና እውቀተ ቢስነታችን ታላቃዊ ድርሻ አላቸው።

ክርስትያኑ "አንድ መጽሐፍ ብቻ አለው" የሚለው አባባል፣ የይኖዋ ምስክሮች የሚባሉትን የክርስትና ክፍሎች አይጨምርም። ምክንያቱም የይኖዋ ምስክሮች ያላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ከሌላው የክርስትና ክፍል የተለየ ነውና።

እኛ ክርስትያኖች "ለሕይወታችን መዋቅር ነው" የምንልበትን አንድ መለኮታዊ መጽሐፍ ይዘን እርስ በእርሳችን እየተበላላን እንዴት በክርስቶስ የማያምነውን ወገን የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ማድረግ እንችላለን??

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይዘን ስላቅራራን፣ ለክርስትና የህይወት መዋቅራችን ዋስትና ነው ማለት አይቻልም። የክርስትና ዋስትናው የሚመዘነው በህልውና እና በኪዳን ውጥናዊ እውቅና ሲሆን፣ ህልውናችን ፅናታዊነቱን የሚያጎላው ማንነታችንን በኪዳን መስታወት ስንገነዘብ ብቻ ነው።

ከየትኛውም የሃይማኖት ክፍል የሆኑትን አንባቢዎችን የምማፀነው ጉዳይ ቢኖር፣ ይህ መጽሐፍ

ያለ ግላዊ ፍርድና ጥላቻ፣ በቅንነትና በእውነተኛነት እንዲነበብ ነው።

ግትርነት የትክክለኛነት መግለጫ እንዳልሆነ ሁሉ፣ የሃይማኖት ድርጅታዊ ምልከታም የትክክለኛነት መለኪያ አይደለም። ከማንነታችን ግላዊ ጥላቻ የተነሳ የራሳችንን ትክክለኛነትን ከመፍጠር የሚጠብቀን ነገር ቢኖር፣ እውቅና ባለው ከሰው ባልመነጨ መለኮታዊ እውነት ላይ ማተኮር ብቻ ነው።

ትክክለኛነት በግላዊ ቅድመ ፍርድ አእምሮ ሊመዘን አይችልም። ትክክለኛነት የሚለካው በተወሰነ የእውነት መዋቅር ብቻ ነው።

ስለዚህ አንባቢዎቼን በእውነትና በትህትና የምማፀነው ነገር ቢኖር፣ ይህን መጽሐፍ በግላዊ ጥላቻ ሚዛን እንዳይነበብ ነው።

**ማስታወሻ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኤሎሂም፣ ያህዌ እና አዶናይ የሚሉት ስሞች ትክክለኛ የአምላክ መጠሪያ ስም እንደሆኑ ይታወቅ፣ ስሙንም በተገቢው ስፍራ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።**

# ምዕራፍ አንድ

## እስላም ብሆን ኖሮ ክርስቲያን መሆን አልችልም ነበር

እንደሰውነታችን አልያም እንደማንነታችን አቅምና መጠን የምንሻውና ሊያረካን የሚችልን ማንኛውም ነገር ለማግኘት መመኘት የማንኛውም ፍጥረት ትልምና ፍላጎት ነው።

በሰው ቋንቋ መናገር የማይችሉ እንስሳት እንኳ ሳይቀሩ፣ በቀበልኛቸው ግንዛቤ ባንረዳቸውም፣ እርካታቸው እንዲሞላላቸው የሚመኙት ጉዳይ አለ። ይህ የጥማት ቁርኝት ሊከሰት የቻለው፣ እንስሳትና ሰው ፍጥረታቸውና ማንነታቸው ቢለያይም የሚጋሩት **"ነፍስ"** የሚባል የአካል ክፍል ስላላቸው ነው።

የሰውነት አካል ውሃን የመጠማቱን ያክል ነፍሳችንም በገዛ ክፍሉ ግዛት የሚጠማው ጥማት አለ። እንደምናውቀው የሰው ልጅ ሶስት የተለያዩ ታላላቅ የአካል ክፍሎች እንዳሉት ሁሉ፣ ነፍስም በክፍሉ ሶስት

ተናጥላዊ ክፍሎች አሉት፣ እነርሱም ሃሳብ፣ ስሜትና አእምሮ ናቸው።

እነዚህ የነፍስ ክፍሎች እለት በእለት ጥማታቸው እንዲከስምላቸው ፍላጎታቸው መሟላት ይኖርበታል። እርካታቸው ግን ለዘወትር ፍፁምነት ሳያገኝም ሊኖር ይችላል። ምክንያቱም ነፍስ በሰው ዐይን የሚታይ ስብዕና ስለሌለው እርካታው በሚታይ ነገር ሊሟላ ስለማይችል ነው። ከዚህም እርካተ ቢስነት የተነሳ የሰው ልጅ ዘወትር ራሱን በሃይማኖት ያጥራል።

**ሃይማኖት ነፍስን ያረካልን? የትኛውስ ሃይማኖት ትክክለኛና ቀናዊ የጥማት ምላሽነት አለው?** ማረጋገጫችንስ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ግብዞችና እምቢተኞች ካልሆንን በስተቀር፣ ሁላችንም የምናምንበትና አስረግጠን የምንቀበለው እውነት ቢኖር፣ ያህዌን ያየ ወይም የተመለከተ ሰው እንደሌለ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያህዌን የተመለከተ ሰው አለ በማለት የተፃፈን አንዳች ዐርፍተ ነገር አላነበብኩም። ስለዚህ ያህዌን ያየና የተመለከተ ሰው እንደሌለ ሁላችንም ተስማምተን መቀበል የሚኖርብን የተጨበጠ እውነት ነው።

የሰው ልጅ በየትኛውም የኑሮ ክልል ውስጥ ቢኖርና ቢያልፍ፣ እርካታው ፍፁም የሚሆንለት ከሚታይ ነገር ሊሆን አይችልም።

ይህንን ከበድ ያለና አከራካሪ ሊሆን የሚችልን ነጥብ በማስረገጥ መናገሬ፣ ማንነቴና የብዙ ወዳጆቼ ልምድና የምንመሰክርለት እውነታ ስለሆነ ነው።

ገንዘብ፣ ውብ ንብረት፣ ሚስት፣ ባል፣ ልጆች፣ ስልጣን፣ የገነነ ስም፣ ታዋቂ ስም፣ የላቀ ትምህርት..... ወ.ዘ.ተ. የሚታዩና የሚለኩ ስለሆኑ፣ የማይታየውንና በዕይታ የማይለካውን የሰውን ውስጣዊ ክፍል ለማርካት ስለማይችሉ ለዘወትር ጥማት በጥማት ላይ ይረባረብብናል።

ነፍስ በሚታይ ነገሮች መርካት ፍፁም አትችልም! ማንኛውም የሚታይ ነገር አቅሙና መጠኑ የሚለካ እልያም የሚመዘን ነው። ከዚህም የተነሳ በየትኛውም የአለም ክፍል ውስጥ ብንመለከት ማንኛውም ነገር የመለኪያ ፅናት አለው።

ቁመት፣ ክብደት፣ ሃብት፣ ውበት...ወ.ዘ.ተ. የመለኪያ መሳሪያ አላቸው፣ ውስን ስለሆኑ መወሰኛቸው ውጥንነት ያለው ነው።

በምድር ላይ ያልተወሰነ ወይም ያልተለካ አልያም ሊለካ የማይችል አንዳች ነገር የለም። የሚታይ ነገር ሁሉ የሚታይ መለኪያ አለው።

የሰው ፍጥረት እርካተ ቢስ ከመሆኑ የተነሳ ሌላው ቀርቶ የወለደውን ልጅ ጨፍጭፎ ይገድላል። ምናልባት ሃይማኖተኞች ይህንን አይነት ክስተት በሰይጣን ገፋፊነት የሚከሰት ነው ሊሉን ይችላሉ፣ ባልስማማበትም <u>የማልቃወመው</u> ጭብጥ ነው። ሆኖም ግን ሰው ጭካኔን የሚፈፅመው እርካታ ቢስ ከመሆኑ የተነሳና የጭካኔውን ስራ በተግባር ሲፈፅመው የሚረካ ስለሚመስለው ነው።

እንደ ባለአእምሮ ሰው ስናስበው ልጁን ጨፍጭፎ የሚገድል አለ ብለን ለመቀበል ይከብደናል፣ ሆኖም ግን ክስተቱ የሆነ፣ ያለና ወደፊትም ሊሆን የሚችል ትዕይንት ነው። ይህ ጭካኔያዊ ክስተት የሚተገበረው የወለዱትን ልጅ በመጥላት ሳይሆን እርካታ ቢስ



ከመሆን የተነሳ ነው። ምክንያቱም ሰው በእለት ተዕለት ኑሮው እርካታ ቢስ ነውና።

እርካተ ቢስነት የማይታይና የሚያስጨንቅ የህይወት ገጠመኝ ነው። ምክንያቱም ነፍስ የሰው ልጅ የጥማት ጉድጓድ ስለሆነች በሚታይ ነገር ልትሞላ ፍፁም ስለማትችል ነው።

በየትኛውም የሃይማኖት ክልል የሚገኝ የሰው ፍጥረት ሁሉ እርካታ ቢስ እንደሆነ በማስረገጥና በመተማመን ወጥኖ መደምደም ይቻላል። ምክንያቱም ሃይማኖት ራሱ የሚታይና የሚለካ ስለሆነ ነፍስን <u>ለዘለቄታ</u> ለማርካት አይችልም።

ማንኛውም ሰው እርካታን በሃይማኖት የሚያገኝ ስለሚመስለውና እርካታም ለማግኘት ፍፁም ስለሚሻ በገጠመው የሃይማኖት ወበቅ በመታጀል ይዋከባል።

<u>**አብዛኛው ሃይማኖተኛ ሰው ስለሚከተለውም ሃይማኖት እውቀትና እውቅና የለውም፣**</u> ሃይማኖቱ በራሱ እርካታ የሚሰጠው ስለሚመስለው ለማወቅም ግድ አይለውም።

እንግዲህ እውነት እንነጋገር ከተባለ፣ በምድር ዙሪያ ሁሉ የምንገኝ ራሳችንን "ክርስትያን" **ብለን**

**የደመደምን ሁሉ** በማስረገጥ "እርካታ በፍፁምነት አለን" እያልን ብንሟገትና፣ "እርካታ ቢስ ነው" ብለን የምንገምተውን፣ ከእኛ ጎራ ያልሆነውን ሰው እንዴት ወደ ጎራችን "እርካታ" ማምጣት እንችላለን?

በምሳሌ ለማስቀመጥና ለርዕሳችንም ይመች ዘንድ፣ **እስላሙን እንዴት ክርስትያን ማድረግ ይቻላል?**

ክርስትያኑ የእርካታዬ ምንጭና ባለቤት "እየሱስ ነው" ካለ፣ "እየሱስ የሌለው ሕዝብ" ተብሎ የሚነገርለትን ወገን እንዴት ወደ እርካታ ግዛት ማምጣት ይቻላል?

በመጀመሪያ ደረጃ ልንዘነጋው የማይገባ ቁምነገር ቢኖር፣ እስልምናና ክርስትና ለህይወታቸው መመሪያ ናቸው የተባለላቸው ሁለት ፍፁም የተለያዩ መጽሐፍቶች አሏቸው። ስለዚህ፣ የተቀመረ ማረጋገጫ ስለሌለንም "የእኔ ትክክል ነው፣ የእነርሱ ትክክል አይደለም" ማለት አይቻልም። ምክንያቱም እስላሙ መጽሐፍ ቅዱስን "ብዙ ጊዜ በመከላለስ የተፃፈና የተለያዩ ሰዎች የፃፉት የራሳቸው ግለሰባዊ አመለካከት እንጂ፣ ከአንድ አምላክ የተቀበሉት አይደለም" ብለው ስለሚያምኑ ነው።



"ክርስትያን" በማለት ራሱን የሚጠራው ክፍል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ቢደረድር አልያም ከጅምርት እስከ ፍፃሜ የመጽሐፍ ቅዱስን "እውቀት" ቢያነበንበው፣ ለእስላሙ ወገን የእርካታ ስጦታ አልያም ወደ እርካታ ድግስ የሚወስድ የግብዣ ጥሪ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም በእስልምናው ዕይታ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል አይደለም ተብሎ የሚወሰድ መጽሐፍ ነውና።

ይህ ሲባል በማይታመን ማሳመን አይቻልም ለማለት እንዳልሆነ ከግምት መግባት አለበት።

የምንወደው፣ የምንቀርበው፣ አብሮ አደጋችን፣ ወዳጆችንና ወገናችን የሆነውን እስላሙን እንዴት እርካታ ይሰጣል ወደሚባለው ክርስቶስ ማምጣት ይቻላል?

ክርስትያኑ ትክክል ነው ያለው ለእስላሙ ትክክል ካልሆነ፣ ክርስትያኑ እርካታ ሰጥቶናል የሚለው ለእስላሙ ተራ ነገር ሆኖ ከተቆጠረ፣ ለክርስትያኑ ህይወት ነው የሚባለው ለእስላሙ የሞት መንገድ መስሎ ከታየ፣ በየትኛው ስልት አልያም ጭብጥ ጎዳና ነው መከናወን የሚገኘው?

እንግዲህ የክርስትያን የሆነው ማንኛውም የሃይማኖት መሳሪያ ለእስልምናው መጠቀሚያ ካልሆነ፣ እውነቱ እንዴት ይታወቃል?

**ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር ክርስትያኑም ሆነ እስላሙ የተለያየ ሃይማኖታዊ ምልከታ ይኑራቸው እንጂ ሁለቱም በጅምርት አምላክ ተምሳላዊ ፍጥረት እኩሌታ እንዳላቸው ነው።**

ይህ እኩል የሆነ <u>ተፈጥሯዊ</u> ማንነት ትክክልና ትክክል ያልሆነ፣ እርካተ ሙሉና እርካተ ቢስነት በማለት ለመለያየት ያስቻላቸው ፅናቱ ምንድነው? <u>ለትክክለኛነታቸውስ ማረጋገጫው ምንድነው?</u>

ሽቶ የተቀባ ሰው የሚሸተው የተቀባውን ሽቶ ብቻ ነው። ሽንኩርት የሚቀቅል ሰው የሚሸተው ሽንኩርት ሽንኩርቱን ነው። በአንደበተ ርትዑነትታችን ብቻ የሌለንን እንዲኖር ለማድረግ እስላሙም ሆነ ክርስትያኑ ብቃት የለውም። የህይወት ወላፊን የምንሸፍነውና የምንደብቀው አይደለም። የሌለንን መስጠት አንችልም! **የማንቀበለውን ልናስተናግድ አንችልም!**



በአለም ዙሪያ የሚኖር የሰው ፍጥረት ሁሉ አንደበተ ርትዑ ነው። ይህ ርትዑነት ለጥቂት ጊዜ ዘለቄታዊ ያልሆነ ውጤት ሊያስገኝልን ይችላል። ሆኖም ግን የጥላቻ ውጥረት ሊፈጥር እንደሚችልና እንደፈጠረ ለብዙዎቻችን ያልተከደነ እውነታ ነው።

የሚያስገርመውና የሚያሳፍረው የአንደበት ርትዑነት ያየለውና በክፋት የገነነው "ክርስቶስ እርካታችን ነው" በሚሉት፣ <u>**ኪዳንን ለይተው ባላወቁ**</u> የሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ ነው።

**አንደበተ ርትዑነት የመናገር ችሎታ ብቻ ሳይሆን ልብ፣ ምላስና ኑሮ ሳይስማሙ ሲቀሩም ነው!**

ስለ አንድ ነገር አስረግጠን በመናገራችን ብቻ የተናገርንለትን ጭብጥ ነገር እንኖርበታለን ወይም ኖረንበታል ማለት አይደለም።

የምንናገርበትን የማንኖርበት ከሆነ የምንናገርበት ጉዳይ አእምሮን በማሰልጠን የተገኘ <u>እውቀት</u> እንጂ፣ ለሌሎች ገልጠን የምናሳየው <u>የህይወት ግልባጭ</u> አይደለም። ይህ ማለት ግን እውቀት ብቻ ሆኖብን የምንናገረው ነገር ውሸትነት አለው ማለት እንዳልሆነ ይታወቅ።

የምንናገረውን ካልኖርንበት፣ የምንናገረው ሁሉ **ወሬ** ይባላል። **ወሬ** ቢሰሙትም ቢተውትም ያው **ወሬ** ነው፡ **ከወሬነቱ** ፈቀቅ አይልም። ስለዚህ የ**ወሬ** ዋጋው ከንቱነት ብቻ ከሆነ፣ ይህ ከንቱ የሆነው ነገር እንዴት ለሰሚው ህይወት ሊሰጥ ይችላል?

አንድ ሰው የሰማውን ወይም የተናገረውን በተግባር ለመግለጥ የሚያዳግተው ምክንያት የሰማው ወይም የተናገረው ነገር **ወሬ** ስለሆነ ወይም ለሰማው ወይም ለሚናገረው ነገር **ዋጋ** ስላልሰጠ ነው።

ዋጋ አለመስጠት የሚመነጨው የምንናገርለትን ነገር በራሳችን ፍላጎትና ብቃት ወይም ጥረት ስላላገኘነው ብቻ ነው። ጥረን ላገኘነው ነገር ሁሉ ዋጋችን እጅግ የከበረ ነውና።

**ክርስትያኑ እስላሙን ወገን ትክክል አይደለም ስላለው ክርስትያኑ ትክክል ነው ማለት አይደለም።** በእስላሙ ክልል ደግሞ ክርስትናው ትክክል አይደለም ስለተባለ እስልምናው ትክክል ነው ማለትም አይደለም። ምክንያቱም በዚህ ዘመን ሁለቱም ክፍል የሚያቀርቡት ድምዳሜያዊ ቁርጠኝነት፣ በሃይማኖታዊ ግትርነት የተወለደ ጥላቻዊ ግንዛቤ እንጂ፡ የማንነት ለውጥ፣



መለኮታዊ ሃይል የፈጠረው ድንቃ ድንቅ የተሞላ የህይወት ምላሽና ሰማያዊ መገለጥ አይደለም።

አንድን ነገር አስረግጠን አውርተንለትና መስክረንለት ነገር ግን በሚታይ ማንነት ለመተግበር የሚሳነን ከሆነ፣ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ከእኩሌታ በሚበልጥ የሚያሳየን ግትር ሃይማኖተኞች መሆናችንን ነው።

አንድ ግትር የሆነን ሰው ያለእቅድ ቢገጥመንና ማንነቱን ባናውቀውም፣ ከግትርነቱ የተነሳ ሃይማኖተኛ እንደሆነ መደምደም የሚቻልበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

ሃይማኖተኞች ዘወትር ግትሮች ናቸው፣ ምክንያቱም ሃይማኖተኛ ሰው ሁልጊዜ እርሱ ብቻ ትክክል የሆነ ስለሚመስለው የሃይማኖቱ መርሃዊ ዕይታ ባይገባውም በግትርነቱ ይፀናል። ግትርነት በሰማይ ሆነ በምድር ድርሻ ቢስ ነው።

**ብንቀበለው ባንቀበለውም፣ ብንረዳው ባንረዳውም ሃይማኖተኛ ሰው ከአምላኩ በላይ ሃይማኖቱን የሚወድ ነው። ለምሳሌ፣ ኦርቶዶክሱ ከአምላኩ በላይ ኦርቶዶክስነቱን ሲያፈቅር፣ ጴንጤውም ከአምላኩ በላይ**

**<u>ለጴንጤነቱ ሲንሰፈሰፍ ተመልክተናል። ይህ የዚህ የመጨረሻ ትውልድ እርግማን ነው!</u>**

ግትርነታችን እውነትን ስለሸፈነብን ብዙ ጥላቻን በመካከላችን ወልዷል። ክርስቲያኑ ራሱ "በክርስቶስ ወንድሜ ነው" ብሎ የሚናገርለትን <u>በብልጫ</u> ብቃት ሲነክስ፣ መቅኖ ሲያሳጣውና እያሳጣውም እንዳለ ለሁላችን ግልፅ የሆነና ከእይታ የማንከልለው ነው።

ይህ የክርስትያኑ የእርስ በእርስ ጥላቻ የተወለደው ከእምነታችን ሃያልነት ወይም ከመንፈሳዊ ፍቅር ምሪት ወይም መገለጥ ሳይሆን ከግትርነታችን ውልደት የመጣ ነው።

በእርግጠኝነትና በድፍረት ኤሎሂም ግትር እንዳልሆነ መናገር እችላለሁ፣ ምክንያቱም **ግትር ምህረት የለውምና**። ስለዚህ ግትርነታችን ትክክለኛነታችንን የማይገልፅ ከሆነ፣ <u>ለትክክለኛነታችን ማረጋገጫውና ማፅኛው ጭብጡ ምንድነው?</u>

በመጀመሪያ በተግባራዊነት ገፅታ ግትርነታችንን በገላጣነት መንገድ ለማየት ከመቻላችን በፊት፣ ትክክለኛ የሆነውን ጎዳና ለመለየትና ለማወቅ



እንዲያስችለን በአቅማችን እውቅና ልክ ለመመልከት እንሞክራለን።

**ይህ የትክክለኛነት ፅናታዊ መርህ መለኪያው በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን በመለኮታዊ ምሪት በሰው የእውቀት ብቃት ልክ እንደሆነ ማወቅ አለብን!!!!**

ኤሎሂም የሃይማኖት አጀባ ግድ አይለውም። ኤሎሂም ግድ የሚለው የሰው ማንነትና መለኮታዊ ስብዕና ብቻ ነው።

ኤሎሂም ህዝቡን "ኦርቶዶክስ፣ ጴንጤ፣ ካቶሊክ፣ እስላም... ወ.ዘ.ተ." በማለት አለያቸውም። ይህ ሃይማኖታዊ ተቀፅላ የኤሎሂም ህዝብ ለመባል መለያው ካልሆነ፣ ለኤሎሂም ህዝብነት ማረጋገጫው ምንድነው? ይህንን ጉዳይ **በጥንቃቄና እድኋዊ ባልሆነ** እይታ እንመለከታለን።

ሰው ከተፈጠረ በኋላ ዐመፃ፣ ክፋትና ጭካኔ እየበዛ ከመሄዱ የተነሳ፣ ከ2,748 አመታት በኋላ ኤሎሂም ፍጥረትን ሁሉ አጥፍቶ፣ ለሰው ፍጥረት ትሩፋት ይሆን ዘንድ ኖህ የሚባል ሰው በኤሎሂም ፊት ሞገስ አግኝቶ ተመረጠ **(ዘፍ 6፡8)።**

ኤሎሂም ከኖህ በስተቀር ሰው ሁሉ ከምድር ላይ ይጠፋ ዘንድ የጥፋት ውሃ በምድር ላይ ለመልቀቅ ወሰነ። ነገር ግን ኖህ ከዚህ የጥፋት ውሃ ሃይል ይድንበት ዘንድ መርከብ እንዲሰራ ከኤሎሂም ትዕዛዝ ተሰጠው **(ዘፍ 6፡14)።**

በዚህ መርከብ ውስጥም ከኖህ ጋር እንዲገቡ የተፈቀደላቸው የሰው ፍጥረቶች የኖህ ቤተሰቦች ብቻ ነበሩ **(ዘፍ 6፡18)።** ታሪኩን እንደምናውቀው የጥፋቱም ውሃ ወርዶ በመርከቧ ውስጥ ከነበሩት በስተቀር የሰው ፍጥረታትን ሁሉ ደመሰሰ።

ኖህና ቤተሰቡ ከመርከቡ ሲወጡ በምድር ላይ ከጥፋቱ ውሃ የተረፈ አንድም የሰው ፍጥረት አልነበረም። ስለዚህ ከጥፋት ውሃ በኋላ ህዝቦች በምድር ላይ የተገኙት ከኖህና ከልጆቹ እንደሆነ ለመረዳት መፈላሰፍ አያስፈልገውም።

**ይህም ነጥብ "የሰው ምንጩ ዝንጀሮ ነው" ብለው በሚያምኑትና በሚገነቡት ፈላስፋዎች ዘንድ እንኳ ተቀባይነት አግኝቷል፣** ይህም ማለት ከጥፋት ውሃ በኋላ የሰው ልጅ ሁሉ ምንጭ ኖህና ልጆቹ መሆናቸውን ነው።



አሁን ላለንበት ለመጨረሻው ትውልድ የተከደነውንና ሚስጥር የሆነውን ድንቅ እውነት በተቻለን መጠን በጥንቃቄ እንመለከታለን።

ኖህ **ሴም፣ ካምና ያፌት** የሚባሉ ልጆች ነበሩት። እነዚህ ሶስቱ ልጆች ለአለም ህዝብ ሁሉ ምንጮች ናቸው **(ዘፍ 9፡19)።**

ኖህ ገበሬ ነበረና ወይን ተከለ፣ ከወይኑም ጠጅ ጠጥቶ በመስከር በድንኳኑ ውስጥ እርቃኑን ተኛ። የኖህ ልጅ **ካም** የአባቱን እርቃን ስጋ አየ፣ ወደ ውጭም ወጥቶ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው። **ሴምና ያፌት** ግን የአባታቸውን እርቃን ስጋ ሳያዩ ሸፈኑት። ኖህ ከስካር ሲነቃ የሚያስደንቅና የሚያስገርም **ትንቢት** እንዲህ በማለት ተናገረ፣ **"የሴም አምላክ ኤሎሂም ይባረክ" (ዘፍ 9፡26)።**

እዚህ ጋር ማወቅ ያለብንና በጥሞና ማየት የሚኖርብን፣ ኤሎሂም ለኖህ ሲገለጥለት "የሴም አምላክ ነኝ" ብሎ አልነበረም (ዘፍ፡6)።

ህዝቦች ኤሎሂምን ከአዳም እስከ ኖህ ድረስ የሚያውቁትና የሚያመልኩት "ኤሎሂም፣ ያህዌና አዶናይ" በማለት እንጂ በነጠላ "የእከሌ አምላክ" ተብሎ

አልነበረም። ስለዚህ ኖህ "የሴም አምላክ" ያለበትን ትንቢታዊ ቃል በጥሞና እንመለከታለን።

እንግዲህ የኖህ ልጆች ለሰው ልጆች መብዛት መንስኤዎች እንደሆኑ ከተመለከትን፣ ዝርያቸውን መመልከት ለመልዕክታችንም ዕይታ የተገባ ስለሆነ፣ በትንታኔና በጥንቃቄ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን።

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የኖህ ልጆች ሴም፡ ካምና ያፌት ነበሩ።

ያፌት ሰባት ልጆች ሲኖሩት ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ነው፣ ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፡፣ ያዋን፣ ቶቤል፣ ሞሳህ እና ቴራስ ይባሉ ነበር።

የያፌት **ክልላዊና ግዛታዊ** ምልክታ እንዲኖረን የልጆቹንም ልጆች ዝርዝርና ወቅታዊ የሀልውና ክልላቸውን እንመልከት።

የያፌት ልጅ ጋሜር ሶስት ልጆች ነበሩት። እነርሱም አስከናዝ፣ ራፋትና ቴርጋማ ይባላሉ። አስከናዝ ያሁኑ **ጀርመን** (Germany) ሲሆን፣ ከዚህም የተነሳ በትውልድ አይሁዳዊ ያልሆኑት ጀርመናዊ



አይሁዶች እስከዛሬ ድረስ አስከናዝያዊ ተብለው የሚጠሩት።

ሌላው የጋሜር ልጅ ራፋት ሲሆን፣ የቅድመ ታሪክ አዋቂዎች ወይም ተመራማሪዎች በማስረገጥ ራፋት ለካርፓቲያን (Carpathians) ምንጭ መሆንን ይናገራሉ።

ካርፓቲያን በማዕከላዊ አውሮፓ ተራራማዊ ክልልን አካቶ **ስሎቫኪያን** (Slovakia) ፣ ሰሜናዊ **ፖላንድን** (Poland) ፣ **ዩክሬንን** (Ukraine) እስከ **ሮማኒያ** (Romania) ሰሜናዊ ምስራቅ ክልልን የሚጨምር ነው።

ሶስተኛው የጋሜር ልጅ ቴርጋማ ሲሆን፡ ቴርጋማ **የአርሜኒያን** (Armenian) ዘር ምንጭ ሲሆን፣ የተለያዩ ጥናቶች **ቱርክን** (Turkey) እንደሚጨምር ይናገራሉ።

ያፌት ማጎግ የሚባልም ልጅ እንዳለው ተመልክተናል፣ ማጎግ ማለት በዘመናችን **ጆርጂያ** (Georgia) ተብሎ የሚጠሩት ህዝቦች ሲሆኑ፣ ይህ ህዝብ በቀድሞ **ራሺያ** (Russia) እና **ሞስኮ** (Moscow) የሚባሉት ህዝቦች ናቸው።

ሌላው የያፌት ልጅ ማዴ ሲሆን፣ ቅድመ ታሪክ ጠቢባኖች **የህንዶች** (India) ምንጭ ነው በማለት ይናገሩለታል።

ሌሎቹ የያፌት ልጆች ያዋል **የግሪኮች** (Greek) ግኝት፣ ቶቤል ደግሞ **የስፔን** (Spain) ምንጭ፣ ሞሳህ ደግሞ **የኢራንና** (Iran) **የአዘርባጃን** (Azerbaijan) ምንጭ ሲሆን፣ በመጨረሻ ደግሞ ቴራስ **ሜዲትራንያን** (Mediterranean) አካሎ **የጣሊያኖች፣ የፈረንሳዮች፣ የፐኒንሱላ** (Peninsula) **እና የኢስያ** ምንጭ ነው ተብሎ ይታመናል።

ሌላው የኖህ ልጅ ካም ሲሆን፣ የካም ልጆች **ኩሽ** ማለትም የአሁኗ __ኢትዮጵያ፣__ ምፅራይም ማለትም የአሁኗ **ግብፅ፣** ፉጥ ማለትም የአሁኗ **ሊቢያ** እና **ከነዐን** ናቸው።

የካም ልጅ ኩሽ (**ኢትዮጵያ**) አምስት ልጆች ነበሩት። እነርሱም ሳባ፣ እውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማ እና ሰበቅታ ናቸው። ሳባ ማለት የአሁኑ **ሱዳን** ሲሆን፣ ከዚህም የተነሳ ነው ሱዳናውያኖች ሳባውያን ተብለው የሚጠሩት።



ሌላው የካም ልጅ የሆነው ምፅራይም (**ግብፅ**) የብዙዎችና **የፍልስጤማውያን** አባት ነበር።

የካም ልጅ የሆነው ከነዐን ደግሞ አስራ አንድ ልጆች ነበሩት። ይህም ህዝብ በከነዐን ምድር ይኖሩ የነበሩት ናቸው።

ከኖህ ጀምሮ ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች የሚነጋገሩበትም ቋንቋ አንድ አይነት ብቻ ነበር፣ ሆኖም ግን ከሕዝቦቹ ማመፅ የተነሳ ኤሎሂም ቋንቋቸውን በመደባለቅ በምድር ሁሉ ላይ __በተናቸው__ (ዘፍ 11፥ 8)።

ሌላው የኖህ ልጅ ሴም ሲሆን ልጆቹም ኤቦር ማለትም **ዕብራዊ፣** አርፋክስድ፣ አይስ፣ ሉድና አራም ናቸው። የሴምን የመጀመሪያ ልጅ ስናነብ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ነጥብን እንመለከታለን። ምክንያቱም __የዕብራውያን__ ሁሉ ምንጭ የሆነው __ኤቦር__ ከሴም እንደፈለቀ እንመለከታለን።

የሴም ልጅ ልጆች የሆኑትን በቅደም ተከተላዊ ውርደት ከተመለከትን በኋላ ናኮር ታራን እንደወለደ እናገኛለን። ታራ **አብረሃምን** ወለደ፣ አብረሃም ከግብጻዊቷ የቤት ሰራተኛው አጋር **እስማኤልን** ሲወልድ፣ ከባለቤቱ ከሳራ ደግሞ **ይስሃቅን** ወለደ።

እስማኤል አስራ ሁለት ልጆችን ሲወልድ፣ ይስሃቅም ከርብቃ ሁለት መንትያ ልጆችን እነርሱም ኤሳውና **ያዕቆብን** ወለደ። ያዕቆብ ከሁለት ሚስቶቹና ከሁለቱ የቤት ሰራተኞቹ **አስራ ሁለት** ልጆችን ወለደ።

እንግዲህ ለውይይታችን አልያም ለርዕሳችን ይመች ዘንድ በጥልቅ ባይሆንም የሰውን ምንጭና አወራረድ በጥቂቱ ተመልክተናል፣ ይህንንም <u>ክልላዊ</u> የዝርዝር ምንጭ ለመመልከት ያስችል ዘንድ ኢንሳይክሎፒዲያን ለመጠቀሜ ሳልገልፅ አላልፍም።

ኤሎሂም ከዚህ ከዘረዘርናቸው ሰዎች ሁሉ ወስጥ ቃል ኪዳኑን የገባውና ኪዳኑን ያፀናው <u>**ከአንድ ሰው**</u> ጋር ብቻ ነበር።

ኤሎሂም ቃል ኪዳን የገባውና ከሌሎች ህዝብ በላይ አስበልጦ የወደደውና ታላቅ እድሎ ያደረገለት ከሴም ለፈለቀው <u>**ለያዕቆብ**</u> ብቻ ነበር **(ዘፍ፣ 46)።** **ከዚህም የተነሳ ነው ኖህ የሚያስደንቀውን ትንቢት "የሴም አምላክ ኤሎሂም" ብሎ የተነበየው።**

ለሁላችንም ግልፅ እንዲሆን ያዕቆብ ቤተሰቡ ተረከዝ ያዢ ነው በማለት ያወጡለት ስሙ ነበር። ሆኖም ግን ከዘመናት ቆይታ በኋላ "ከሰዎች ጋር



ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ <u>**እስራኤል**</u> እንጂ ያዕቆብ አትባልም" በመባል ምንጩ መለኮታዊ የሆነ ተለውጧዊ ስም ወጣለት (ዘፍ 32፡28)።

ከዚህ የተነሳ የምንደመድመው ጉዳይ የኤሎሂም ቃል ኪዳን የተሰጠውና የኤሎሂምን አድኗዊ ፅናት ያገኘው **ከሴም ለፈለቀው እስራኤል** ብቻ **ነበር።**

ጥንት የኤሎሂም ህዝቦች ካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስ፣ እስላም፣ ጴንጤ..ወ.ዘ.ተ. በመባል አይለዩም ነበር። መለያቸው የነበረው <u>**እስራኤላዊ**</u> የሚል ብቻ ሲሆን፣ ከእስራኤላውያን ውጪ ያሉ ህዝቦችም ሁሉ መለያ ስማቸው <u>**አህዛብ**</u> የሚል **ነበር።**

ከመሰረት ቃሉ ስንነሳ አህዛብ የሚለው ቃል በእብራውያን ቋንቋ "ጎይም (GOYIM)" ማለት ሲሆን፣ ትርጉሙም ከእስራኤላውያን ውጭ ያለ ሕዝብ ሁሉ የሚጠራበት የጥሪ ስም ነበር።

ማወቅ ያለብንና በድፍረት የምገልፀው እውነት ቢኖር፣ ሌላው ቀርቶ የብዙዎች አባት የነበረው አብረሃም እንኳ <u>በትውልዱ</u> እስራኤላዊ አልነበረም። **የአብረሃም ልጆች የነበሩት እስማኤልና ይስሃቅ በትውልዳቸው እስራኤላዊ አልነበሩም።**

እስራኤላዊያን የተባሉት ከእስራኤል (ከያዕቆብ) የተወለዱት ብቻ ነበሩ።

ተቀበልንም አልተቀበልንም ከያዕቆብ (እስራኤል) ልጆች ውጪ ያለ ህዝብ ሁሉ የኤሎሂም ሕዝብ ያልነበረ ሕዝብ ነበር። ሁሉም መጠሪያው አህዛብ ነበር፣ ስለዚህ በወቅቱ በምድር ላይ ሁለት አይነት ህዝብ ሲኖር፣ እነርሱም እስራኤልና አህዛብ ተብለው ይለዩ ነበረ። **ይህ ሕዝብም ጠበኛ የነበረ ሕዝብ ነበር።**

የእስራኤልና የአህዛብ ጠበኝነታቸው በእንዲህ እንዳለ፣ **እስራኤላውያኖች አህዛቦችን ወደ ሃይማኖታቸው፣** አህዛቦችም እስራኤላውያኖችን ወደማይናገሩት ጣኦቶቻቸው ይገባበዙ ነበር። ለዚህም ማስረጃ እንዲሆን እየሱስዬ "...አንድን ሰው ወደ አይሁድ ሃይማኖት ለማስገባት በባህርና በየብስ ስለምትጓዙ፣ ባመነም ጊዜ ከእናንተ በእጥፍ የባሰ የገሃነብ ልጅ ስለምታደርጉት ወዮላችሁ" በማለት የተናገረውን እናነባለን (ማቴ 23፡15)።

እስራኤላውያኖች አህዛቦችን ወደ አይሁድ ሃይማኖታቸው ይጋብዟቸው እንጂ፣ ወደ ኤሎሂም ኪዳን ግን ሊያስገቧቸው ፍፁም አይችሉም ነበር፣ ምክንያቱም ኪዳኑ በትውልድ ከእስራኤል ለወጣ ህዝብ ብቻ ነበርና።

ከመሰረት ቃሉ ስንነሳ አህዛብ ማለት ከእስራኤላውያን ውጭ ያለ ሕዝብ ሁሉ የሚጠራበት የጥሪ ስም እንደሆነ ከተግባባን ፣ **ኢትዮጵያዊ ሁሉ በትውልድ ከያዕቆብ ስላልሆነ አህዛብ የሆነ ሕዝብ ነበር።**

ቀደም ብለን ትውልዶችን በዝርዝር የተመለከትንበት ዋናው ጉዳይ ይህንን እውነታ ለማፅደቅ ነው። ስለዚህ ከያዕቆብ ያልተወለደ በአለም ዙሪያ ያለ ሕዝብ ሁሉ አህዛብ ነበር ማለት ነው።

ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን በትውልድ አህዛብ ስለነበርን የኤሎሂም ህዝብ አልነበርንም!!

**ክልላችንን ለክተን ስንናገር በዚህ ዘመን ክርስቲያን ይሁን እስላም ተብሎ የሚጠራ ኢትዮጵያዊ በሙሉ አህዛብ ነበር።**

ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከኤሎሂም ወገን ያልሆነ ስለነበር፣ ይህም ማለት አህዛቦች ስለነበርን ነብዩ ዳዊት "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ኤሎሂም ትዘረጋለች" አለ (መዝ 68፡31)።

ይህ ነብዩ ዳዊት የተናገረው ቃል በእንግሊዘኛው ትርጉም ስናነበው በይበልጥ ውበቱን ይገልጠዋል። ኪንግ ጀምስ (King James) በሚለው ትርጉም "Ethiopia **shall** **<u>soon</u>** stretch her hands unto God" ይላል። "Shall soon" የሚለው ቃል ትልቅ ጉድለት በአማርኛው ትርጉም ውስጥ አስገብቷል፣ ምክንያቱም "Shall soon" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተደርጎ ያልነበረ ሆኖም ግን <u>በቅርቡ በግድ</u> የሚደረግ መሆኑን የሚያጎላ ቃል ነው።

ይህንን ጥቅስ ብዙ ቄሶች፣ ባታውያኖች፣ ፓስተሮች፣ ወንጌላውያኖች፣ አስተማሪዎች...ው.ዘ.ተ. ትክክለኛ ባልሆነ ምልከታ በመተርጎም ሃይል አልባ አድርገውት፣ ለችግር፣ ለረሃብ፣ ለጦርነት፣ <u>ለፖለቲካ</u> ..ወ.ዘ.ተ. ማፅናኛ አድርገውብን ተመልክተናል።

ነብዩ ዳዊት ይህንን ቃል የተናገረው ነብይ ስለነበረ ኤሎሂም ሕዝቡ ያልሆኑትን ሕዝብ የሚያደርግበትን መንገድ በነብዩ ዳዊት አንደበት ሲያፀና ነበር። ነብዩ ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁሉ እየተናገረ የነበረው ስለ **<u>መሲሁ</u>** ነበር (መዝ፡ 68)።

በሌላ ስፍራ ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ነብዩ ኢሳይያስ ስለ **<u>መሲሁ</u>** እያወራ "ኤሎሂም እጁን ዘርግቶ ከአሶር፣ ከታችኛው ግብፅ፣ ከላይኛው ግብፅ፣ **<u>ከኢትዮጵያ፣</u>** ከኤላም፣ ከባቢሎን፣ ከሓማትና ከባህር ጠረፍ ምድር ሕዝብን ይሰበስባል" ይላል (ኢሳ 11፥11)።

**ለመሆኑ ይህ መሲሁ የተባለው ለምንና <u>ለማን</u> ሊመጣ ተገባው?**

ለዚህ ምላሽ ከመደርደራችን በፊት በቅድሚያ ማወቅ የሚገባንን የተጨበጠ ጉዳይ እንመልከት።

ኢትዮጵያ በትውልዷ አህዛብ እንደሆነች ተመልክተናል። ብዙዎች በዘልማድና <u>በውርስ</u> የምናምነው የራሳችን የሆነ እምነትና በገዛ ራስ ላይ የተፈጠረ የአምልኮ ስሜት ስላለን፣ ይህንን እውነት ለመቀበል ምናልባት ያዳግተን ይሆናል።

**ተቀበልንም አልተቀበልንም ኢትዮጵያ በትውልድ አህዛብ ተብለው ከሚቆጠሩ፣ የኤሎሂም ህዝብ ያልነበረችና ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ አምላኳ እንዳልነበር ማወቅ አለብን።** ይህ እንቁ ነገር ካልገባን መሲሁ የመጣበት ጥቅሙ አይገባንም።

**እውነት ትግለጠን ከተባለ፣ ሕግን መቀበል፣ የኤሎሂም ልጅ መሆን፣ መለኮታዊ ክብር፣ ኪዳን፣ በወርቅ የተለበጠው የኪዳን ታቦት፣ የኪዳኑ ፅላት፣ ስርየቱ፣ የቤተ መቅደስ ስርዐት፣ የቤተ መቅደስ አገልግሎት፣ የወርቅ ማዕጠኑ፣ የመንግስት ካህንነትና ተስፋ ሁሉ የእስራኤል ብቻ ነበር።**

የኪዳን ታቦት ለእስራኤል እንጂ ለኢትዮጵያ አልነበረም፣ አይደለም። የክህንነት አገልግሎት ለእስራኤል እንጂ ለኢትዮጵያ አልነበረም፣ አይደለም። **ኢትዮጵያዊ እስራኤላዊ አይደለም።**

የኪዳን ታቦት፣ የክህነት አገልግሎት፣ የወርቅ ማዕጠን፣ መስዋዕቱ....ሌላም ሌላ ሁሉ የመጣው በሕጉ በኩል ነበር።

ይህ ሕግ የመጣው ደግሞ ያህዌ ለአብረሃም ከሰጠው ተስፋ አራት መቶ ሰላሳ አመት በኋላ እስራኤል ከምድረ ግብፅ ባርነት ነፃ እንዲያወጣቸው በተመረጠው በሙሴ በኩል ነበር **(ዘፍ፣ 19)።**

ሕጉም የተሰጠው በግብፅ ባርነት ላይ ለነበረው ህዝብ **ብቻ** ነበር (ሚል 4፡4)። በግብፅም ባርነት ላይ



የነበረው ሕዝብ የሙሴ ወገን የነበሩት የያዕቆብ **(የእስራኤል)** ልጆች ብቻ ነበሩ **(ዘፀ 5፡2)።**

ስለዚህ ሕጉ የተሰጠው ለአህዛብ ወይም ለኢትዮጵያ ሳይሆን **በወቅቱ** ኤሎሂም ሕዝቡ ለነበሩት ለእስራኤል ብቻ ነበር (ሚል 4፡4)።

**እስርቱ ትዕዛዛት፣ የፍትህና የምህረት ሕጎች፣ የዐውደ አመት በዐላት፣ የኪዳን ፅናት፣ የመገናኛ ዱንኳኖች፣ የህብስት ስርዐት፣ የማደሪያ ድንኳን፣ የመብራት መቅረዞች፣ የቃል ኪዳን ታቦት፣ የሚቃጠል መስዋዕት፣ የመቅርዕ ዘይት፣ ልብሰ ተክህኖ፣ የዕጣን ማጠን ስርዐት፣ የአራተኛው የአምስተኛው የሰባተኛውና የዐስረኛው ወር ጾሞች... ወ.ዘ.ተ. ሁሉ የእስራኤል እንጂ የኢትዮጵያ አልነበረም!!!**

ይህ ከሆነ እውነቱ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ወይም ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ያሏቸው ታቦታቶች፣ ልብሰ ተክህኖ፣ ፅላቶች፣ የዕጣን ማጠን ስርዐቶች፣ ጾሞች....ወ.ዘ.ተ ምንጫቸው ከየት ነው?

ኩሽ **(ኢትዮጵያ)** የካም ልጅ እንጂ የያዕቆብ **(እስራኤል)** ልጅ አልነበረም። ኩሽ (ኢትዮጵያ) የያዕቆብ ልጅ ካልሆነ ታቦቱ፣ ኪዳኑ፣ ትዕዛዛቱ፣ አስራቱ፣

ክህነትነቱ፣ እጣን ማጠኑ፣ የመቅደስ አገልግሎቱ ከየት መጣ?

ይህን ሁሉ ይዘን እናመልካለን ብለን <u>ከመረጥን፣</u> የኮርማዎቹ ደም፣ የሚቃጠለው አውራ በግ፣ የማይጠፋው የመሰዊያው እሳት፣ የስብ መቃጠሉ፣ የኮርማ ደም መረጨቱና የሰባት አመት እረፍቱስ የታለ?

**ኢትዮጵያዊ እስራኤላዊ አይደለም!!!!!!**

**<u>የጴንጤውስ</u>** በገንዘብ አጀባ ከመጠመድ የተነሳ **<u>በአስራት</u>** ወላፈን የሚወበቀው ከምን የተነሳ ነው? አስራት **<u>እንዲሰጥ</u>** የታዘዘ እስራኤላዊ ብቻ ነበር።

አስራት በመገናኛ ድንኳን ለሚያገለግሉትና ለሚሰሩት ስራ ደመወዝ እንዲሆናቸው **<u>ለሌዋውያን ብቻ</u>** ኤሎሂም ርስት አድርጎ የሰጣቸው ነበር።

ሌዊ የያዕቆብ (የእስራኤል) ልጅ ሲሆን፣ የእርሱ ቤተሰብ ሁሉ የሌዊ ነገድ ይባላል። ኤሎሂምን ለማገልገልና የእስራኤላውያንን ግዴታ ለመወጣት የመገናኛውን ድንኳን ሁሉ እንዲጠብቁና በውስጡም እንዲያገለግሉ በኤሎሂም የተመረጡ ጎሳዎች ነበሩ።

ይህ ነገድ በእስራኤላውያን መካከል **ርስት** የለውም ነበር። በዚህ የተነሳ እስራኤላውያን መባ



አድርገው ለኤሎሂም የሚያቀርቡትን **<u>አስራት</u>** ለሌዋውያን ርስታቸው ነበር። ይህ ነገድ <u>ብቻ</u> ነበር አስራት **<u>እንዲቀበል</u>** የተደነገገለት (ዘኁ፡18)። ይህም ከእስራኤል ፊልቆ ለእስራኤላውያን <u>ኪዳን</u> ሆኖ የፀና ነበር።

እስራኤላውያኖች ይህንን ኪዳናቸውን ስላልጠበቁ፣ ኤሎሂም በነብዩ ሚልኪያስ በኩል "... እናንተ <u>የያዕቆብ ልጆች ሆይ፣</u> <u>...አስራትና</u> መባ ትሰርቁኛላች..." በማለት ሲከሳቸውና ሲወቅሳቸው እናነባለን። <u>"የያዕቆብ ልጆች"</u> የሚለው ቃል የሃላፊነትን ድርሻና የሰራቂውን ባለቤትነት እንደሚያሳይ መዘንጋት የለብንም (ሚል 3፡6-10)።

<u>ኢትዮጵያዊ እስራኤላዊ ወይም የያዕቆብ ልጅ ስላልሆነ አስራት መስጠቱ ገንዘብ ማባከኑ እንጂ ሰማያዊ እውቅና የለውም።</u> <u>አስራት መስጠትና መቀበል የኢትዮጵያዊ ሃላፊነት አይደለም።</u>

አስራት "ሰማያዊ እውቅና" አለው ብለን የምንሟገት ከሆነ፣ ሕጉ የሚያዘውን **<u>ሁሉ</u>** **(613 ሕጎችን)** ሳናስቀር መፈፀም አለብን። <u>አስራት የቀድሞ ኪዳን</u>

ስለሆነ፡ ጴንጤውም እንደ ኦርቶዶክሱና ካቶሊኩ በሁለት ኪዳን ውስጥ እንደተዘፈቀ ማወቅ ይኖርበታል!!

ይህ በእንዲህ እንዳለ፡ **በወቅቱ** የምድር ሕዝብ ሁሉ በኤሎሂም ፊት መለያው እስራኤልና አህዛብ ተብሎ ብቻ **እንደነበር** አይተናል። ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ጴንጤ፣ የይኖዋ ምስክሮች፣ እስላም.. ወ.ዘ.ተ. የሚባሉ ሃይማኖቶች ሆነ ተከታዮች **በወቅቱ** አልነበሩም።

ሌላው ቀርቶ ክርስትና እንኳ የተጀመረው ከ2,785 አመታት በኋላ ሲሆን፣ በዚያ ሁሉ ዘመናት ግን የኤሎሂም ሕዝብ የሚባሉት እስራኤል **ብቻ ነበር።**

ኤሎሂም የእስራኤላውያን አምላክ ብቻ ከነበረ፣ አሁን በምድር ዙሪያ የሚኖር በትውልድ እስራኤላዊ ያልሆነ ፍጥረት ሁሉ አምላክ ብሎ የሚያመልከው አምላክ ማነው?

ቀደም ብለን እንዳየነው የኤሎሂም ሕዝብ በነበረውና የኤሎሂም ሕዝብ ባልነበረው ህዝብ መካከል ከፍተኛ ጠብ ነበረ።

ይህ ሁለት የተለያየ ሕዝብ በአንድነት ወይም በሕብረት ሊያደርገው የተገባና የተፈቀደ አንዳች ነገር አልነበረም። የትዳር ትስስራቸው እንኳ ትውልዷዊነት



ያቀፈው መሆን ነበረበት፣ ከዚህም የተነሳ ማርያምና አሮን፣ ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ ስለነበር ባገባት ኢትዮጵያዊት ምክንያት ነቀፉት (ዘኁ 12:1)።

በኤሎሂም ፊት በወቅቱ ለነበሩት የሕዝቦች ልዩነት አድሏዊነት ነበረው። ከዚህ የተነሳ እስራኤላውያን ከአህዛቡ የተለየና የተቀደሰ አኗኗር ይኖሩ ዘንድ ሕጉ ከነትዕዛዛቱ በኪዳን ፅናት ተሰጣቸው።

ነገር ግን ይህ ኪዳን የተሰጠው ህዝብ ኤሎሂም እንደሚፈልገውና እንደሚመኘው ለመኖርና የነፍሳቸውን እርካታ ለማግኘት አልቻሉም። ከዚህ የተነሳ ይጠብቁትና ህይወት ይሆናቸው ዘንድ የተሰጣቸውን ሕግ ቀጥ በሌለው መንገድ ተላለፉት።

የእስራኤላውያን አኗኗርም ከአህዛቡ የተለየ አልሆነም፣ ኤሎሂምም "በዙሪያችሁ ካሉት **አህዛብ** ይልቅ ሞገደኞች ሆናችኋል" በማለት በሕዝቅኤል በኩል ወቀሳቸው (5:7)።

ግፍ፣ ክፋት፣ ዝሙት፣ ሴሰኝነት፣ መዳራት፣ ጥንቆላ... ወ.ዘ.ተ. በእስራኤላውያን መካከልም ገነነ። ይህ ሁኔታቸው የኤሎሂምን ወዳጅነት አሳጣ። ሙሴ

እንዳለው ኤሎሂም ሕዝቡ ወዳልነበሩት አህዛቦች በመሄድ እስራኤልን ለማስቀናት መረጠ (ዘዳ 32፡21)።

**ይህ የኤሎሂም ውሳኔ ግን ለእስራኤል የገባውን ኪዳን ማፍረስ ስለሚሆን፣ የገባላቸውንም ተስፋና ኪዳን ማጠፍ ይሆንበታል።** ስለዚህ ኪዳን ሳያፈርስ እንዴት ሕዝቡ ወዳልነበሩት ፊቱን ማዞር ይችላል?

ለምሳሌ፣ አንድ የቆዳ ጫማ በገበያ ስፍራ ብመለከትና ብገዛው፣ ከወር በፊት ገዝቼ የነበረውን በቀለሙ ተመሳሳይነት ያለውን ሌላ የቆዳ ጫማ ወደ ቆሻሻ መጣያ ያስጥለኛል ማለት አይደለም። ነገር ግን አዲሱ ጫማና አሮጌው ጫማ በማለት እለያቸዋለሁ።

በተመሳሳይ መልኩም ኤሎሂም ለእስራኤል የተሰጠውንና ሊመጣ ላለው አምሳል የነበረውን ኪዳን አሮጌ አድርጎ ሌላ የተለየ ዘላለማዊ፣ የማይለወጥ፣ የማይሻርና የተሻለ ኪዳን ለማምጣትና ለማፅናት ጎህ ማፅናት ግድ ነበር። ይህ ፅናት ግን እንዴት ህልውና ሊያስገኝ ይችላል?

ኤሎሂም ሁለት ጠበኞች የነበሩትን ሕዝቦች አዲስ በሆነ ኪዳን ሊያቀራኝ የሚችልበት መንገድና የሃላፊነት ድርሻ ለመቀበል የሚችልና ብቃት ያለው



በወቅቱ ከሴት የሚወለድ አንድም ሰው አልነበረም። ስለዚህ ኤሎሂም የሚወደውንና ትልሙን የሚያከናውንለትን ሰው እስኪገልጥ ድረስ ከአዳም አመፃ ጀምሮ አምስት ሺህ አምስት መቶ አመታት ተቆጠረ።

እዚህ ጋር መዘንጋት የሌለብን እውነት ቢኖር፣ ከኖህ ትንቢታዊ ፅናት ጀምሮ መሲሁ እስኪገለጥ ድረስ **ኢትዮጵያዊ ሁሉ አህዛብ ነበር። ምናልባት የሃዋርያት ስራ ላይ የተፃፈውን የኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ታሪክ ስናነብ ጥያቄ ሊፈጠርብን ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ቀደም ብለን እንደተመለከትናው በትውልድ እስራኤላዊ ያልሆኑትም ወደ አይሁድ ሃይማኖት እንደተጨመሩ እየሱስ የተናገረውን ተመልክተናል። ስለዚህ ይህ ጃንደረባ ትውልድ አልባ በሆነ አይሁድነቱ ሊሰግድ ወደ እየሩሳሌም ሄዶ ነበር (ሃዋ 8፡26-29)።**

ኤሎሂም ሊያመጣ ለነበረው የሕርቅ መንገድ ብዙ ነብያቶች ተንብየው አልፈዋል። የተነበዩትም ከግምታዊ ምልከታ ሳይሆን ከተስፋ ነበር። ተስፋ ማለት የተወቀረና ይሆናል ብለን በድፍረት የምንጠባበቀው ጉዳይ ነው።

ለምሳሌ፣ አንድ ወዳጄ ከአስመራ ሊጎበኘኝ እመጣለሁ ቢል፣ የምጠባበቀው ተስፋ ወዳጄን ብቻ እንጂ ሌላ አዲስን ሰው አይሆንም። በተመሳሳይ መልኩ ኤሎሂም ሁለት የነበረውን ሕዝብ ልዩነት ሊያስወግድ የመረጠበት መንገድ ጥንት ለብዙ ነብያቶች **የታወቀ** ሲሆን፣ ነገር ግን ለእነርሱ **ያልተገለጠ** ስለነበር ሳይገለገሉበት ከመናገር ብቻ አላለፉም ነበር።

የወቅቱ ነብያቶች እና ቅዱስ መላዕክቶች ሁሉ በማስረገጥ ሊመጣ ላለው ነገር በድፍረት ተለሙ።

ይህም የፅናት ቃል መጠሪያው **"መሲሁ"** የሚል ነበር።

መሲህ የሚለው ቃል በጅምርት የመጣው ከአይሁድ ሲሆን፣ ትርጉሙም የተቀባው ማለት ነው። እዚህ ጋር ማስተዋል የሚኖርብን ቁምነገር ቢኖር፣ ቃሉ የተቀባ አይልም፣ የሚለው የተቀባው ነው።

**የተቀባ** የሚለው ቃል ተሰጥዋዊ ምልክታ የሌለውና ላልተገመተ ሰብዐዊ ፍጡር የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ በኤሎሂም ተቀብተው ያለፉ ሰዎች እንደነበሩ እናነባለን።

እነዚህ ሰዎች ለመቀባታቸው ማረጋገጫ የነበረው በላያቸው ላይ ዘይት ሲፈስባቸው እንጂ ቀደምት የሆነ



ፅናታዊ የቅባት ማረጋገጫ የላቸውም ነበር። ይህ ማለት ዘይት በላያቸው ከመፍሰሱ በፊት የተቀቡ አልነበሩም፣ ዘይቱ ከፈሰሰባቸው በኋላ የተቀቡ ይባላሉ።

ስለዚህ የተቀባው (መሲሁ) ከሌሎቹ የተቀቡ ሰዎች የተለየና **አስቀድሞ** የተቀባና ለሰው ያልተገለጠ ነበር።

ይህ የተቀባው (መሲሁ) ይገለጥ ዘንድ በብዙ ነብያቶች አንደበት **ከሶስት መቶ ያላነሰ** ትንቢት እንደተነገረለት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እናነባለን። እነዚህ ነብያቶች የተነበዩለት ይህ መሲህ ማንነቱ በአይሁድ ዘንድ ስለማይታወቅ የተነገሩለትን **ትንቢቶች ሁሉ መፈፀሙ ማረጋገጫው ነበር (ሉቃ 24፡44)።**

አይሁዳውያን በትንሹ የዛሬ ሶስት ሺህ አመት የዚህ መሲህ ወቅቱን ጠብቆ መምጣት የሚንገበገቡለትና መውለድም የምትችል እስራኤላዊት ሴት ሁሉ መሲሁን ለመፀነስ የሚመኙት ታላቅ ተስፋቸው ነበር።

መሲህ የሚለው ቃል በግሪክ ደግሞ ክርስቶስ ማለት ሲሆን፣ ለዚህም ነው እየሱስ ክርስቶስ ወይም ክርስቶስ እየሱስ የሚለው ስም የመጣው።

የሚደንቀው ግን አይሁዶች (ሁሉም ሳይሆኑ) እየሱስ ነብይ እንጂ ክርስቶስ አይደለም ብለው ይመኑበት እንጂ፣ በእስልምናው ክልል ታላቅ ነብያቸው የሆነው ነብዩ መሃመድ እንኳ እየሱስ ከሞተ ከ600 አመታት በኋላ መጥቶ የእየሱስን ክርስቶስነት መስክሯል (ሱራ 3:40)።

እየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ማንነቱ ለአይሁዶች ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች ጥያቄ ሆኖ ነበር።

ብዙ የታሪክ ፀሃፊዎችም እየሱስን እንደ ሃያል መሪና ድንቅ አስተማሪ ብቻ የቆጠሩበትም ወቅት ነበር።

በአውሮፓውያን ታሪክ ውስጥ እጅግ የሚፈራውና እውቅናው የገነነው ፈረንሳዊው ናፖልዮን ስለ እየሱስ ማንነት ሲገልፅ፣

> "...አሌክሳንደር፣ ቄሳር፣ ቻርሊ ዘ ግሬትና እኔ ራሴ በጉልበት ታላቅነትን አገኘን፣ **እየሱስ** ግን **ብቻውን** ሆኖ የራሱን ታላቅነት <u>በፍቅር</u> አፀና፣ እንደ እርሱ ሰው ብንሆንም ማንኛችንም እንደ እርሱ ልንሆን አንችልም፣ **እየሱስ ከሰው በላይ ነውና።** እየሱስ ያለ ገደብ የሚፈልገው የሰውን



ልብ ብቻ ነው፣ ይህ ለእኔ ድንቅ ሆኗል። ይህ ስራው ነው የእየሱስን **መለኮታዊነት** እንድመለከት ያስቻለኝ..." በማለት እንደተናገረ ታሪክ ይመሰክራል (The Divinity of Our Lord & Savior Jesus Christ; H.P. Liddon: 1860-1870)።

የኤሎሂም ህዝብ ለመሆን የሚያበቃን ቁልፉ የእየሱስን ማንነት ማወቅ ነው። እየሱስ ከተወለደበት ቀን አንስቶ የተነሳ ጥያቄ ቢኖር "እየሱስ ማነው?" የሚል ነበር። ለእዚህም ነው እስከዛሬ ድረስ አይሁዳውያን እየሱስን በመቃወም "የዮሴፍ ልጅ አናፂው የናዝሬቱ እየሱስ" ብለው <u>ክርስቶስነቱን</u> በተቃውሞ የሚመለከቱት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በኤሎሂም ሃላፊነት አንፃር እየሱስ ጅምርት አመጣጡ <u>ለማን</u> እንደነበር ለማየት እንሞክር።

ነብዩ ዳንኤል የራሱንና <u>የእስራኤልን</u> ሃጥያት እየተናዘዘ ሲፀልይና ስለ ቅዱስ ተራራውም ያህዌ አምላኩን እየለመነ ሳለ፣ መልአኩ ገብርኤል በፍጥነት እየበረረ ወደ ዳንኤል መጥቶ "ዳንኤል ሆይ፣.... አመፃን

ለማስቆም፣ ሃጥያትን ለማስወገድ፣ በደልን ለማስተሰረይ፣ ዘላለማዊ ፅድቅን ለማምጣት፣ ራዕይንና ትንቢትን ለማተምና፣ እጅግ ቅዱስ የሆነውን ለመቀባት ስለ **ህዝብህና** ስለ ተቀደሰችው ከተማህ ሰባ ሱባዔ ታውጇል" በማለት የመሲሁን ቅድመ ዓላማ በተናጥል ለእስራኤል እንደሆነ ገለጠ (ዳንኤል 9)።

በሌላ በኩል ደግሞ እየሱስ ሲዶና በተባለ አገር በቆየበት ወቅት አንዲት ከነዓናዊት ሴት **(አህዛብ የሆነች)** ወደ እየሱስ መጥታ "የዳዊት ልጅ ራራልኝ፣ ልጄ በርኩስ መንፈስ ተይዛ በጣም ትሰቃያለች" ብላ ጮኸች። እርሱ ግን አንድም ቃል አልመለሰላትም፣ በዚያ ጊዜ የእየሱስ ደቀመዛምርቱ ወደ እርሱ ቀርበው "እየተከተለችን ትጮኻለችና ብታሰናብታትስ?" ብለው ጠየቁት። እርሱም "የተላኩት **ከእስራኤል** ቤት ሆነው ወደ ጠፉት በጎች **ብቻ** ነው" አለ (ማቴ 15፡21-24)።

በሌላም ስፍራ እየሱስ የመጀመሪያዎቹን ዐስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ትዕዛዝ ሲሰጣቸው፣ "ወደ **አህዛ** አትሂዱ፣ ወደ ሳምራውያን ከተማ አትግቡ፣ ይልቁንስ የእስራኤል ቤት ወደሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ" ያለውንም አንዘነጋም (ማቴ 10፡5-6)።



እንግዲህ እየሱስ ጅምርት አመጣጡ ለእስራኤላውያን ብቻ ከሆነ፣ ዛሬ በአለም ዙሪያ ያለው ፍጥረት ሁሉ እንዴት የኤሎሂም ሕዝቦች ለመሆን ብቃት አገኙ?

እየሱስ ቅድመ አመጣጡ በትውልድ ወገኖቹ ለሆኑት ለእስራኤላውያን ቢሆንም፣ ወገኖቹ አልተቀበሉትም ነበር (ዮሃ 1፡11)። **ለምን አልተቀበሉትም??????**

እስራኤላውያኖች ከወገናቸው ለወገናቸው የሆነውን **መሲሁን** ያለተቀበሉበትን ምክንያት ሃዋርያው ጳውሎስ "**ምስጢር** ነው" በማለት ወደ ሮሜ ሰዎች በፃፈው መልዕክቱ ላይ ሲገልፅ፣ "...ወንድሞች ሆይ፣ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ፣ ይህን **ምስጢር** ሳታውቁ እንድትቀሩ አልፈልግም። **የአህዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ፣** እስራኤል በከፊል በድንዳኔ ወስጥ አልፋለች..." (11፡25) አለ።

ሃዋርያው ጳውሎስ የእስራኤል የመደንደን ምክንያትን ደግሞ ሲገልፅ "..እስራኤልን ለማስቀናት ሲባል በእነርሱ (በእስራኤል) መተላለፍ ምክንያት **ድነት ለአህዛብ መጥቷል**...." አለ(11፡11)።

ስለዚህ በትውልዳችን የቁጣና የጥፋት ሕዝብ የነበርን **አህዛብ** ሁሉ በእስራኤል መተላለፍ ምክንያት በረከትን አገኘን። አሜን!

**ኢትዮጵያዊ ሁሉ በትውልዳችን አህዛብ ስለነበርን ከእስራኤላውያን መተላለፍ የተነሳ ለኤሎሂም ሕዝብ የመሆንን መብት በመሲሁ ምክንያት አገኘን።**
ነብዩ ዳዊትም "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ኤሎሂም ትዘረጋለች" ያለው ትንቢት መሲሁ በፈፀመው ድንቅ ስራ ተፈፅሞ ብዙዎች እየኖርንበት እንገኛለን።

ይህንን እውነት ለማስረገጥም እንዲያስችለን ሃዋርያው ጳውሎስ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን በእስር ላይ ሆኖ በኤፌሶን ለነበሩት አህዛብ አማኞች የፃፈውን ደብዳቤ ስናነብ፣ "... እናንተ ቀድሞ **በትውልድ አህዛብ** የሆናችሁ፣ በአካል ላይ በሰው እጅ ከተደረገው የተነሳ፣ ራሳቸውን "ተገርዘናል" በሚሉት "ያልተገረዙ" የተባላችሁ ያን አስታውሱ፣ በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይታችሁ፣ **ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ፣ ለኪዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣** በአለም ላይ **ያለ ተስፋና ያለ ኤሎሂም** እንደ ነበራችሁ አስታውሱ። አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ **በመሲሁ** እየሱስ ሆናችሁ፣



**በመሲሁ** ደም አማካይነት ቀርባችኋል። ሁለቱን **(አህዛብና እስራኤል)** አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ፣ ሰላማችን እርሱ ራሱ ነውና፣ **ሕጉንም** ከትእዛዛቱና ከስርዐቱ ጋር በስጋው **ሻረ።** ዐላማውም ከሁለቱ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ ሰላምን ለማድረግ ነው። ጥልን በገደለበት በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከኤሎሂም ጋር አስታረቀ። መጥቶም **ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ፣ ቀርበው ለነበሩትም ለእነርሱ** ሰላምን ሰበከ፣ ሁላችንም በእርሱ አማካይነት **በአንዱ** መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና" በማለት ውብና ድንቅ የሆኑ መገለጦች አስቀምጦልናል (3፡11-18)።

ከዚህም የተነሳ እነዚህ ቀደሞ ጠበኛ የነበሩ ሕዝብ በክርስቶስ ሕርቅን ካገኙ በኋላ በመካከላቸው የአምልኮ ልዩነት እንዳይገንንና እንዳይፈጠር፣ አንድነታቸውን ለማሳየት "…. አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፣ ከሁሉም በላይ የሆነ በሁሉም የሚሰራ በሁሉም የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ

አለ" በማለት ሃዋርያው ጳውሎስ የተጠሩበትን አንድነት ያለልዩነት እንዲኖሩ የመከራቸው (ኤፌ 4፡3-6)።

ሃዋርያው ጳውሎስ "አንድ ጥምቀት አለ" ሲል፣ ኦርቶዶክስ ወይም ተመሳሳይ እምነቶች እንደሚገልፁት የሕፃንነት ጥምቀትን ሊያስታውስ ሳይሆን፣ እስራኤልና አሕዛብ በክርስቶስ የተነሳ አንድ ሕዝብ ከመሆናቸው የተነሳ የሚከናወነው መንፋሳዊ ትዕይንት <u>ሁሉ</u> የተለያየ እንዳልሆነ ለማሳየት ነው። ምክንያቱም የአሕዛብ ወደ ኤሎሂም መጨመር በእስራኤላውያኖች አይን አንገብጋቢና አወዛጋቢ ጉዳይ ነበርና። ከዚህም የተነሳ በክርስቶስ አማካኝነት <u>አሕዛብና እስራኤላውያኖች</u> በጋራ የሚያመልኩትን አምላክ ለመግለፅ <u>"አንድ አምላክ አለ"</u> በማለት የእረፍት ቃልን አበሰራቸው።

በትውልዳችን አህዛብ የሆንን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ወደ ኤሎሂም የመቅረቢያ መንገድና ምንጫችን **<u>መሲሁ</u>** ብቻ ነው፣ ምክንያቱም ያለ መሲሁ በትውልዳችን ከኤሎሂም የራቅንና ተስፋ ቢስ የተባልን ነበርንና!!!

ስለዚህ ድምዳሜያዊ ቃሉ እስላም፣ ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ጴንጤ፣ የይኖዋ ምስክር... ሌላም ሌላ ሁሉ



በትውልዱ አህዛብ ስለነበርን፣ የኤሎሂም ህዝብ ለመባል **በመሲሁ ማመንና መሲሁን <u>መታዘዝ</u> ይኖርብናል**!!!!!!!

መባ፣ አስራት፣ አስርቱ ትዕዛዛት፣ የፍትህና የምህረት ሕጎች፣ የዐውደ አመት በዐላት፣ የኪዳን ፅናት፣ የመገናኛ ዱንኳኖች፣ የህብስት ስርዐት፣ የማደሪያ ድንኳን፣ የመብራት መቅረዞች፣ የቃል ኪዳን ታቦት፣ የሚቃጠል መስዋዕት፣ የመቅርፅ ዘይት፣ ልብሰ ተክህኖ፣ የዕጣን ማጠን ስርዐት... ወ.ዘ.ተ. ሁሉ የእስራኤል እንጂ የኢትዮጵያ አልነበረም፡ አይደለምም!!!

**ይህም በሙሴ በኩል** የመጣ ኪዳን እንጂ **በመሲሁ** አማካይነት የመጣ ኪዳን አይደለም። **<u>በሁለት ኪዳን መኖርም አይቻልም፣</u>** ስለዚህ የኪዳን ፅናታችን መሲሁ ብቻ ካልሆነ፡ የቀድሞ ኪዳን የሆነውንና በሕግ ላይ የተመሰረተውን ብንፀናበት ከኤሎሂም የራቅንና እስካሁንም አህዛቦች ተብለን እንደምንቆጠር ማወቅ ይኖርብናል!!

<u>አስራት የቀድሞ ኪዳን ብቻ ሳይሆን የእስራኤሎች ብቻ ነው። የቃል ኪዳን ታቦት የቀድሞ ኪዳን ብቻ ሳይሆን የእስራኤሎች ብቻ ነው።</u>

ለልዩነታችን ጥምረት መሲሁ ብቻ ነው! ለሕዝብ ሁሉ የትክክለኛነት ምላሽ እና መድሃኒታዊ ሙላት መሲሁን **ብቻ** በተናጥሏዊ ትልም ማመንና መከተል ከአሕዛብነታችን ማምለጫ መንገድ ነው።

ማመን ማለት ማስተዋል ማለት ሳይሆን፣ ማወቅ ማለት ነው። ማስተዋል የውጫዊ ምሪት አስተዋፆ ሲኖረው፣ ማወቅ ግን ውስጣዊነት ያለው ነው። መንፈስ ሲያውቅ፣ አእምሮ ያስተውላል።

በአእምሮ የተወለደ እምነት ክስረት እንጂ መለኮታዊነት የለውም። አለማመን ያስከተለውን ፍርድና መዘዝ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን።

ይህን ታላቅ እውነት እንድናውቅና እንድናይ፣ ሰማይንንና ምድርን ያፀና፣ ዘላለማዊና ራሱ በራሱ ህላዊ ያለው፣ የሃያላን ሁሉ ሃያል የሆነው፣ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው፣ ጌታና ገዥ የሆነው አዶናይ ህልዋቱን በመንፈሳችን ያኑር! አሜን!

**እየሱስን የማይወድ የተረገመ ይሁን!**



# ምዕራፍ ሁለት

## የዔድን የሞት ጠረን

ቀደም ባለው ምዕራፍ ላይ የመሲሁን ቀንድያ አላማና ትልም ተመልክተናል። በሚቀጥሉት ምዕራፎች ደግሞ የመሲሁን የመለኮት **ስም** እና ማንነቱን በመተንተን ለመመልከት እንሞክራለን።

በጥንት ዘመናት **ስም** እጅግ ውጥን ተሰጧዊ ሃላፊነት ነበረው። በአምላካችንም ዘንድ የስሙ አጠቃቀምና አገባብ ለሚልካቸው መልዕክቶቹ ግንዛቤ ማስረጃዎች ነበሩ።

በቀድሞ ኪዳን ለግለሰቦች ይሰጡ የነበሩት ስሞችም የተሟላ ትርጉም ነበራቸው። ለምሳሌ፣ አዳም የሚለው ስም የተሰየመለት ከተፈጠረበት ምንጭ ሲሆን፣ ትርጉሙም ምድር ማለት ነው (ዘፍ 2)።

በመለኮታዊ እይታም ስም እጅግ ከፍተኛ ስፍራ እንደሚሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን።

ኤሎሂም መለኮታዊ ገፀ በረከትነቱን በስም ላይ ሲያፀና፣ አብራምን ወደ አብረሃም፣ ሰራን ወደ ሳራ፣

ያዕቆብን ወደ እስራኤል፣ ስምኦንን ወደ ጴጥሮስ፣ ሳኦልን ወደ ጳውሎስ... ወ.ዘ.ተ. ለወጣቸው።

የስም ለውጡም ከገጠመኝ የተነሳ ሳይሆን፣ ከመለኮታዊ ብቃት ግኝት የመነጨ ነው። ስምኦን ወደ ጴጥሮስ የተለወጠው የመንግስተ ሰማያት ቁልፍ ስለተሰጠው ነበር (ማቴ 10)።

**የስም ተሰጥኦ ከፍተኛ ስፍራ ከተሰጠው፣ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ የምጠይቀው ጥያቄ ቢኖር፣ "<u>እግዚአብሄር</u>" የሚለው "የአምላክ" ስም መጠሪያው ከየት እንደመጣ ነው? "እግዚአብሄር" የሚለው መጠሪያ ስም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን፣ ሰብዐዊ ተሰጥኦነት ያለው የሃይማኖት ቅርፃዊ ስም ነው። በሰው ተሰጪዊ ብቃት የተወለደው ይህ ስም ሃይል አልባ ከመሆኑ የተነሳ መለኮታዊ ሃይልን ሊፀንስ አልቻለም።**

የመሲሁን ስም ማለትም <u>እየሱስ</u> የሚለውን ስም ስንመለከት ደግሞ የተለየ፣ ሚስጥራዊና ሰማያዊ ትርጉም እንደሚኖረው ብንገምትም፣ የስሙ አክብሮት ስለተለየን፣ የስሙን ዋጋ በተለይ <u>ጴንጤው</u> ከንቱ አድርጎታል። ብርጭቆ ሲሰበር "በእየሱስ ስም"፣ ሽንኩርት ስንልጥ ዐይናችንን ሲያስለቅሰን "በእየሱስ



ስም" ወ.ዘ.ተ. እያልን ስሙን አርክሰነውና ሃይል አልባ አድርገነዋል።

እየሱስ ማለት በዕብራውያን ቋንቋ **"ያሽዋ"** ወይም "እያሱ" ማለት ሲሆን፣ ትርጉሙም "ኤሎሂም አዳኝ ነው" ማለት ነው።

እየሱስ ማለት እንደተመለከትነው "እያሱ" ማለት ከሆነ፣ "እያሱ" ተብለው፣ ተቀብተው የኖሩና ያለፉ ፃድቅ ሰዎች ስማቸው የእየሱስን ያክል መለኮታዊ ሃይል ለምን ተሳነው?" ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ እንችላለን። ምላሹ ግን በምድር ላይ ይኖሩ የነበሩት "እያሱዎች" ስማቸው የቤተሰቦቻቸው <u>የተሰጠ</u> ስም ሲሆን፣ የእየሱስ ስም ግን ከእናቱ ከድንግል ማሪያም የወጣለት <u>ሳይሆን</u> <u>የውርስ</u> ስሙ ነው (ዕብ 1፡4)።

ጥንት የኤሎሂም ተወዳጅ ሕዝብ ተብለው የሚታወቁት እስራኤላውያን የነበራቸው ተስፋ **በመሲሁ** ላይ ሲሆን፡ <u>**አህዛብ**</u> የተባለው ሕዝብ ደግሞ ተስፋ ያደርጉ የነበሩት በመሲሁ <u>**ስም**</u> ብቻ እንደነበር እየሱስ ራሱ ግልጥ አድርጎ ተናግሯል (ማቴ 12፡21)።

ለመሆኑ የአህዛቡ በመሲሁ <u>**ስም**</u> ላይ ተስፋ ማድረጋቸው **ለምን** አስፈለገ?

በያህዌ መልክና አምሳያ የተፈጠረው የመጀመሪያው ሰው በፍጥረቱ የሃጥያተኛ ማንነት አልነበረውም።

ለሕይወት፣ ለመለኮታዊ ስብዕና፣ ለቅድስና፣ ለቀናዊነት፣ ለብርሃንና ለዘላለማዊነት የተፈጠረው ይህ የመጀመሪያው ሰው፣ በመለኮታዊ ምሪትና በውብ ለኖረባት ዔድን ባለማመኑ የሞት ሽታ ሆነባት።

ኤሎሂም ሁሉን አዋቂ ከመሆኑ የተነሳ፣ የመጀመሪያ ሰው በተወሰነለት ሰማያዊ ወይም መለኮታዊ ክልል እንደማይፀና ይወቅ እንጂ፡ በያህዌ አምሳል የተፈጠረው ይህ የመጀመሪያው ሰው ግን እውቅናው አልነበረውም።

በዔድን የአትክልት ስፍራ በመጀመሪያው ሰው ፊት ማንነቱን ለወደፊት ሊተልሙ የሚችሉ የሕይወትና የሞት ዛፍ ተቀመጡለት። የመጀመሪያው ሰው ሁለቱንም ዛፎች የመብላት **መብት** ከኤሎሂም ቢሰጠውም፣ የሞትን ዛፍ እንዲያስወግድም **ትዕዛዝ** ተሰጥቶት ነበር (**ዘፍ 2፥17**)። ይህ ትዕዛዝ ግን በመጀመሪያው ሰው ፍቃድና ምርጫ የሚለካ እንጂ፣ በኤሎሂም ፍቃድ የሚወሰን አልነበረም።

ኤሎሂም ሁሉን አዋቂ ከመሆኑ የተነሳ፣ የመጀመሪያው ሰው የነበረው አዳም የዕውቀት ዛፍ እንደሚበላ አስቀድሞ ቢያውቅም፣ ከትዕይንቱ ግን ሊያስመልጠው የአዳምን **መብት** አልያም **ፈቃድ** ሊጋፋ አልፈለገም ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ግን በአዳም ምክንያት ለሚመጣው ድቅድቅ ፍርድ፣ ኤሎሂም አስቀድሞ አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ፈውስን አዘጋጅቶ ነበር።

ኤሎሂም አስቀድሞ ስላዘጋጀው ፈውስ ሃዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በፃፈለት ሁለተኛው መልዕክቱ ላይ "... ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን ኤሎሂም ነውና፣ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ስራችን መጠን አይደለም። ይህም ጸጋ <u>ከዘላለም ዘመናት በፊት</u> <u>በክርስቶስ እየሱስ</u> ተሰጠን፣ አሁን ግን በመድሃኒታችን <u>በእየሱስ ክርስቶስ</u> መገለጥ ታይቷል" (1፥9-10፣ አሮጌው ትርጉም)።

ይህን የሃዋርያው ጳውሎስን መልዕክት በጥሞና ስናስተውለው፣ ፀጋው የተሰጠው **<u>በክርስቶስ እየሱስ</u>** ሲሆን፣ ፀጋው የተገለጠው ግን **<u>በእየሱስ ክርስቶስ</u>** ነው ይላል። እዚህ ጋር ክርስቶስ እየሱስ እና እየሱስ ክርስቶስ የሚለው ገላጫዊ **<u>ስም</u>** መለኮታዊ ሚስጥር አለው።

**ክርስቶስ እየሱስ** ሲል ጥንት ምድርና ሰማይ ህልውና ሳይኖራቸው፣ በኤሎሂም ታቅዶ፣ ተወስኖና ተበይኖ የነበረው **<u>መሲሁን</u>** ሲያመለክት፣ **እየሱስ ክርስቶስ** የሚለው የስም ገላጭ ደግሞ፣ ጥንት በኤሎሂም የታቀደውና ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረውን <u>መሲህ</u> ከድንግል ማሪያም የተወለደው እየሱስ **<u>እንደገለጠው</u>** የሚያሳይ ነው።

በዘመናት ሚዛን ሲለካ፣ **ክርስቶስ እየሱስ የሚለው ገላጭ ዘመንና ፍፃሜ አልባ መሆኑን ሲያሳሳ፣ እየሱስ ክርስቶስ የሚለው ገላጭ ግን በትንሹ የሁለት ሺህ አመታት ጊዜያቶችን ያስቆጥረናል።**

ለመሆኑ የመጀመሪያው ሰው የፈፀመው ሃጥያት ምን ነበር? ዝሙት ወይስ <u>ወንድሞችን መለያየት?</u>



አዳም ይህንንና የመሳሰሉትን ሃጥያቶች አልፈፀመም ነበር። አዳም የፈፀመው አመፃ ቢኖር፣ ኤሎሂም የመረጠለትን **የህይወት መንገድ** ትቶ፣ እንደ ያህዌ "ለመሆን" በሚስቱ ሄዋን አማካሪነት **የእውቀት መንገድን** መምረጡ ነበር (**ዘፍ 2፡9**)።

ይህ አመፃ በኤሎሂምና በአዳም መካከል መጋረጃ አበጀ። ኤሎሂም የነገረውን **<u>ባለማመኑ</u>** ከኤሎሂም ራቀ! **ካለማመኑም** የተነሳ ሃጥያት ለመፈፀም በቃ።

ከአዳም አለመታዘዙ የተነሳ **<u>የሰው ፍጥረት ሁሉ</u>** ሃጥያት ሳንፈፅምም **<u>ሃጥያተኛነትን ወረስን</u>** (ሮሜ 5፡19)፣ እዚህ ጋር የውርስ ሃጥያት መጽሐፍ ቅዱስ ቁልጭ አድርጎ ቢያስቀምጠውም፣ በተለያዩ የክርስትና እምነቶች የውርስ ሃጥያት አይታመንበትም። ለምሳሌ፣ የክርስቶስ ቤተክርስትያናት (CHURCHES OF CHRIST) የተባሉት የክርስትና ተከታይ ክፍሎች በውርስ ሃጥያት አያምኑም።

ማንነታችን ከአዳም ሃጥያተኝነትን ሊወርስ የቻለበት ምክንያት፣ እንደ አዳም ስጋ ስለለበስን አይደለም። **<u>ስጋን በለበሰ ቢሆን ኖሮ እየሱስም እንደ እኛ ሃጥያተኛ በተባለ ነበር።</u>** ሆኖም ግን አዳም

የእውቀትን ዛፍ መርጦ በበላ ወቅት፣ <u>እኛም በውስጡ ሆነን ስለበላን</u> **<u>ብቻ</u>** <u>ነው።</u>

ይህንን እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ስንመዝነው፣ አብረሃም ነገስታትን ድል አድርጎ ሲመለስ፣ ለመልከ ጼዴቅ ካገኘው ምርኮ ዓስራት አውጥቶ ሰጠው። አብረሃም ይህንን አስራት በሰጠበት ወቅት ይስሃቅም ሆነ ያዕቆብ አልተወለዱም ነበር፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የያዕቆብ ልጅ ሌዊ **<u>(ገና ሳይወለድ)</u>** በአብረሃም በኩል ዓስራትን ከፍሎ ነበር ይላል። ምክንያቱም መልከ ጼዴቅ አብረሃምን ባገኘው ጊዜ፣ ሌዊ ገና በአባቱ በአብረሃም **<u>አብራክ</u>** ነበር (ዕብ 7፡10)። የአብረሃምን ልምምድ ሌዊ **<u>ባይወለድም</u>** በአብረሃም አብራክ ውስጥ ሆኖ **ይለማመደው ነበር።**

ስለዚህ አዳም የሆነውንና ያደረገውን ሁሉ **<u>በውስጡ</u>** ሆነን የስራው ተካፋዮች ሆነናል። ለዚህም ይመስላል ጌታ እየሱስ በምድር ላይ በነበረ ወቅት ፈሪሳውያንንና የኦሪት ሕግ መምህራንን በነቀፈ ወቅት "እውነት እላችኋለሁ ላለፈው ነገር ይህ ትውልድ ይጠየቅበታል" ያለው (ማቴ 23፡36)።



እንግዲህ አዳም ነፍሱ በመቅበዝበዟ መልካምና ክፉውን ለመለየት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ያህዌ ለመሆን ከመሻትዋ የተነሳ በኤሎሂም የመታመንን ፈተና ወደቀች (ዘፍ 3)።

ሰይጣን ለሂዋን (አዳም) እንደ ያህዌ እንደሚሆኑ ዜናውን ያብስራት እንጂ፣ የአዳምና የሂዋን ቀደምት **ፍጥረትነት** በያህዌ መልክና አምሳል እንደሆነ **አዳምና ሄዋን** <u>እውቀት ቢስ</u> በመሆናቸው ሰይጣን መርዙን ረጨባቸው።

አዳምም (ሂዋን) በአምሳሉ የፈጠረውን ያህዌን ሳይሆን በኤሎሂም **የተፈጠረውን** ለማመንና ለመታዘዝ በቃ።

አዳም በተፈጠረ ጊዜ የተሰጠውን ስልጣንም (ዘፍ 1፡26) ለሞት አስረከበ። ከአዳምም የተነሳ ሞት በሰው ሁሉ ላይ ነገሰ (ሮሜ 5፡14)። የዚህም ሞት መንገስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ለ3,090 አመታት አይታወቅም ነበር (ሮሜ 5፡14)፣ ምክንያቱም ሃጥያት በሃጥያትነቱ አልተገለጠም ነበር። ሆኖም ግን በሙሴ በኩል <u>የተጨመረው</u> ሕግ፣ ሃጥያት ምን እንደሆነ ግልጥ

አደረገው፣ ምክንያቱም ሕጉ አታመንዝር ባይል ኖሮ፣ **ሕጉ የተሰጣቸው እስራኤላውያኖች ማመንዘር በጎነት ይመስላቸው ነበር።**

ሃጥያትና ሞት እስከ ሙሴ ድረስ ባይታወቁም ቅሉ፣ የመጀመሪያው አዳምና ከእርሱ በኋላ የነበሩት ሰዎች ሁሉ የሚወርሱት ተመሳሳይ ማንነት ተካፋይ ነበሩ (ሮሜ 5፡19)። ሆኖም ግን አዳምና ተከታዮቹ **የሚለያዩበት** ቁልፍ የሆነ ምልከታ እንዳላቸው ማወቅ የሚኖርብን ጭብጥ አለ። ይህንን ቁልፍ ልዩነት ማወቅ ለእውነተኛ የኤሎሂም ህዝብነትና መንፈሳዊ ኑሯችን እጅግ ወሳኝ ነው።

የመጀመሪያው አዳም ሃጥያተኛ የተባለው ሃጥያት **ስለፈፀመ** ሲሆን፣ እኛ ከእርሱ በኋላ የመጣነው አልያም የተፈጠርነው ሃጥያተኞች የተባልንበት ምክንያት ሃጥያት ስለምናደርግ ብቻ ሳይሆን **ውስጣዊ ማንነታችን** በሽተኛ ስለሆነ ነው። ከዚህ ማንነታችን የተነሳ ሃጥያት ለመስራት ብቃቱን አገኘን።

እስላሙ፣ ኦርቶዶክሱ፣ ካቶሊኩ፣ ጴንጤው፣ ወ.ዘ.ተ. ..የሚያተኩሩት ሃጥያት ማድረጋቸውን እንጂ



**ማንነታቸው** ላይ አይደለም። ይህ ደግሞ ከመለኮታዊ ፅናት እይታ አንፃር ኪሳራ ነው።

አዳም በፈፀመው ሃጥያት ሃጥያተኛ ሲባል፣ ሆኖም ግን እኛ ከአዳም በኋላ የተፈጠርነው እንደ አዳም ሃጥያት ባንፈፅምም በተፈጥሯችን ሃጥያተኞች ሆነናል።

ስለዚህ በመጀመሪያው አዳም የተነሳ ኤሎሂም የሚጠየፈው **ሁለት** ጉዳዮች በእስላሙ፣ በኦርቶዶክሱ፣ በካቶሊኩ፣ በጴንጤው፣ ወ.ዘ.ተ. .ፊት እንዳሉ ለማየት መቻል አለብን፣ እነርሱም **ሃጥያትና ሃጥያተኛነታችን** ናቸው። እነዚህንም ነጣጥለን እንመለከታቸዋለን።

ድሮ ልጅ እያለን በመንደራችን የኮክ ዛፍ የነበራቸው በሃብት ጠገብ ያሉ አዛውንት ነበሩ። የኮኩ ዛፍ እጅግ ከማፍራቱ የተነሳ ኮክ በግቢያቸው መመላለሻ ላይ እንደ አሸዋ ነበር። ይህ በመሬት ላይ የሚትረፈረፈው ኮክ በምሽት ሰክረው ለሚመጡት አባወራ እያንሸራተተ እየጣላቸው ተቸግረው ነበር። ሰራተኞቻቸው ኮኩን ከምድር ለቅመው ቢያጠፉም፣

ከትንሽ ቀናቶች በኋላ በድጋሚ መሬቱን በመትረፍረፍ ይሞላዋል።

አባወራውም በስካራቸው ወቅት ይህ በመሬት ላይ የሚንሰራፋው ኮክ ተመሳሳይ ጉዳት በመደጋገም ያደርስባቸዋል።

ሰራተኞቻቸውም ኮኩን ከመሬት በመልቀም በመደጋገም ተመሳሳይ እርዳታ ያድርጉ እንጂ፣ ዘለቄታዊ ለውጥ ሊያመጣላቸው ግን አልቻለም። ነገር ግን በአንድ ወቅት የአባወራው ወንድም ከክፍለ ሃገር በአጋጣሚ መጥቶ ሁኔታውን ሲመለከት ለአንዴና ለመጨረሻ የሚሆንላቸውን እቅድ ሰጣቸው። ይኸውም **ዛፉን መቁረጥ** ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ መከራቸው። አባወራውም "ህይወቴን ከማጣ ዛፉን ባጣ ይሻላል" በማለት የኮኩን ዛፍ አስቆረጡት። ከዚህ በኋላ የመውደቅና የመቁሰላቸው ልምምድ ተቋረጠ።

የእኛም ኑሮ ከአባወራው ኑሮ ጋር ተመሳሳይነት አለው። የምንፈፅመውን **ሃጥያት** እንደ ኮኩ ብናስበው፣ የኮኩን ዛፍ ደግሞ እንደ **ሃጥያተኛው ማንነት** ማሰብ አለብን።



ወደ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ሃጥያት በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉማዊ ሚዛን ሲለካ ምንድነው?

ሃጥያት የሚለው ቃል እንደ መጀመሪያ ምንጩ ወደ አማርኛ በምንረዳው ተናጥሏዊ መንገድ አልተገለበጠም። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ሁሉ፣ ሃጥያት የሚለው ቃል በየትኛውም ስፍራ ተመሳሳይ መልዕክትና ተናጥሏዊ ያልሆነ ምልከታ አሳድሯል።

ግልጥ አድርጎ ለማሳየት የሚከተሉትን ምሳሌዎች በጥሞና እንመልከት። የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘች ሴት ወደ እየሱስ አመጡና "መምህር ሆይ፣ ይህች ሴት ስታመነዝር ተያዘች፣ ሙሴም እንደዚች ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ በሕጉ አዞናል፣ አንተስ ምን ትላለህ?" ብለው ሲጠይቁት፣ "…. ከእናንተ ሃጥያት የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት" ማለቱን ሃዋርያው ዮሃንስ ፅፎ አስነብቦናል (ዮሃ 8፡3-8)።

ሃዋርያው ዮሃንስ ራሱ በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመርያ መልዕክቱ ላይ "… ሃጥያት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ

የለም። ሃጥያታችንን ብንናዘዝ፣ ሃጥያታችን ይቅር ሊለን ከአመፃ ሁሉ ሊያነፃን እርሱ ታማኝ ፃድቅ ነው…" ብሏል (1፡8-9)።

በኤሎሂም መንፈስ አነሳሽነት ሃዋርያው ዮሃንስ በፃፋቸው ሁለቱ መልዕክቶች ላይ፣ "ሃጥያት የሌለበት" እና "ሃጥያት የለብንም" በሚሉ ተምሳሌያዊ የቃላት አጠቃቀም ተቀምረው እናነባለን። ሆኖም ግን ይህ ተምሳሌያዊነትን የምንመለከተው በአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ እንጂ፣ በሃዋርያው ዮሃንስ ቅድመ ቃል የተቀመረ አልነበረም።

ሃዋርያው ዮሃንስ መልዕክቶቹን ሁሉ የፃፈባቸው ቀጥተኛ የቋንቋ ቀመር በግሪክ ነበር። ሆኖም ግን ከላይ እንደ ምሳሌ የወሰድናቸውን ተምሳሌያዊነት ያላቸውን ቃሎች እንደ ሃዋርያው ዮሃንስ ቀጥተኛ አፃፃፍ እንደሚከተለው ያስነብቡናል።

በመጀመሪያ እየሱስ ከተናገረው ቃላቶች ብንጀምር፣ "…ከእናንተ ሃጥያት (አናማርቲቶስ፣ ANAMARTETOS) የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት" አለ። እንደ ግሪኩ መዝገበ ቃላት ፍቺ



አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) ማለት ሃጥያት ሊያደርግ የማይችል ማንነት ያለው ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ፣ ሃዋርያው ዮሃንስ በመጀመሪያው መልዕክቱ ላይ "…ሃጥያት (ሃማርቲያ፣HAMARTIA) የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም" አለ። እንደ ግሪኩ መዝገበ ቃላት ፍቺ ሃማርቲያ (HAMARTIA) ማለት ትክክል ያልሆነን ነገር አድርጎ ወይም አከናውኖ መገኘት ማለት ነው።

ይህ አመለካከት የቃላት ንትርክ፣ ፀጉር ስንጠቃ ወይም ውሃ ቀጠነ ይምሰል እንጂ፣ ልዩነታቸው ቀናዊነት ለሚኖረው የመንፈሳዊ ህይወት ጉዞ እጅግ የተዋበ መልዕክታዊ ድርሻ አሏቸው። ጊዜን ወስደን በጥሞናዊ ጥናትና በመለኮታዊ ምልከታ ስንመዝናቸው ውስጠ እውቅናቸው እጅግ የተለያየ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን በተሰጧዊ ጥናት ስናነበው፣ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ያሉ ልዩነቶችን የሚመስሉ ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ራእይ ድረስ በትንሹ ሰማኒያ (80) የሚሆኑን እናገኛለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) የሚለው ቃል በተፃፈበት

መልዕክት ሁሉ እንብበን የምንገነዘበው ነገር ቢኖር፣ **<u>ውስጣችንን</u>** እየገፋ **ያለ ፍላጎትና ያለ እውቅና** ክፉ ነገር ወይም አመፃ እንድንፈፅም የሚያደርገን በውስጣችን የሚኖር ሃይል ሲሆን፣ ሃማርቲያ (HAMARTIA) የሚለው ቃል በተፃፈበት መልዕክት ደግሞ የምንረዳው **<u>በውጫዊ</u>** አካሎቻችን ተግብረናቸው የምንገኘው ውጤቶች ናቸው (ለምሳሌ፣ ዝሙት)።

ሃዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በፃፈው መልዕክቱ ላይ "...የማደርገውን አላውቅም ለማድረግ የምፈልገውን አላደርግም፣ ነገር ግን የምጠላውን ያን አደርጋለሁና.......ይህን የማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን በእኔ **<u>ውስጥ</u>** የሚኖረው <u>ሃጥያት</u> (አናማርቲቶስ፣ ANAMARTETOS) ነው" ሲል እንመለከታለን (7፡15-18)። ይህ የሚያሳየን አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) በውስጣችን የሚኖረው ተፈጥሯዊ ወይም አዳማዊ ማንነት እንደሆነ ነው።

ስለዚህ እንደ ሃዋርያው ጳውሎስ አገላለፅ ይህ አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) መላው ብልቶቻችንን **<u>ከውስጥ</u>** ሆኖ መቆጣጠር የሚችል ሃይል መሆኑን እንረዳለን (ቁጥር 23)።



ሃማርቲያ (HAMARTIA) የኤሎሂምን **ይቅርታ** የሚፈልግ መሆኑን ጌታ እየሱስ የአይሁድ ፋሲካን በዐል ባከበረ ቀን "ስለ ብዙዎች <u>ሃጥያት</u> (ሃማርቲያ፣ HAMARTIA) ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ" በማለት ሲገልፅ (ማቴ 26፡28)፣ አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) ደግሞ **ነፃ መወጣት** ያለበት እንደሆነ ሃዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሲፅፍ "<u>ከሃጥያት</u> (አናማርቲቶስ፣ ANAMARTETOS) ነፃ ወጥታችሁ፣ የፅድቅ ባርያ ሆናችኋል" ሲላቸው እናነባለን (6፡18)።

ከዚህ መደምደም የምንችለው ነገር ቢኖር ሃማርቲያ (HAMARTIA) ውጫዊ ሲሆን፣ አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) ደግሞ ውስጣዊ መሆኑን ነው።

<u>ለመልዕክታችንና ለአንባቢዎቼም እንዲመች አናማርቲቶስ (ANAMARTETOS) የሚለውን ሃጥያተኛነት፣ ሃማርቲያ (HAMARTIA) የሚለውን ደግሞ ሃጥያቶቻችን በማለት ለመተካቴ በትህትና አሳውቃለሁ።</u>

መጽሐፍ ቅዱስ <u>ሃጥያተኛነት</u> ከኤሎሂም ይቅርታ ያስፈልገዋል ብሎ አያስነብበንም፣ በተመሳሳይ መልኩም ከ<u>ሃጥያቶቻችን</u> ነፃ መወጣት አለበት በማለትም

አያስተምረንም። ይህን ልዩነት በእውነተኛ ብርሃን ብንመለከት፣ ያህዌ በመሲሁ እየሱስ ለሰራው ስራ ምስጋናችን ታላቅ ይሆንልናል።

እንግዲህ ሃጥያቶቻችን ይቅር ተብሎልንም፣ ሃጥያተኛነት ተቆጣጥሮን መመላለስ እንደምንችልም ማወቅ አለብን። ምክንያቱም ከሃጥያተኛነት ነፃ መወጣት አለበትና።

ሃጥያተኛ ለመባል ሃጥያቶችን መስራት ብቻ ሳይሆን፣ ሃጥያቶችም እንዲሰሩ በሚገፋፋ በሃጥያተኛነት ሃይል ውስጥም ስንኖር ጭምር ነው።

ማወቅ ያለብንና መረዳት የሚገባን እውነት፣ ቀድሞ የፈፀምናቸውና አሁንም የምንፈፅማቸው ሃጥያቶቻችን ወደዚህ አለም በአዳም በኩል አልገቡም። በአዳም የተነሳ ወደ አለም የገባው ሃጥያተኛነት ሲሆን፣ ይህ ልዩነት ፍፁም ግልፅ መሆን ያለበት እውነት ነው። ሳንወለድ፣ ገና በእናታችን ማሕፀን እያለን እንኳ ሃጥያተኞች ነበርን።

ትልቁ ጥያቄዬ ሃጥያቶቻችን ከኤሎሂም ዘንድ እንዴት ይቅርታን ወይም ምህረትን ያገኛሉ የሚል ነው?



በእስላሙ፣ በኦርቶዶክሱ፣ በካቶሊኩ፣ በጴንጤው፣ ወ.ዘ.ተ. **ንስሃ** መግባት የምህረት በር መክፈቻ እንደሆነ ይታመንበታል። ሆኖም ግን ቅዱስ፣ ንፁህ፣ ጉድለት አልባና ብርሃን የሆነውን አምላክ፣ እንዴት እኛ በተፈጥሯችን ያልተቀደስን፣ ነውራም፣ ጎደሎና ጨለማ የሆንን ፍጥረቶች ኤሎሂምን **በቀጥታ** ልንገናኘው እንችላለን?

የማይታይና ገደብ የሌለውን አምላክ እንዴት በሚታይና በሚገደብ ማንነት ልንቀርበው እንችላለን?

ቅዱስ መላዕክቶች እንኳ ኤሎሂምን በፊቱ አይታ የሚያመልኩትበት ምክንያት ህልውናቸው እንደ ኤሎሂም **ቅዱስና መንፈስ** ስለሆኑ ብቻ ነው።

ለምሳሌ፣ ሰው በጋብቻ የሚጣመረው ከሰው ጋር ብቻ እንጂ ከእንስሳት ጋር አይደለም፣ ምክንያቱም ሰው እኩላዊ ግሪት ያስፈልገዋልና። እርግብ ያገባ ሰው ሰምቼ አላውቅም። ውሻም ያገባ አህያ አይቼ አላውቅም። በተመሳሳይ መልኩ ጉድፉም የሆንን **እኛ** (የሰው ፍጥረት ሁሉ) ቅዱስ የሆነውን አምላክ በቀጥታ ለመገናኘት የሚያስችል ብቃት የለንም።

ብቃት ለማግኘት የሚያስችለን ነገርም ቢኖር እንኳ፡ መንትያ ይዘት ሊኖረው ይገባዋል። ይኸውም፣ **በተፈጥሮችን ቅዱስ መሆን አለብን ወይም በአምላክ ፊት በቅድስና ሊያቆመን የሚያስችል ከእኛ ውጭ የሆነ የተቀደሰና የሚቀድሰን ነገር ያስፈልፈናል።**

ቀደም ብለን በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ እንደ ተመለከትነው በትውልዳችን አህዛቦች ነበርን። ኤሎሂምም ሕዝቡ ያልነበርነውን አህዛቦች በመሲሁ በኩል የራሱ ማድረጉ **መዋጀት** ይባላል። አህዛቡም በመሲሁ **ስም** ተሰፋ የሚያደርገው ለዋጆነት ነበር።

ለምሳሌ፣ መዋጀት እንዴት እንደነበር ለማወቅ እንዲያስችለን፣ ለትምህርታችን እንዲሆን ወደ ተጻፈልን የቀድሞው ኪዳን ባለቤት ወደ ሆኑት እስራኤላውያን ታሪክ እንመልከት።

አስቀድመን እንዳየነው ሌዋውያን እስራኤልን ወክለው በያህዌ ፊት የሚቆሙ የተለዩ ወገኖች ነበሩ። ያህዌ አንድ ወርና ከዚያ በላይ የሆኗቸውን ወንዶች **ሌዋውያን** እንዲቆጥሯቸው ለሙሴና ለአሮን ትዕዛዝ ሰጠ። የሌዋውያን ወንዶች ልጆች ጠቅላላ ብዛት ሃያ ሁለት ሺህ (22,000) ነበር።



ያህዌ በማስከተልም "በኩር ሆነው የተወለዱትን፣ አንድ ወርና ከዚያ በላይ የሆናቸውን **እስራኤላውያን** ወንዶች ሁሉ ቁጠር" በማለት ለሙሴ ትዕዛዝ ሰጠው። ሙሴም በታዘዘው መሰረት በኩሮችን ሁሉ ቆጠረ፣ የተመዘገቡት ወንድ በኩሮች ሁሉ ብዛታቸው ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሶስት (22,**273**) ነበር።

እንግዲህ እንደምናየው ከሌዋውያን ቁጥር በሁለት መቶ ሰባ ሶስት በልጦ የተገኘውን እስራኤላውያን በኩሮች **ለመዋጀት፣** ለእያንዳንዱ በኩር ክብደቱ ባለ ሃያ አቦሊ በሆነው በቤተ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን ልክ አምስት አምስት ሰቅል (ግራም) እንዲቀበልና፣ በወቅቱ ሊቀ ካህን ለነበረው ለአሮንና ለልጆቹ እንዲሰጥ ሙሴ በኤሎሂም ታዘዘ፣ በዚህም የተነሳ ቁጥራቸው ትርፍ የሆኑት ሁሉ ለኤሎሂም **ተዋጁ** (ዘኍ 3)።

በተመሳሳይ መልኩ በትውልድ አህዛብ የነበርን ሁሉ፣ አሁን በመሲሁ በኩል የኤሎሂም ሕዝብ የመሆንን መብት ካገኘን፣ ለፅናታችን ማረጋገጫ የሚሆነው **መዋጀታችን** ነው። ሆኖም ግን፣ ቀደም ብለን

እንደተመለከትነው፣ በትውልድ እስራኤላውያን ስላልሆንን **ለመዋጀታችን** ማረጋገጫው ምንድነው?

**መዋጀት** ማለት **ዳግም መግዛት** ማለት ሲሆን፣ ይህም ማለት በትውልድ የኤሎሂም ሕዝብ ያልተባልን ሁሉ፣ **<u>በፍጥረታችን</u>** የያህዌ አምሳል ትክክለኛ ቅጂ ስለሆንን፣ ይህንን ከጅምርት የታቀደልንን መለኮታዊ ኑሮ እንድንኖር፣ እንደገና ወደ ያህዌ የህይወት መዋቅር መመለሻ ብቸኛ መንገድ ነው።

አዳም የእውቀትን ዛፍ ከመብላቱ በፊት ስጋ ለባሽ ቢሆንም እንኳ የነበረው ማንነት ኤሎሂም እጅግ የተደሰተበት ነበር (ዘፍ 1፡31)። ይህንን በቅድስና መዋቅር የተፈጠረውን ጅምርት የአዳም ማንነት ኤሎሂም እንደገና ለመመለስ የሚያስችለው መንገድ **መዋጀ** ይባላል።

እንደ ቀድሞ ኪዳን ሌዋውያን <u>አማካይ</u> ስለማይሆኑልን፣ ኤሎሂም ሃጥያተኛ የሆንነውን የአዳም ዘር ሁሉ የሚዋጅበት መንገድም አዳማዊ መሆን አይኖርበትም። ይህም ማለት <u>አማካይ</u> ሊሆን የሚገባው፣ **ሃጥያት የሌለበትና ቅዱስ** የሆነ፣ ሆኖም ግን እንደ አዳም ስጋ ለባሽ መሆን ይኖርበታል። ነገር ግን ይህን



የሚያሟላ ስጋ ለባሽ <u>ሰው</u> ከየት ይመጣል? **<u>የእየሱስ እናት ማርያም ይህንን ታሟላለችን??</u>**

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሃጥያት የለሽ የሆነና እንደ አዳም **ስጋ** ለባሽ የሆነ **እየሱስ** ብቻ ነው (1 **ጴጥ 2፡22)**።

በዚህ ምድር ላይ የትኛውም የሃይማኖት መስራች የትውልድ ምንጩ ከእየሱስ ጋር ቅርርብ የለውም።

እየሱስ እንደ ሰው ልማድ አልተወለደም። እንደ ሰው ልማድ ቢወለድ ኖሮ መሃመድና እየሱስ እኩል በሆኑ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ እየሱስ በመንፈስ ቅዱስ **የተፀነሰ** የሃይማኖት መስራች የለም። እየሱሴ የሃይማኖት መስራች እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።

የእየሱስ በምድር ቆይታው ላይ ኑሮው ሃጥያት አልባ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ቁራን እንኳ ሳይቀር ያስነብበናል (ሱራ 3)።

የእስልምና፣ የጁዳ፣ የቡዳ፣ የሂንዱ፣ የጂና፣.... ወ.ዘ.ተ. ሃይማኖት መስራቾች ሁሉ ሌላው ቀርቶ **በተፈጥሯቸው** ሃጥያተኞች ናቸው። ከዚህ ማንነታቸው

የተነሳ የሰውን ልብ ሊነኩና ለኤሎሂም **የመዋጂያ** መንገድ ሊሆኑ አይችሉም።

እንግዲህ ኤሎሂም በትውልድ አሕዛብ የነበርነውን ሕዝቦች የዋጀበትን እንቁ መንገድ ሃዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያ መልዕክቱ ላይ ሲያስነብበን "**ከንቱ ከሆነ ሕይወት** __**የተዋጃችሁት**__ በሚጠፋ ነገር፣ በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፣ ነገር ግን እናንተ __**የተዋጃችሁት**__ ነውርና እንከን በሌለበት __**በመሲሁ**__ ክቡር __**ደም**__ ነው..." ይላል (1፡18-19)።

__ሃጥያቶቻችን__ በክርስቶስ እየሱስ ደም በመፅዳት ይቅርታን ያገኛሉ ከተባለ፣ __ሃጥያተኛነት__ ግን ቀድመን እንደገለጽነው ነፃ አውጪ ያስፈልገዋል።

ለምሳሌ፣ አሮጌን ህግ ለመሻር ሌላ ህግ መውጣት እንዳለበት ሁሉ፣ በተመሳሳይ መልኩም ከዚህ __ሃጥያተኛነት__ ነፃ ለመውጣት ሌላ __ሃጥያተኛነት__ መተካት አለበት። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ __"...ሃጥያት (አናማርቲቶስ፣ ANAMARTETOS) የሌለበትን እርሱን (እየሱስን) ኤሎሂም ስለ እኛ **ሃጥያት** አደረገው"__ የሚለው (2 ቆሮ 5፡21)።



__ሃጥያት__ (አናማርቲቶስ፣ ANAMARTETOS) ደግሞ በኤሎሂም ፊት ፍርዱ ሞት ስለሆነ (ሮሜ 6፡23) በሞት ተፈረደበት፣ ከዚህም የተነሳ ሁላችንም ነፃ እንድንሆን ከእርሱ ጋር __ሞተናል__ (2 ቆሮ 5፡14)። ከዚህም የተነሳ ነው አጥማቂው ዮሃንስ እየሱስን "የአለምን __ሃጥያት__ (አናማርቲቶስ፣ ANAMARTETOS) የሚያስወግድ የኤሎሂም በግ" ያለው (ዮሃ 1፡29)።

ለምሳሌ፣ እስራኤላውያኖች ጥቦት ገድለው፣ የቤቶቻቸውን መቃንና ጉበን በደም ባይቀቡ ኖሮ፣ ሬሳቸው ግብፅ በቀረ ነበር (ዘፀ 12)። የእየሱስ መሞት ብቻ ሳይሆን፣ __መስዋዕት__ መሆኑ ነው __ከሃጥያተኛነት__ የሚያስመልጠን! አሜን!

ለእዚህ ሁሉ ግን **በመሲሁ** ስራና ማንነት __**ማመን**__ ያስፈለገናል። ይህ ድንቅ የክርስቶስ ስራ በኤሎሂም መንፈስ አማካኝነት በማንነታችን ላይ በተግባር ለማየት እምነት እንጂ የሃይማኖት ወጀባ አያስፈልገንም።

__እምነት በተግባር የሚለካ፣ በእይታ የሚመዘን፣ በኤሎሂም ሃይል የሚመራ፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚታቀፍና በብዙ መረዳት የሚፀና ነው።__

በአዳምና በኤሎሂም መካከል ጥል የፈጠረው የአዳም አለማመን እንደሆነ መንፈሳችን፣ ነፍሳችንና ስጋችን መረዳት አለበት። የሃጥያት ትልቅና ትንሽ ባይኖረውም፣ <u>አለማመን</u> ግን የሃጥያት ሁሉ ንጉስ ነው።

ኤሎሂም አመፃ የእለት ተዕለት ኑሯችን እንዳይሆን፣ አባወራው የኮኩን ዛፍ እንዳስወገዱት ኤሎሂምም ሃጥያት የሚያመነጨውን ዛፍ (አዳም) ለማስወገድ ከዘመናት በፊት ወሰነልን።

የመሲሁ እየሱስ የመስዋዕት ደም በአምላካችን በኤሎሂም ፊት በንፁህ ህሊና ለመቆም በቂ ሲሆን፣ ነገር ግን ሰው በስቃይ ወላፈን እንዳይኖር የስቃዩን ስር ለማስወገድ ኤሎሂም ለመጀመሪያው አዳም በወቅቱ ባይገባውም ቃል ገባለት (ዘፍ 3፡15)።

ኤሎሂምን <u>በእውነት</u> ሊከተል የሚወድ እነዚህን ሁለት ተናጥላዊ ገፅታዎች በመንፈሱ ካልተረዳ የድል ሕይወት ሊገጥመው አይችልም።

ከሃጥያት ነፃ ለመውጣት የሃጥያትን ምንጭ ማወቁም ዘለቄታዊ መፍትሄ ያመጣል። እውቅናው ከሌለን ግን ለዘወትር መውደቅና መነሳት ይሆናል።



ለምሳሌ፣ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር JUNE 6, 2008 በሃያ ሶስት የአሜሪካን ከተሞች 228 የሚሆኑ ሰዎች ከተመገቡት ቲማቲም የተነሳ SALMONELLA (ሳልሞኔላ) በሚባል ረቂቃን ነፍሳት (BACTERIA) ተለክፈው ሲታመሙ፣ 23 ሆስፒታል ሲተኙ፣ ሁለት ሰዎች ደግሞ ሊሞቱ ችለዋል።

የመንግስት ጤና ክፍል የቲማቲሙን የዘር አይነት ሁሉ ከገበያና ከምግብ ቤቶች ሁሉ አስወገዱ፣ ሆኖም ግን ይህ ቲማቲም ምንጩ ከየት እንደሆነ ስላልደረሱበት ግራ ተጋቡበት። ምክንያቱም ምንጩ ካልተገኘ በሽታውን ፍፁም ለመፈወስ አይቻልምና። በተመሳሳይ መልኩ ከሃጥያት ነፃ ለመውጣት ምንጩ መታወቅና መነቀል አለበት።

እንደተመለከትነው ለምንፈፅማቸው <u>ሃጥያቶቻችን</u> ከኤሎሂም **ይቅርታ ሲያስፈልገን**፣ ከአዳማዊ ማንነት <u>(ሃጥያተኛነት)</u> ግን **ነጻ መወጣት** እንዳለበት አይተናል። ይህ ማለት በኤሎሂምና በእኛ መካከል ከመሲሁ እየሱስ ትንሳኤና <u>ደም</u> የተነሳ ሰላም ኖሮን፣ ከአዳማዊ ማንነት ነፃ ሳንወጣም ልንሰቃይ እንደምንችል ማወቅ

ይኖርብናል። ምክንያቱም **የመሲሁ እየሱስ ደም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ፣ የአዳምን ማንነት ወይም ሃጥያተኛነትን አያፀዳም**። የእየሱስ ክርስቶስ ደም የሚያፀዳው **ሃጥያቶቻችንን** እንጂ **ሃጥያተኛነትን** አይደለም።

ኤሎሂም አለም ሳይፈጠር ጀምሮ የነበረው አላማ ይህንን የመጀመሪያ ሰው (ሃጥያተኛነት) በደም አጥቦና አፅድቶ ለማሽሞንሞን ሳይሆን ፈፅሞ አስወግዶት ሕዝብ ሁሉ ነፃ መውጣት ይችሉ ዘንድ ነው (2 ቆሮ 5፡14)። ይህ ነው ትክክለኛና ፈውስ ሊፈጥር የሚችል **እውነት**።

ይህን ድንቅ የመስቀል ስራ በጽሁፍ ሳስቀምጠው ለያህዌ እውነት ምስክር በመሆን እንጂ፣ አእምሮዬ በእውቀት ስላበጠ አይደለም። ምክንያቱም በኤሎሂም ፊት ለምተላለፋቸው ሃጥያቶቼ ምህረትን እየተቀበልኩኝ፣ በሌላ ገጠመኝ ደግሞ ውድቀት ላይ ስገኝ ስለኖርኩ ሕያው ምስክር ነኝ።

ይህ ማለት ደቀ መዝሙር ሆኜ እንኳ፣ እንደ ባሪያ ያለመብት በሃጥያተኛነት ቁጥጥር ስር ሆኜ ስነዳና ስጨማለቅ በመኖር አስታውሳለሁ። ቀምሼው፣



እንገፍግፎኝና ተሸማቅቄ አልፌበታለሁና ምስክር ነኝ። ያልሆነብኝን ለመመስከር ብቃት የለኝም። ለምስክርነት የሚበቃ በዐይኑ የተመለከተ፣ በእጆቹ የዳሰሰና በማንነቱ ያጣጣመ ብቻ ነው።

ሃጥያተኛነት (የመጀመሪያው አዳም) ለሃጥያቶች ባርያ እንድሆን የሸጠኝ ነበርኩ። ባርያ ደግሞ ለሁለንተናው ሃላፊነት ወይም ፍቃድ የለውም። የገዥው ፈቃድ የባሪያው ፍቃድ መሆን አለበት። ባሪያ በባርነት የሚኖረው ነፃ አውጪ እስኪያገኝም ድረስ ብቻ ነው።

ከሃጥያተኝነት ነፃ የሚወጣው ወይም አዳም ሃጥያት ከማድረግ ሊቆጠብ የሚችለው አዳም በሕይወት መኖር ሲያቆም ብቻ ነው።

አዳም በሕይወት እስካለ ድረስ የዘወትር ድርሻውን ከመፈፀም አይቆጠብም። ይህንን ጠንቅቆ የሚያውቅ አምላክ ለሃዋርያው ጳውሎስ በመንፈሱ በመግለጥ ወለል አደረገለት። ከዚህም የተነሳ ሃዋርያው ጳውሎስ "ከእንግዲህ የሃጥያት ባሮች እንዳንሆን፣ የሃጥያት ሰውነት እንዲሻር **አሮጌው ሰዋችን** ከእርሱ

ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን" በማለት ለሮሜ ሰዎች ግልጥ አደረገላቸው (6፡6)።

የሚያስጨንቀንና የሚወዘውዘን የመጀመሪያው ሰው (ሃጥያተኛነት) በክርስቶስ መስቀል ላይ **ተሰቅሏል**! ሃሌሉያ! ይህ እውነት የምንፀልይበት ሳይሆን የምናመሰግንበት የነፃነትና የድል አምድ ነው።

**የሚያስደንቀው ግን፣ የጴንጤ አስተማሪዎች፣ ፓስተሮች፣ ወንጌላውያን.... ወ.ዘ.ተ. አዳማዊ ማንነት እለት በእለት ይሞታል በማለት እያስተማሩ፣ የክርስቶስን ድንቅ የመስቀል ስራ በተዘዋዋሪ ይቃወማሉ።**

እነዚህ አስተማሪዎች፣ ፓስተሮች፣ ወንጌላውያን ወ.ዘ.ተ..... የሚጠቅሱት ጥቅስ፣ ሃዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልዕክቱ ላይ "እኔ በየቀኑ እሞታለሁ" የሚለውን ቃል ሲሆን፣ ያላስተዋሉት ወይም በማወቅ የሸፈኑት ጉዳይ ቢኖር ሃዋርያው ጳውሎስ "እኔ በየቀኑ እሞታለሁ" ያለበትን ምክንያት ነው።



በመጀመሪያ ሃዋርያው ጳውሎስ "እኔ በየ ቀኑ እሞታለሁ" ያለበትን ምክንያት ከማየታችን በፊት፣ በጥቅሱ ላይ "እሞታለሁ" የሚለውን ቃል ትርጉም እንመልከት። "እሞታለሁ" የሚለው ቃል በግሪክ "አፖተነስኮ (APOTHNESKO)" የሚል ሲሆን፣ ትርጉሙም እንደ ግሪኩ መዝገበ ቃላት (GREEK LEXICON) አተረጓጎም "በሰዎች ወይም በእንስሳት አመፃ አማካኝነት ለሞት መዳረግ" ማለት ነው።

ስለዚህ፣ ሃዋርያው ጳውሎስ "እየሱስ ከሞት ተነስቷል፣ የሙታንም ትንሳኤ አለ" በማለት አስረግጦ በሚናገርበትና በሚያስተምርበት ወቅት፣ ታላቅ ችግር ገጠመው፣ ለአደጋ ተጋለጠ፣ ከአራዊት ጋር ታገለ፣ ስቃዩ በዛበትና፣ ከዚህ የተነሳ "እኔ በየቀኑ እሞታለሁ" ለማለት በቃ (1 ቆሮ 15)።

መልዕክቱን እንጂ ጥቅሱን ብቻ መውሰድ የለብንም። ጥቅሱን ብቻ በመውሰዳችን የክርስቶስ መስቀልን መቃወም ቻልን።

አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር **ተሰቅሏል!** አሜን! የከንፈር ፍሬ ብቻ ሆኖ እንዳይቀርብን እምነት ያስፈልገናል።

ይህ “ተሰቅሏል” የሚለው ቃል በግሪክ “ሱስታውሮ (SUSTAUROO) ሲሆን፣ ትርጉሙም “አብሮ ስቅለት ወይም አብሮ መሰቀል” ማለት ነው። ለምሳሌ በተመሳሳይ ቃል፣ እየሱስ በተሰቀለ ወቅት ሁለት ወንበዴዎች አንዱ በቀኙ፣ ሌላው በግራው አብረውት ተሰቅለው (ሱስታውሮ፣ SUSTAUROO) እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ገልጦልናል (ማቴ 27:44)።

ሁለቱ ወንበዴዎች በእየሱስ ግራና ቀኝ መሰቀላቸውን ካመንን፣ ለምን “አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል (ሱስታውሮ፣ SUSTAUROO)” የሚለውን ጭብጥ እውነት ለመቀበል ተሳነን? መልሱን ለጴንጤዎች ሹማምንት ትቸዋለሁ።

አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር **ተሰቅሏል!** አሜን!



“ይህ አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀለ፣ አሁን በመደጋገም የምንፈፅማቸው ሃጥያቶችስ ምንጫቸው ምንድነው?” ብለን ልንጠይቅ ስለምንችል ምላሹን በምዕራፍ አራት ላይ እናገኛለን።

የምንፈፅማቸው ሃጥያቶቻችን በእየሱስ ክርስቶስ ደም ሲደመሰሱ (ሮሜ 5:9)፣ ሃጥያተኛነት (አሮጌው ሰዋችን) ደግሞ በሞት ተፈረደበት (ሮሜ 6:6)። ይህ ነው የኤሎሂም የውጀት ነፀብራቅ።

ስለ አዳም ከክርስቶስ ጋር መሰቀልን ስንረዳ፣ አንድ እጅግ ወሳኝና በመንፈሳችን ማወቅ ያለብን እውነትም አለ።

አሮጌው ሰው በክርስቶስ መስቀል ሲሰቀል ወደ መስቀሉ የተወሰደው ማንነቱ **በከፊል** ሳይሆን **በሙላት** ነበር። ይህም ማለት የተሰቀለው **መጥፎነቱ** ብቻ ሳይሆን **“በጎነቱም”** ነው።

ከአዳማዊነት የመነጨ ፍፁም የሆነ “በጎነት” አልያም “መልካምነት” ቢኖረንም፣ ያለንን ሁሉ ለድሃ

ብንሰጥ በኤሎሂም ፊት የተረገመ ነው፣ ምክንያቱም "የበጎነቱ" ምንጭ አዳም ነውና።

ብዙ በባህሪያቸው የሚያስደንቁን በሰዎች ዘንድ ጨዋዎች፣ የማይጠጡ፣ የማይዘሙቱ፣ ድሃን የሚረዱ፣ ከሙክራብ፣ "ከቤተክርስትያን" እና ከመስጊድ የማይለዩ....ወ.ዘ.ተ ተብለው የተመሰከረላቸውን ሰዎች እናውቃለን።

እነዚህ ሰዎች በሰው ፊትና በራሳቸው ሚዛን መልካም መስሎ ይታዩ እንጂ፣ በኤሎሂም ፊት ግን ይህ ሁሉ ከንውን የተረገመና ሞት የተፈረደበት ከራስ የፈለቀ ፅድቅ ነው። እነዚህም ሰዎች ያላቸው አዳማዊ ማንነት ኤሎሂምን ማስደሰት ፍፁም አይችልም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ከስጋ የተወለደ ስጋ ነው (ዮሃ 3:6)፣ ይህ ማንነት ደግሞ ልቡ በስጋ ፍላጎት ላይ ስለሚያርፍ በኤሎሂም ሕልውና ስፍራ ማጣት ብቻ ሳይሆን፣ ኤሎሂምንም ማስደሰት አይችልም (ሮሜ 8:8)።



ለምሳሌ፣ እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቃውያን (**አህዛቦች**) በመንገዱ ላይ ስለተቃወሙት ያህዌ እቀጣቸዋለሁ በማለት ወሰነ።

ከዚህ የተንሳ ያህዌ በሳሙኤል በኩል ለሳኦል "...አማሌቃውያንን ውጋ፣ ያላቸውን **ሁሉ** ፈፅመህ **አጥፋ**፣ አንዱንም አታስቀር፣ ወንዱንና ሴቱን፣ ልጁንና ሕፃኑን፣ የቀንድ ከብቱንና በጉን፣ ግመሉንና አህያውን **ግደል**" አለው።

ከዚህም ትዕዛዝ የተነሳ ሳኦል አማሌቃውያንን ከኤውላጥ አንስቶ በምስራቅ ግብፅ እስካለው እስከ ሱር ድረስ ወጋቸው።

የአማሌቃውያንን ንጉስ አጋግን **ከነህይወቱ ማረከው**፣ ሕዝቡን ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈፅሞ አጠፋቸው። ነገር ግን ሳኦልና ሰራዊቱ **አጋግን**፣ **ምርጥ ምርጡን** በግና የቀንድ ከብት፣ **የሰባውን** ጥጃና ጠቦት፣ **መልካም የሆነውን** ሁሉ **ሳይገድሉ ተዉት**።

ከዚህ ውጊያ በኋላ ያህዌ "ሳኦልን በማንገሴ ተፀፅቻለሁ" አለ፣ ምክንያቱም ያህዌ አማሌቃውያንና

ንብረታቸውን <u>ሁሉ</u> ተጠይፎት መጥፋት አለበት በማለት ወስኗል፣ ሆኖም ግን ሳኦል በስብእናው ብቃት **መልካም የሆነውን** ሁሉ ለያህዌ መስዋዕት እንዲሆን ሳይገድል **ተዋቸው።**

ሳኦል ያደረገውን እንደ ሰው ብናስበው ምንም ጥፋት አናገኝበታም፣ ምክንያቱም ምርጥ ምርጡን ከብት ያስተረፈው ከድል በኋላ ለያህዌ መስዋዕት ለመሰዋት ነበር። ሆኖም ግን ከአማሌቃውያን የሚመጣ ማንኛውም ነገር በያህዌ ፊት የተረገመ ነበር። ስለዚህ <u>ሁሉ</u> መጥፋት ነበረበት።

የሳኦል ችግር የነበረው የያህዌን መልዕክት በትክክል **አለማድመጡ** ስለሆነ ያህዌ "**ማዳመጥ** ከአውራ በግ ስብ ይበልጣል" አለው (ምዕራፍ 15)።

በተመሳሳይ መልኩ ከአዳም የሚመጣ መልካም የሚመስለን ሁሉ በመስቀል ማለፉ ግዴታው እንደሆነ የኤሎሂም ቃል ስለሚናገር <u>ማድመጥ</u> አለብን።

አዳማዊ ማንነት ተጠናውቶን ኤሎሂምን "ማምለክ" እንችላለን። ሆኖም ግን ኑሯችን የድል



ሳይሆን የምርኮ ይሆናል፣ ከዚህም ማንነት የተነሳ ሌላው ቀርቶ <u>ምህረትን</u> መስጠትና <u>ማፍቀር</u> እንኳ ተስኖን እንማቅቃለን።

የብዙዎቻችን ችግር የሚጀምረው የአዳም መጥፎነት ብቻ በመስቀል ያለፈ ስለሚመስለን ነው። የኤሎሂም ቃል ግን የሚመክረን የአዳም በጎነትም ይሁን መጥፎነት በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ ነው (ሮሜ 6፥6)። ይህን ማመን ይገባናል! አዳም ባለማመኑ የተነሳ የሕይወት ዛፍ እንዳመለጠው፣ ዛሬም ባለማመናችን የተነሳ ኤሎሂም ከዘመናት በፊት ያዘጋጀልንን የድል ኑሮ በምድር ላይ ሳንኖርና መጭውን የክብር ተስፋን ሳንመለከት እንዳያመልጠን እንጠንቀቅ።

እንግዲህ አስቀድመን እንደተመለከትነው <u>ሃጥያቶቻችን</u> ይቅር ተብሎልንም <u>ሃጥያተኛነት</u> ተቆጣጥሮን መመላለስ እንደምንችል ማወቅ አለብን። ምክንያቱም <u>ከሃጥያተኛነት</u> **ነፃ መውጣት** አለብንና።

ሃጥያተኛ ለመባል <u>ሃጥያቶችን</u> መስራት ብቻ ሳይሆን፣ ሃጥያቶችም እንዲሰሩ በሚገፋፋ በመጀመሪያው አዳማዊ ማንነት ስንኖርም ጭምር ነው።

ይህ ድንቅ የመሲሁ ስራ በኤሎሂም መንፈስ አማካኝነት በማንነታችን ላይ በተግባር ለማየት **እምነት** እንጂ የሃይማኖት ወጋዊ ጥረቃ አያስፈልገንም። በአዳምና በኤሎሂም መካከል ጥል የፈጠረው የአዳም **አለማመን** እንደሆነ መንፈሳችን፣ ነፍሳችንና ስጋችን መረዳት አለበት።

**እየሱስን የማይወድ የተረገመ ይሁን!**



# ምዕራፍ ሶስት

## የሲኦል አሮማ

በጥልቅ በሲኦል፣ ተስፋ በሌለበት፣ ፍርድ በሚጠበቅበት፣ ብርሃን አልባ በሆነበት፣ ሳይገመትና ሳይታሰብ፣ ለሚገማው የጨለማ ሕይወት፣ የሕይወት አሮማ የሆነው የመጨረሻው አዳም በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ማንነቱ ለብዙዎች ጥያቄ ሆኖ ነበር።

ከድንግል የተወለደው የመጨረሻው አዳም እየሱስ ማንነቱ ድብቅ ከመሆኑ የተነሳ፣ የአክስቱ ልጅ የነበረው አጥማቂው ዮሃንስ እንኳ፣ እየሱስ ማን እንደሆነ አልተገለጠለትም ነበር። አጥማቂው ዮሃንስ እየሱስን በትንሹ ለሰላሳ አመት በዝምድናው ይወቀው እንጂ፣ ክርስቶስ እንደሆነ አያውቅም ነበር (ዮሃ 1:33)።

የኤሎሂምን መንግስትና ኤሎሂምን ለማወቅ ቁልፉ የእየሱስን ማንነት ማወቅ እንደሆነ ተነጋግረናል። በመጀመሪያ ምዕራፍ እንደተመለከትነው እየሱስ ከተወለደበት ቀን አንስቶ የተነሳ ጥያቄ ቢኖር "እየሱስ ማነው?" የሚል ነበር።

እየሱስ በአንድ ወቅት የራሱን ማንነት ሊገልፅ ቆርጦ ወሰነ። ይህ በእንዲህ እንዳለ እየሱስ ፊሊጶስ ቂሳርያ ወደ ተባለው አገር በደረሰ ጊዜ ደቀመዛምርቱን "ለመሆኑ ሰዎች የሰውን ልጅ ማነው ይላሉ?" ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም "አንዳንዶች መጥምቁ ዮሃንስ ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነብያት አንዱ ነው ይላሉ" አሉት። እየሱስ በማስከተልም "እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?" አላቸው። ስመኦን ጴጥሮስ "አንተ ክርስቶስ የህያው ያህዌ ልጅ ነህ" በማለት መለሰ (ማቴ 16)።

ስመኦን የክርስቶስ ማንነት የተገለጠለት፣ ከመጀመሪያው አዳም በወረሰው የእውቀት ብቃት ሳይሆን፣ በኤሎሂም መገለጥ የተነሳ ነበር። ይህም መገለጥ ለስመኦን መለኮታዊ የተለውጦ ስምና ስልጣን አስገኝቶለት ጴጥሮስ ተባለ (ማቴ 16:18)።

በዚህ ምድር ላይ የትኛውም የሃይማኖት መስራች የትውልድ **ምንጩ** ከእየሱስ ጋር ቅርርብ እንደሌለው ቀደም ብለን ተመልክተናል። እየሱስ እንደ ሰው ልማድ አልተወለደም። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ



እየሱስ <u>በድፍረት</u> "እኔ የያህዌ ልጅ ነኝ" ያለና በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ የሃይማኖት መስራችም የለም።

የመጨረሻው አዳምና የመጀምሪያው አዳም **በመልክ ወይም በአማሳላቸው** ቢመሳሰሉም፣ የመጨረሻው አዳም ግን ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት **ከኤሎሂም ጋር የሚተካከል** ነበር (ፊል 2:6)። ሁሉም ነገር፣ ሌላው ቀርቶ የመጀመሪያው አዳምም በእርሱ ተፈጥሯል (ቆላ 1:16)። ይህን ሁሉ ግን ከምንም ሳይቆጥር የባርያን መልክ ይዞ፣ በሰው አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ፣ እስከ ሞት ያውም **በመስቀል** ላይ እስከ መሞት ድረስ **ታዛዥ** ሆነ (ፊል 2:8-10)።

በመስቀል ላይ ሞተ የሚለው ቃል በተወሰኑ የክርስትና ክፍሎች እየሱስ በመስቀል ላይ እንዳልተሰቀለ የሚያምኑም አካሎች አሉ፣ ከእነርሱም መካከል የይሖዋ ምስክሮች ይገኛሉ።

ቀደም ብለን በተመለከትነው ጥቅስ ላይ ታዛዥ ሆነ ሲል፣ እየሱስ የታዘዘው ትዕዛዝ እንዳለ እንገምታለን። አንድ ሰው ትዕዛዝ ሲሰጥ ትዕዛዙ ቀደም

ብሎ የተወቀረ መሆን አለበት። ስለዚህ እየሱስን የላከው መዋቅሩ ምንድን ነበር?

**እየሱስ** በምድር ላይ በነበረው ሕይወቱ ማንኛችንም ተሳታፊዎች አልነበርንም። ምክንያቱም የነበረው ሕይወት ሰውን ሁሉ ለማዳን ከመሆኑ የተነሳ፣ የዚህ ተግባር ኢምንቱም የለንም፣ ሊኖረንም አይችልም!

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው **እየሱስ** የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ትርጉሙ "**ኤሎሂም ያድናል ወይም አዳኝ ነው**" ማለት ሲሆን ስለዚህም ድርሻው አልነበረንም። ነገር ግን ከሞቱ ጀምሮ የሕይወቱ ተካፋዮች እንድንሆን ከኤሎሂም ተወስነልን (2 ቆሮ 5፡14)። ስለዚህ **ቤተልሄም ለእየሱስ ብቻ** ሲሆን፣ **ጎልጎታ ግን ለእየሱስና ለእኛም ጭምር** ነው።

ወገኖቼ፣ የቤተልሄምና የጎልጎታ አላማው አንድ ቢሆንም **ሚዛኑ** ግን የተለያየ ነው። ለዚህ ነው ሃዋርያው ጳውሎስ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በስጋ ነገር አንመዝንም፣ ከዚህ ቀደም መሲሁን በዚህ መልክ መዝነነው ነበር ያለው (2 ቆሮ 5፡16)።



እንደሚመስለኝና እንደተረዳሁት ወንድሜ ሃዋርያው ጳውሎስ ለማለት የፈለገው፣ ጳውሎስ ይሰብከው የነበረው መሲህ፣ ከማሪያም ያገኘውን፣ ማርያም ልጄ ትለው የነበረው አይነት **ማንነትን እና** እንደ ሰው **የተገደበውን** ስብዕና ለብሶ የነበረውን አይነት እየሱስ እንዳልሆነ ለማስቀመጥ ነው። ማርያም በእናትነቷ የምታውቀው **በስጋ** በመካከላቸው ይመላለስ የነበረውን **ጊዜና ስፍራ** ገድቦት የነበርውን ማንነቱን ነበር።

መሲሁ በምድር ላይ እንደነበረው ማንነት አሁን ያለው ቢሆን ኖሮ ሁላችንም ኪሳራ ውስጥ እንወድቅ ነበር። ምክኒያቱም በምድር ላይ የነበረው ማንነቱ **ጊዜና ስፍራ** ስለሚገድበው የሳምራዊቷ ሴት እንዳለችውና አንዳንዶች የሃይማኖት ክፍሎች እንደሚያደርጉት ለስግደት ወደ እየሩሳሌም ተራራ በተወሰኑ ጊዜያት መወጣት ባስፈለገን ነበር (ዮሃ 4፡20)። ፍቅሩም እንደ ሰው አድሏዊነት ይኖረው ነበር (ዮሃ 11፡5፣ 36)።

ምንም እንኳ አልአዛር ከሞት ቢነሳም፣ እየሱስ ከዮርዳኖስ ተነስቶ ቢታንያ እስኪደርስ አራት ቀን

ፈጅቶ ነበር፣ ይህ ክስተት አሁን የሚፈፀም ቢሆን፣ ብዙ በመለኮት ያልተወሰነ ሙት አልአዛሮች ይበዙ ነበር። ስለዚህ ኤሎሂም ይህንን ማንነት በመስቀል ለማሳለፍ ወስኖ ይህን እየሱስ **ጌታም ክርስቶስም (መሲህ)** አደረገው (ሃዋ 2፡36)። አሜን!

**<u>በምድር ላይ በስጋ የነበረው እየሱስ በውስጣችን ማደር አይችልም ነበር</u>**። ምክንያቱም እየሱስን በስጋ ለባሽነቱ የተነሳ የሚገድቡት ጉዳዮች ነበሩ። እየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኋላ ግን ማንኛውም ነገር ስለማይገድበው በተመሳሳይ ሰዐት በትንሹ በሶስት ሺህ ሰዎች ውስጥ ማደር ቻለ (ሃዋ 2፡41)። እዚህ ጋር ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር እየሱስ ያለ አካል አርጓል ለማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።

ስጋ ለብሶ በምድር ላይ የተመላለሰው ጊዜና ስፍራ ወስነውት የነበረው እየሱስ አልፎ፣ ገደብ የሌለው እየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ በተመሳሳይ ሰዐት በላይ በኤሎሂም ቀኝና በታች በምድር በአማኝ ውስጥ ለመኖር ብቃት አገኘ። አሜን!



ይህንን ታላቅ ልዩነት እየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ወቅት ይከተሉት የነበሩት እነ ወንድሞቼ ጴጥሮስም <u>ተደፍኖባቸው</u> ነበር ብዬ እገምታለሁ። የሚያውቁትና የተለማመዱት እየሱስ ጊዜና ስፍራ የሚገድቡትን እየሱስ እንጂ ክርስቶስን አልነበረም።

ወንድሜ ጴጥሮስ ከዚህም የተነሳ ይመስለኛል ብዙውን ጊዜ በነፍሱ ይቅበዘበዝ የነበረው፣ እንደውም ለጴጥሮስም ምላሽ ይሆነው ዘንድ እየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ "...ሂዳችሁ ለደቀ መዛምርቱ **እና <u>ለጴጥሮስ</u>**<u>...</u>" ብሎ ለነማርያም የትንሳኤውን መልዕክት መናገሩ ምናልባት ለጴጥሮስ ምላሽ ነው ብዬ እገምታለሁ (ማር 16፡7)።

ወገኖቼ፣ ይህን ልዩነት ማወቅ ለመንፈሳዊ ኑሯችን ወሳኝነት አለው። ውድ ክርስትያኖች ሆይ፣ የትኛው እየሱስን ነው **በውስጣችን** እንደሚኖር ያመንነው ወይም የምናምነው?

<u>በስጋ የነበረውን ወይስ በመንፈስ ያለውን?</u> አሁንም ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር እምነታችን በሁለቱም አይነት ማንነቱ ሲሆን በውስጣችን ሲኖር

የሚችለው ግን ሞትን ድል አድርጎ በመንፈስ ያለውን እየሱስ ክርስቶስን እንደሆነ ለማስረገጥ ነው።

ይህንን ልዩነት በመንፈሱ የተረዳ አማኝ የድል ኑሮ ለመኖር አስቸጋሪ አይሆንበትም።

ሃዋሪያው ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች "..**እየሱስ** በውስጤ ይኖራል.." አላላቸውም፣ ያለው "...**ክርስቶስ** በውስጤ ይኖራል..." ነው (2:20)። በተመሳሳይ መልኩ ወንድሜ ሃዋርያው ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች ሲፅፍ "...ሕይወታችሁ የሆነው **እየሱስ**..." አላለም፣ ያለው "...ሕይወታችሁ የሆነው **ክርስቶስ**..." ነው (3:4)።

ለማስረገጥ ብዙ መጥቀስ ይቻላል ሆኖም ግን የሰው ምስክርነት በሶስት ስለሚፀና የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ሃዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች አጶናይ በመንፈሱ በኩል ሃይል እንዲሰጣቸው የፀለየበትን ምክንያት ሲገልፅ "...በእምነት **ክርስቶስ** በልባቸው እንዲያድር..." አለ እንጂ "...በእምነት **እየሱስ** በልባቸው እንዲያድር..." አላለም (3:17)።



ኤሎሂም መሲሁን ለአለም ሁሉ ሲሰጠ ዳግመኛ በሞት ስቃይ ውስጥ እንድንዘፈቅ ሳይሆን በድል እንድንኖር ነው። ስለዚህም ኤሎሂም በክርስቶስ እንድንሆን አብቅቶን፣ ክርስቶስንም ጥበባችን፣ ፅድቃችን፣ ቅድስናችንና ቤዛችን **አደረገው** (1 ቆሮ 1:30)። ክርስቶስ **ሁሉም** ነው (ቆላ 3:11)።

ክርስቶስ ሁሉም ነው የሚለው ጥቅስ በአማርኛው ብዙ የሚያስደስትና ጠንከር ያለ ወዝ አይሰጠውም። በእንግሊዘኛው **"Christ is all"** ሲለው ከክርስቶስ ውጭ ያለ ምንም ነገር እንደሌለ ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጠዋል።

ክርስቶስ አለን ማለት ሁሉ አለን ማለት ነው። ክርስቶስ ካለን ምህረት አለን፣ ክርስቶስ ካለን ፍቅር አለን፣ ክርስቶስ ካለን **<u>አንድነት</u>** አለን፣ ክርስቶስ ካለን ሰላም አለን፣ ክርስቶስ ካለን ራስን መግዛት አለን፣ ክርስቶስ ካለን ታማኝነት አለን... ወ.ዘ.ተ።

የገላትያ ሰዎችን መልዕክት ስናነብ የመንፈስ **ፍሬ** ብሎ ዘጠኝ ነገሮችን ሲገልፅ እናያለን፣ በተፈጥሯዊ እይታ ስንመለከተው የመንፈስ **<u>ፍሬዎች</u>** ማለት

ነበረበት፣ ሆኖም ግን የዘጠኙም ምንጭ አንዱ ክርስቶስ ስለሆነ ነጠላዊ ገፅታ ተሰጠው (5፡22)። ክርስቶስ ሁሉም ነው!!

ይህን ክርስቶስ ሕይወታችን መሆኑን በመንፈሳችን ሳንረዳ የራሳችንን ጉዞ የምንጓዝ ብዙዎች ነን። አልያም ክርስቶስ ሕይወታችን እንደሆነ በአእምሯችን ብቻ የተረዳነውና ጉዟችን የድል ያልሆነ ብዙዎች አለን። ለዚህ እውነት ምስክር ነኝ!

ክርስቶስ የሆነውና ያለው ሁሉ የእኛ ነው። ሲሞት ሞተናል (2 ቆሮ 5፡14)፣ ከሞት ሲነሳ አብረን ተነስተናል (ሮሜ 6፡5)፣ በአባቱ ቀኝ ሲቀመጥ አብረን ተቀምጠናል (ቆላ 3፡3)፣ ሲገለጥ እንገለጣለን (ቆላ 3፡4)፡ በነገሰበትም (ነግሶ ባለበት) እንነግሳለን (ራእይ 20፡4-6)፣ የነገስታትም ገዢ ስለሆነ መንግስትም አድርጎናል (ራእይ 1፡6)። ክርስቶስ እስካለ ድረስ የእርሱ የሆነው ሁሉ የእኛ ነው።

ሃዋርያው ጳውሎስ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፣ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል ማለቱ ወንድሜ ጳውሎስ ለመኖር ዋስትናው ክርስቶስ መሆኑን



ሲያመለክት ነው። ክርስቶስ እስካለ ድረስ የጳውሎስ ኑሮ የድል ኑሮ ይሆናል፣ ምክንያቱም ኑሮውን የሚኖረው ክርስቶስ ነውና።

ክርስቶስ ኑሯችንን ስለማይኖረው ነው የምንባላው፣ ክርስቶስ ኑሯችንን ስለማይኖረው ነው ተነስተን ወንድሞችን የምንከፋፍለው፣ ክርስቶስ ኑሯችንን ስለማይኖረው ነው አምፀን የእከሌ አገልግሎት በማለት ለመወራጨት የምንሮጠው፣ ክርስቶስ ኑሯችንን ስለማይኖረው ነው ምህረት ለማድረግ የምንቸገረው፣ ክርስቶስ ኑሯችንን ስለማይኖረው ነው ትዳራችን የማይፀናው....ሌላም ሌላ። ሕይወታችን ክርስቶስ ነው (ቆላ 3፡4)!!

እየሱስ <u>ዐስራ አንዱን</u> ደቀ መዛሙርት በላካቸው ወቅት "ባለቤቱን ብዔልዜቡል ካሉት ቤተ ሰዎችንማ እንዴት አብልጠው አይሏቸው" በማለት በተዘዋዋሪ ሕይወታቸውን ሲገልፅላቸው እናነባለን (ማቴ 10፡25)። ይህም በተግባር የታየ እውነት ሲሆን፣ "አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ ላይ ደረሰብኝ" ተብሎ እንደተፃፈው (ሮሜ 15፡3)፣ እርሱ የተባለውን ሁሉ

ተብለናል። እውነት እያለን ሃሰተኞች፣ የኤሎሂም መንፈስ ገዝቶን አጋንንት ያለባቸው፣ የጌታ መጠቀሚያ ሆነን አሳቾች ተብለን በደስታ ያለፍንበት ወቅት አለ። እየሱሴ "በእርጥብ እንጨት እንዲህ ካደረጉ፣ በደረቁ ምን ያደርጉ ይሆን" ብሎ እንደተነበየው ነው (ሉቃ 23፡31)።

እነዚህን ሰዎች የሚለጥፉብን መሪ ለመሆን የሚወዱ እንደ ዲዮጥራጢስ ያሉ እውነትን ለመቀበል የማይወዱ ናቸው (3 ዮሃ 9-10)።

የሚደንቀው ግን ዲዮጥራጢስና መሳዮቹ እውነትን አይቀበሉ እንጂ፣ እንደ ኤሎሂም ቃል የክርስቶስ አካሎች ናቸው፣ ሆኖም ግን ኑሯቸውን ክርስቶስ ስለማይኖረውና የመለኮታዊ ብቃታቸው መመዘኛ በክርስቶስ አካልነት ስላልሆነ፣ በክልላዊ ጥላቻ ተሞልተው ይዋልላሉ። ለዚህ ትዕይንት ምስክር ነኝ!

ክርስቶስ ካለን ምንድን ነው የምንፈልገው? አንድ አማኝ ክርስቶስ ካለው ሁሉ የእርሱ ነው። ፅድቅን ከፈለግን ክርስቶስ ፅድቃችን ነው፣ ቅድስናን ከፈለግን



ክርስቶስ ቅድስናችን ነው፣ ለኤሎሂም መኖር ከፈለግን ክርስቶስ ኑሯችን ነው።

እየሱስ አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሳው ከሞት አስነሳዋለሁ አላለም፣ እየሱስ ያለው "ትንሳኤ እኔ ነኝ" ነው፣ ይህ ማለት ለአልዓዛር ትንሳኤ ሆነለት ማለት ነው (ዮሃ 11፡25)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚያስደንቁኝ ቃሎች አንዱ "በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል" የሚለው የሃዋርያው ጳውሎስ መገለጥ ነው (ቆላ 2፡10)። ሙሉ ትሆናላችሁ አላለም፣ የሚለው ሙሉ ሆናችኋል ነው። ይህ በኤሎሂም የተፈፀመልን ስራ ነውና አሜን ብሎ መስማማትና ማመን ያለብን እንጂ፣ የምንለምነው ወይም የምንፀልይበት አይደለም። ክርስቶስ ሙሉ ስለሆነ እኛም ሙሉ ተባልን። አሜን!

በአንደበት ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል ብለን ፎክረን የድልን ኑሮ የማንኖር ቤት ይቁጠረን። ይህ ቃል ወንድሞችን ለመክሰስ ሳይሆን ልምምዴም ስለነበር አውቀዋለሁ። ምክንያቱም በመንፈስ ሳልሆን በአእምሮዬና በጥረቴ መንፈስ የሆነውን ክርስቶስን

ለመንካት ሞክሬ ልምምድ ብቻ ሆኖ ስለቀረብኝ ያለፈውን ከንቱነቴን አልዘነጋውም።

ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን የተናገረውም ቃል ሳይቀር መንፈስ ነው (ዮሃ 6፡63)። እኔ ግን <u>በአእምሮዬ</u> ብቃት <u>ብቻ</u> መጽሐፍ ቅዱስን አውቄ ሕይወት ሳይሆነኝ የከሰርኩበት መንፈሳዊ ጉዞ ነበረኝ።

በዘመናችን በአማኞች ዘንድ ግልፅ ሆኖ የሚታይ ጉዳይ ቢኖር አስመሳይነታችን ነው። በመንፈሳዊ ኑሯችን እያስመሰልን የማንገፋው ምን አለ? ሌላው ቀርቶ ሕይወታችን የሆነውን ክርስቶስን እያስመሰልን እየኖርን ነው።

በመሪዎቻችን፣ በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ፊት ብቁ ሆኖ ለመታየት ብዙ እናስመስላለን። ይህ በምድርም ሆነ በላይ በሰማይ ትርፍ አልባ ነው (ሮሜ 2፡28-29)። ለዚህ ደግሞ ከኤሎሂም ምህረት ያስፈልገናል፣ ምክንያቱም በተዘዋዋሪ ኤሎሂምን "አንተ ስላልቻልክ በራሴ እየጣርኩኝ ነው" ማለታችን እንደሆነ ማወቅ አለብን። ይህ ንስሃ ያስፈልገዋል! እውነተኛነት ሊጀምር የሚችለው ከንስሃው በኋላ ነው።



ከሌለን የለንም፣ እንዳለን ሆነን የምናስመስል ከሆነ በእምነት ስላልተደረገ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ ሃጥያት ነው (ሮሜ 14፡23)።

ወንድሜ ጳውሎስ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፣ አሮጌው አልፏል አለ (2 ቆሮ 5፡17)። ብዙዎቻችን አዲስ መስሎ ለመታየት የማናደርገው ጥረት የለም፣ አማኝ ጓደኛ እናፈራለን፣ ዘፈንን በመዝሙር እንለውጣለን... ሌላም ሌላ። <u>**የአዲስነታችን ማሰሪያ በክርስቶስ መሆናችን ብቻ ነው።**</u>

ከክርስቶስ ውጭ የሚደረግ ሁሉ የሃይማኖት ወጀብ ሲሆን፣ ይህም ሁሉ የአሮጌው ማንነት ትሩፋቶች ናቸው። ጌታ እየሱስ እንዳለው በአሮጌው ልብስ ላይ አዲስ ጨርቅ የሚጥፍ ማንም የለም (ማር 2፡21)።

ክርስቶስ ሁሉም ነው የሚለው ቃል ለመንፈሳዊ ኑሯችን በቂ መመሪያ መሆን በቻለ ነበር። ሆኖም ግን ማመን ስለተሳነን ክርስትናን <u>እንደተገለጠው</u> ለመኖር አልቻልነውም።

**ብዙዎቻችን በአዳም ሃጥያተኞች እንደነበርን በጣም ግልፅ ሆኖልናል። በተመሳሳይ መልኩ ክርስቶስ የሆነውን ሁሉ መሆናችን መረዳቱ ቀላል መሆን አለበት።** ለዚህም ነው መጽሐፉ በአዳም አለመታዘዝ ብዙዎች ሃጥያተኞች እንደ ሆኑ፣ በእየሱስ ክርስቶስ መታዘዝ ብዙዎች ፃድቃን እንደሚሆኑ የተናገረው (ሮሜ 5፡19)። ይህ ነው የፀጋ ዘመን!! በኤሎሂም ክንውን ውስጥ ድርሻችን "አሜን" ብሎ መቀበል ብቻ ነው።

በክርስቶስ መሆናችን ብቻ ነው የኤሎሂምን በረከት ልንቀበል ያስቻለን፣ ምክንያቱም ኤሎሂም እኛን ሲመለከት የሚያየው ክርስቶስን ብቻ ነው።

በእኔነቴ ብቁ የሚያደርገኝ አንዳች ነገር የለኝም፣ ከክርስቶስ ውጭ ያለኝ ሁሉ ፍርድ የሚገባውና የተረገመ ነው። አንድ ወንድሜ እንዳለው ሌላው ቀርቶ ኤሎሂም ፊት የማነባው እንባዬ ምህረት ያስፈለገዋል።

ክርስትና ማለት ክርስቶስ ማለት ነው! ክርስትያን ማለት የክርስቶስ ማለት ነው! ቤተ ክርስትያን ማለት ክርስቶስ ማለት ነው! ክርስቶስ ሁሉም ነው! አሜን!



ይህን ክርስቶስ በውስጣዊ ሰውነታችን ስላላመንነው የድል ህይወት የለንም። የድል ሕይወት ማለት የዘማሪ ማሊያ ለብሶ "ዘማሪ" መሆን ሳይሆን የክርስቶስ ግልባጭ መሆን መቻል ነው።

<u>እውነተኛ አምላክና የዘላለም ህይወት</u> የሆነው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል የሚያስተምረን፣ ድል የሚነሳ <u>ብቻ</u> ነው የተዘጋጀለትን የሚወርሰው (ራእ 2 እና 3)። ድሉም የሚነሳው በክርስቶስ ብቻ ነው!

ያለ ክርስቶስ ማገልገሉም፣ መዘመሩም፣ መውደዱም ሆነ ትጻሩ ሁሉ ከንቱ ነው። ክርስቶስ የሌለበት ሁሉ ሽንፈት ነው። ክርስቶስ ሁሉም ነው! ሁሉም በክርስቶስ ነው! አሜን!

## እየሱስን የማይወድ የተረገመ ይሁን!

# ምዕራፍ አራት

## ሕገ ሕይወት በሕገ ሃጥያት

እውነተኛና በኤሎሂም የተወለደ ተጨባጭ መንፈሳዊ ኑሮ ለመኖር ፍላጎቱና ምኞቱ ቢኖረን፣ ይህ ፍላጎታችን በራሱ የድል ኑሮ ለማስኖር ብቃት የለውም።

አንድ አማኝ በድል የታቀፈ መንፈሳዊ ኑሮን ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ስለተመኘ ብቻ የተመኘውን ሆኖ መገኘት ፍፁም አይችልም። ምክንያቱም ምኞታችን አልያም ፍላጎታችን የድል ኑሮ ለማስገኘት የሚያስችል የራሳቸው ብቃትና ሃይል የላቸውም።

ማንኛውም አማኝ በሕይወቱ ያለፈበትና እያለፈበት ያለ ቀናዊም ይሁን ኢ-ቀናዊ የመንፈሳዊ ጉዞ አለው። ይህም ጉዞ ብዙዎቻችን "ትክክል" በማለት የምንመሰክርለት እውነታዊ ገፅታ አለው። የዚህ ጉዞ ትዕይንት አብዛኛው ጊዜ የታቀፈው "መልካም ለማድረግ በመፈለግ ነገር ግን መልካም ያልሆነውን



አድርጎ በመገኘት" መዋቅር ውስጥ ነው። በዚህ አይነት ጉዞ ያላለፈ አማኝ ባይኖር እጅግ የሚያስደንቅ ከመሆኑም ባሻገር ለአዲስ ፍጥረትነቱ ጥርጥር ውስጥ ይከተናል።

ወንድማችን ሃዋርያው ጳውሎስም የዚህ አይነት ስቃይ ተካፋይ በመሆኑ "....ለማድረግ የምፈልገውን አላደርግም፣ ነገር ግን የምጠላውን ያን አደርጋለሁና..." በማለት ለሮሜ ሰዎች ስቃዩን ሳይደብቅ ገለፀላቸው (7፡15)።

ቀደም ባሉት ምዕራፎች የመሲሁን ድንቅ ስራ በአስረጋጭነት እንደተመለከትነው፣ ሃጥያተኛው ማንነት ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል። ሆኖም ግን ሃጥያተኛው ማንነት ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀለ፣ አሁን የምንፈፅማቸው ሃጥያቶች ምንጫቸው ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም ነው። ስለዚህ፣ አሮጌው ማንነት ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀለ፣ አሁን የምንፈፅማቸው ሃጥያቶቻችን ምንጫቸው ምንድነው?

የፈፀምናቸው ሃጥያቶቻችን በክርስቶስ ደም ሲታጠቡልን፣ አሮጌው ሰዋችን በመስቀል ላይ

ሲሰቀልልን “እልል” ብለን እየኖርን ሆኖም ግን የምንፈልገውን ሳይሆን የምንጠላውን እየፈፀምን እንገኛለን።

በሃዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በተፃፈው መልዕክት ምዕራፍ 7 ላይ ስንመለከት ከባድ የሆነ ውስጣዊ ትግልን እናያለን። ትግሉም “የማደርገውን አላውቅም፣ ለማድረግ የምፈልገው አላደርግም፣ ነገር ግን የምጠላውን ያን አደርጋለሁና” በሚል ውጥረት የተካተተ ነበር (15-16)።

ሃዋርያው ጳውሎስ ከኤሎሂም ጋር ጠበኛ እንዳልነበር ከፃፈው መልዕክቱ ብንረዳም (ሮሜ 5፡1)፣ ውስጡ ግን በሰላም የተሞላ አልነበረም። መልካም ለማድረግ ይፈልጋል፣ ሆኖም ግን አልቻለም ነበር።

ለምሳሌ፣ <u>መዋሸትና መሃላ ከአጋንንት</u> እንደሆነና ኤሎሂምም እንደሚጠየፈው ተገንዝበን ላለመዋሸትና ላለመማል ውሳኔ ስናደርግ፣ ነገር ግን ብዙም ሳንቆይ ዋሽተንና ምለን ስንገዘት እንገኛለን። ስለዚህ ይህ ውጥንቅጥ የሞላው ኑሮ የሚፈጠረው ከምን የተነሳ ነው?



ሃዋርያው ጳውሎስ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አንድ ሕግ እንደሚሰራበት ተረዳና “...ስለዚህ ይህ ሕግ እንደሚሰራ ተረድቻለሁ፣ ይኸውም **በጎ ነገር ለመስራት ስፈልግ፣ ክፋት ከእኔ ጋር አለ**። በውስጤ በኤሎሂም ሕግ ሃሴት አደርጋለሁ፣ ነገር ግን በብልቶቼ ውስጥ ለሚሰራው <u>**የሃጥያት ሕግ**</u> እኔን እስረኛ በማድረግ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋ ሌላ ሕግ በብልቶቼ ውስጥ ሲሰራ አያለሁ” አለ (ሮሜ 7፡21-23)። ሃዋርያው ጳውሎስ “የሃጥያት ሕግ” ሲል ምን ማለቱ ነው?

**የሃጥያት ሕግና ሃጥያት እጅግ የተለያዩ ናቸው**። ለምሳሌ፣ መኪና ስንነዳ የትራፊክ ሕጎችን የምንጠብቀው **ትራፊኩ** በዚያ ስፍራ ስለሚቆም አይደለም። ትራፊኩ **ቢቆም ባይቆም** ሕጉን መጠበቅ አለብን። ሕጉ ሕግ የሚባለው ትራፊኩ በስፍራው ስለሚኖር ሳይሆን፣ ለዘወትር የምንከተለውና የሚደጋገም፣ ተረቆ የተወሰነና መከበር ያለበት ሃላፊነት ስለሆነ ነው።

የሃጥያት ሕግም በተመሳሳይ መልኩ <u>በሃጥያት እንድንላቆጥ የሚያደርገን ሃጥያተኛው ሰው</u> በሕይወት ሳይኖርም እንኳ፣ በመደጋገም የሃጥያት ርዝራዦችን

እንድንፈፅማቸው የሚወጥንና ወደ አመፃ የሚመራን የሰቆቃ ህይወት ግዞት ነው።

ትራፊኩ በስፍራው እንደማይኖር ሁሉ ሃጥያትን እንድንፈፅም የሚገፋፋውም ሃጥያተኛው ሰው ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለ ብናውቅም (ሮሜ 6፡6)፣ የአሮጌውን ማንነት ሕግ ግን እንከተላለን።

ለምሳሌ፣ ትናንት የዋሸነውን ዛሬ የምንደግምበት ሰበብ፣ የትናንት ውሸታችን በአሮጌው ማንነት ብቃት እውነት ስለሚመስለን ነው። ምክንያቱም ማንነታችን የሚደጋግመው ውሸት ከብዛቱ የተነሳ ጤናማነት ስለሚመስለው ነው። ይህ የስቃይ ኑሮ ያወዛወዘው ወንድሜ ሃዋርያው ጳውሎስ "እኔ ምን ዐይነት ጎስቋላ ሰው ነኝ፣ ከዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል" በማለት እርዳታን መፈለግ ጀመረ (ሮሜ 7፡24) ።

ብዙዎቻችን ይህን የሕይወት ጉዞ ቀምሰናል፣ አሁንም የምንኖርበት ቤት ይቁጠረን። ይህ ጉዞ ለአንድ ሰው ለአዲስ ፍጥረትነቱ ምልክቶች ከሆኑት አንዱ ነው ብሎ ለመድፈር እችላለሁ። ምክንያቱም ወደ ክርስቶስ



ሳንጨመር በፊት፣ ሃጥያት እንፈፅም አንፈፅም የሚጨንቀን ጉዳይ አልነበረም፣ መልካምም ለማድረግ የሚገፋፋ ማንነት ይሁን ፍላጎት ስላልነበረን ከፅድቅ ነፃ ነበርን። መልካም ለማድረግም መፈለግ በክርስቶስ ብቻ የሚገኝ አዲስ የሆነው ሰው ህይወት ነውና።

ኤሎሂም መልካም ለማድረግ እየፈለግን ክፉ ከምንፈፅመው የሰቆቃ ሕይወት እንድንወጣ እጅግ ይፈልጋል። ግን እንዴት ነፃ እንወጣለን?

ለምሳሌ፣ በአሜሪካ ምድር የሚያሰክር መጠጦችን ለመገበያየት የወጣ የእድሜ ገደብ ሕግ ሲኖር፣ ይህም ሕግ የሚያዘው እድሜ ከሃያ አንድ አመት በላይ ብቻ ነው።

የሃያ አመት ጎልማሳም የሚያሰክር መጠጥ በሕጋዊነት ገዝቶ መጠጣት አይችልም። ይህ በአሜሪካ ግዛት የተደነገገ ሕግ ነው። ነገር ግን ሕጉን አርቃቂዎች ከብዙ ጥናት በኋላ የሃያ አመት ጎልማሳ የሚያሰክር መጠጥ ገዝቶ መጠጣት ይችላል የሚል ስምምነት ላይ ቢደርሱ፣ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር የቀድሞውን ሕግ አዲስ በሚያወጡት ሕግ መሻር ብቻ ነው። ስለዚህ የሃያ

አመት ወጣት የሚያሰክርን መጠጥ በሕጋዊነት መንገድ እንዲገበያይ ቀድሞ ወጥቶ የነበረውን ሕግ በአዲስ ሕግ መሻር ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

በተመሳሳይ መልኩም **የሃጥያትን ህግ የሚሽር ሌላ ሕግ** መምጣት ይኖርበታል። ኤሎሂምም የሃጥያትን ሕግ ለመሻር አዲስ ሕግ በማምጣቱ፣ ሃዋርያው ጳውሎስ "**...የሕይወት መንፈስ ሕግ** በክርስቶስ እየሱስ **ከሃጥያት ሕግ ነፃ አውጥቶኛል**" አለ (ሮሜ 8:2)። ሃሌሉያ!

ይህ የሕይወት መንፈስ ሕግ ነው በውስጣችን ሆኖ የድል ኑሮ እንድንኖር የሚያደርገን። የዚህ ክንውን ድርሻችን በክርስቶስ የድል ስራ ማመን ብቻ ነው!

መልካም ለማድረግ በጥረታችን ከመሯሯጣችን ይልቅ "ኤሎሂም በልጁ በጌታችን በክርስቶስ ይፈፅመው" ብለን ማመን አለብን። በሮጠ ቢሆን ኖሮ ኤሳው በኤሎሂም በተወደደ ነበር (ሮሜ 9:13)።

ሁልጊዜ በመዋሸት የምንሰቃይ ከሆነ በራሳችን ላለመዋሸት እንሞክር፣ ሆኖም ግን ለኤሎሂም



"አልቻልኩም ስለዚህ በራሴ አልጥርም ለአንተ ትቻለሁ" በማለት ማስረከቡ በኤሎሂም መታመን ይባላል።

ለሰው የማይቻል ለአዶናይ ይቻላል! አዶናይ ግመልን በመርፌ ቀዳዳ ያሾለከ አምላክ እንደሆነ ዘኬዎስ ይመሰክርልናል (ሉቃ 19)። በራሳችን መጣር መፍትሄ አለማምጣቱ ብቻ ሳይሆን "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ያለውን ጌታ አለመታመንን ይሆናል (ዮሃ 15:5)።

**የሕይወት መንፈስ ሕግ** በሚለውን ቃል ውስጥ በክርስቶስ ያለው የሕይወት መንፈስ ራሱን የቻለ ሕግ እንዳለው ሲያስገነዝበን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ፍጥረት ሁሉ መንፈስ እንዳለው ሁሉ የክርስቶስ ሕይወቱ ራሱ መንፈስ እንዳለው እንገነዘባለን። ይህም መንፈስ የሕይወትን ህግ ተከትሎ ከውጭ ሳይሆን በውስጣችን በመኖር በድል የሚያስኖረን ሃይል ነው።

ይህ የሕይወት መንፈስ ሕግ በእኛ ብቃት የምንዋቀረው ሳይሆን በራሱ ሃይል የሚመራን የመንፈሳዊ ኑሮ መተዳደሪያ ነው። የተዘረጋለትም ይሁን የተወጠነለት መርህ የለም። የሚዘረጋና

የሚወጠንን የኑሮ መተለሚያን ክርስቶስ በመስቀል እንዳስወገደው እናውቃለን (ቆላ 2፡14)።

ይህ የሕይወት መንፈስ ሕግ በመንፈሳዊ ኑሮ "ቁም" ሲል እንቆማለን፣ "ሂድ" ሲል እንሄዳለን። ምሪቱን ለማግኘት ትዕዛዙን መጠበቅ አለብን።

ለምሳሌ፣ በነፍሳችን ብቃት ከሕይወት መንፈስ ሕግ የሚመነጨውን ትዕዛዙን መጠበቅ ስለማንችል ራሳችንን "ፓስተር"፣ "ወንጌላዊ"፣ "ነብይ"..... ብለን እንወራጫለን። <u>የኤሎሂምን ሰዐት መጠበቅ ስለሚሳነን ለሕዝባችን በረከት ልንሆን አልቻልንም።</u>

የሕይወትን መንፈስ ሕግ የሚከተሉ ምንም እንኳ ወንጌልን መናገር ግዴታና ሃልፊነት እንደሆነ እያወቁም፣ ይህ የመንፈስ ሕግ ግን እንዳይሰብኩ የነገራቸውና የታዘዙበት ወቅት ነበር (ሃዋ 16፡6)።

ይህ ጉዳይ በዚህ ዘመን የተከሰተ ቢሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ጳውሎስና ባልደረቦቹ ከሙከራብ በተባረሩ ነበር፣ ምክንያቱም የዘመኑ ምሪታችን ትኩረቱ ነፍሳዊ እውቅና ላይ ብቻ ስለሆነ ነው።



በድል ነሺነት የተዋቀረ መንፈሳዊ ኑሮ የሚመነጨው በኤሎሂም መንፈስ ምሪትና በክርስቶስ የሕይወት ሕጋዊ መርህ ስንታቀፍ እንደሆነ ማወቅ አለብን። ሌላው ቀርቶ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ሁሉ በነፍሳችን ሸምድደን ለመታዝዝ ሙከራ ውስጥ ብንገባ፣ ከሕይወት መንፈስ ሕግ ጋር መፃረር ይሆናል፣ ኑሮውም የድል ሊሆን አይችልም፣ አስረግጠን የምንጠቅሰውን ጥቅስ እንኳ መኖር አንችልም። ምክንያቱም የክንውናችን ምንጩ መለኮታዊነት የተሳነው በግላዊነት የታጀለ ስለሆነ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያችን ሊሆን የሚችለው በኤሎሂም መንፈስ ሲታቀፍ ብቻ ነው፣ ምክንያቱም የኤሎሂም ቃል መንፈስ ስለሆነ የሚገለጠውም በመንፈስ ብቻ ነው (ዮሃ 6፡63) ።

ለምሳሌ፣ እህቶቻችን መጽሐፍ ቅዱስ "ቤተ ክርስትያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ፣ ሚስቶች ለባሎቻችሁ ተገዙ (ራሳችሁን ስጡ)" የሚለውን ቃል (ኤፌ 5፡22) ተመልክተው ብቻ የሚገዙ ከሆነ፣ ለእውነት ቃል እንዳልታዘዙ ማወቅ አለባቸው። ምክንያቱም

እህቶቻችን ይህን ጥቅስ እንደ ሕግ ተቀበሉት እንጂ፣ ለመንፈሳቸው መገዛት (ራስን መስጠት) እና የመገዛቱም ተምሳሌነት መዋቅር የሆነውን ቤተክርስትያን **ምንና እንዴት** እንደሆን በኤሎሂም መንፈስ ስለተገለጠላቸው አይደለም። ያለ ሰማያዊ መገለጥ የሚወለድ "መታዘዝ" ሃሴትን አይፈጥርም!

የኤሎሂም ቃል የሚለውን በጥረታችን መታዘዝና በኤሎሂም መንፈስ በርቶልን መታዘዝ ምስራቅና ምዕራብ የመለያየቱን ያክል የሰፋ ነው። ከዚህም የተነሳ ይመስለኛል ሃዋርያው ጵውሎስ የገላትያን ሰዎች በመንፋስ እንዲኖሩ ያስጠነቀቃቸው (5:16)።

ወገኖቼ፣ ኤሎሂምን ለመከተል ፈቃደኞች መሆናችን ብቻ በቂ አይደለም። በሮሜ ሰዎች መልዕክት ላይ እንደ ተመለከትነው ሃዋርያው ጳውሎስ "በጎ የማድረግ ምኞት አለኝ" ሲል የሚያሳየው ፍቃዱን ሲሆን፣ ሆኖም ግን እንደምናውቀው ለሃዋርያው ጳውሎስ ፈቃደኛነቱ ብቻ ድልን አልሰጠውም፣ ምክንያቱም የፍላጎቱ ምሪት የማንነቱ ብቃት እንጂ በመንፈስ የታቀፈ አልነበረም።



እስራኤላውያን ከግብፅ ለቀው በወጡበት በዚያች ዕለት በሲና ምድረ በዳ በተራራው ፊት ሰፈሩ፣ ኤሎሂምም "በፍፁም ብትታዘዙኝ ከአህዛብ ሁሉ እናንተ የተወደደ ርስቴ ትሆናላችሁ" ሲላቸው ሕዝቡም ሁሉ "ያለውን ሁሉ እናደርጋልን" በማለት ተስማሙ (ዘፀ 19)። ነገር ግን በአፋቸው የገቡት ቃል በልባቸው ወስጥ ስላልፀና ውጤቱ ከክንፈራቸው ፍሬ አላለፈም ነበር (ዘኁ 25:9)።

ብዙዎቻችንም ስለ እየሱስ ክርስቶስ እንመሰክራለን፣ ሆኖም ግን ምስክርነታችን ገላጭነቱ የሚያጎላው ምን እንደሆነ አልተገለጠልንም።

እየሱሴ በዚህ ጉዳይ ላይ በማስመልከት "ከአብ የሚመጣው አፅናኙ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፣ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ስለ ነበራችሁ ትመሰክራላችሁ" ማለቱን አንዘነጋም (ዮሃ 15:26-27) ። እንደ እየሱስ አገላለጥ ምስክር ሊሆን የሚበቃ ሰው በተመለከተው ጉዳይ እንጂ፣ በእጅ አዙር በሰማው አይደለም።

ለምሳሌ፣ መኖሪያው ባዶ ትሁን፣ የሚኖርባትም ሰው አይገኝ፣ ሹመቱን ሌላ ሰው ይውሰደው ለተባለለት እየሱስን በሸጠው በይሁዳ ምትክ የሚሆን ሲፈልጉ "...ከዮሃንስ ጥምቀት ጀምሮ እየሱስ ከእኛ ተለይቶ እስካረገበት ቀን ድረስ የነበረ መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከእኛ ጋር የትንሳኤው ምስክር እንዲሆን ያስፈልጋል" በማለት ተነጋገሩ (ሃዋ 1፡22)። ይህ ነው ምስክር ለመሆን ብቃቱ፣ ሁሉን ያየና የቀመሰ!

"ኤሎሂም ፍቅር ነው" የሚል ሰው የኤሎሂምን ፍቅር ቀምሶ ለማስተላለፍ የሚችል ለፍቅሩ ምስክርነት ብቁ ነው፣ <u>በማንነታችን ላይ ያላየነውን መናገር ምስክርነት አይደለም!</u>

"ኤሎሂም ሁሉን ቻይ ነው" ብለን በጎሪጥ በራሳችን ጥረት የምንታገል ከሆነ፣ ምስክርነት አይደለም። ለምንመሰክረው ሰውም ፈውስ አይሆንም፣ ምክንያቱም ምስክርነታችን ምድራዊ ጥበብ የሞላው ነውና።



"እየሱስ መንገድም፣ ሕይወትም፣ እውነትም ነው" ብለን ስንመሰክር ሆኖልንና አጣጥመነው መሆን አለበት፣ ሕይወት ክርስቶስ እየሆነ እኛ ግን የኤሎሂምን መንግስት በራሳችን ሕይወት ለመኖር ስንታገል ምስክርነት አይደለም። አዶናይ ለዘካርያስ "በመንፈሴ እንጂ በሃይልና በብርታት አይደለም" ያለውን አንዘንጋ! (ዘካ 4፡6)።

<u>የሕይወት መንፈስ ሕግ በውስጣችን ለመኖሩ እውቅናው በማመን የሚለካ እንጂ በስሜታችን፣ በጩኸታችን፣ በመውደቅና በመነሳታችን የሚመዘን አይደለም።</u> ስሜታችን የኤሎሂምን ሃሳብና እውነት ሊያውቅ ፍፁም አይችልም (1 ቆሮ 2፡11)። ስሜትን ለመንፈሳዊ ሕይወት ስፍራ የማይሰጥ ራሱን የካደና የተባረከ ነው!

ያህዌ <u>ለእምነት</u> አባታችን ለሆነው አብርሃም የገባለትን የተስፋ ቃል ባለመጠበቁና በራሱ መንገድ የያህዌን ተስፋ ሊያሟላ ስለሮጠ፣ እንደ ሙሴ መልዕክት አቀማመር ለ13 አመት ኤሎሂም ሳይገለጥለት መቆየቱን እናነባለን (ዘፍ 16፡16ና ዘፍ 17፡1)።

ወገኖቼ፣ ኤሎሂም እንቁ የሆነውን ልጁን ለአለም ሁሉ የሰጠን ፍቅር መሆኑን ሊያሳየን ብቻ ሳይሆን ልጁ ሕይወታችን እንዲሆንልንም ጭምር ነው።

ክርስቶስ ሕይወታችን እንደሆነ በአእምሯችን ተረድተን ሆኖም ግን በኑሯችን ካልተገለጠ፣ የኤሎሂም ብርሃን ስለሚያስፈልገን፣ በዚህም ብርሃን ለመታቀፍ ራስን መካድ ስለሚጠይቅ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ በውስጣችን ለመኖሩ መለኪያችንም ክርስቶስ ስለሆነ፣ በሁሉ ነገር ክርስቶስን በምላሳችን ሳይሆን ከልባችን ማስቀደም ስለሚኖርብን አይኖቻችንን ከእርሱ እናንሳ።

መንፈሳዊን ድንቅ ስራ ሁሉ በማንነታችን ላይ በመለኮታዊ በረከት ልንመለከት የምንችለው በክርስቶስ ብቻ ነው። ለዚህም ነው ሃዋርያው ጳውሎስ የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ እየሱስ ነፃ አወጣኝ ያለው።

በሁሉ ነገር የበላይነት ይኖረው ዘንድ ክርስቶስ እየሱስን በማንኛውም ነገር የመጀመሪያ እናድረገው (ቆላ 1፡18)!!



ክርስቶስን ከባሎቻችን በላይ፣ ከሚስቶቻችን በላይ፣ ከልጆቻችን በላይ፣ ከሙያችን በላይ፣ ከሃይማኖታችን በላይ፣ ከውበታችን በላይ፣ ከአይን አምሮታችን በላይ፣ ከምኞታችን በላይ ካላደረግነው የድል ህይወት ልንቀምስ አንችልም፣ አዲሲቷን እየሩሳሌምን ልንረግጣትም ፍፁም አንችልም!!!

## **እየሱስን የማይወድ የተረገመ ይሁን!**

# ምዕራፍ አምስት

## የደራሲው ዓምድ

እስላም ብሆን ኖሮ ክርስትያን መሆን አልችልም ነበር ማለቴ፣ የቀድሞውን ማንነቴንና ህልውናዬን በጥልቅ ሳስታውሰው፣ በቀላሉ በዚህ መለኮታዊ ህይወት በጎደለው፣ መለያየት እድገት በሚመስለው፣ ችሎታንና ስጦታን ባለየ፣ አምልኮን በጩኸት በመዘነ፣ ነብይነትን "በጥንቆላ" በተካ፣ አድመኛነት ፍቅር በሚመስለው፣ ከአምላኩ በላይ "ፓስተሩን" በሚፈራ፣ <u>ኪዳን ባለየ፣</u> ጥቅስ እውቀት በሚመስለው ትውልድ የማልዘረርና የማላምን ግትር መሆኔን አውቅ ስለነበር ነው። ግትር ነበርኩ ስል ግን ሃይማኖተኛ ነበርኩ ማለቴ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።

በኢትዮጵያ ምድር ስኖር አንድም ቀን እንደ ወዳጆቼ ለመሰብሰብና ሃይማኖታዊ ወግ ለመጠረቅ እግሬንና ልቤን ያነሳሁበት ወቅት ትውስ አይለኝም።

ቀድሞ የነበረኝን ማንነትና ብቃት ሳስበው በቀላሉ <u>**በተለይ**</u> በዚህ ዘመን ራሱን "ክርስትያን" በማለት በሚለካ ትውልድ አፈ ቀላጤነት የማልዘረር



መሆኔን ሳስበው ያሳዝናኛል። ምክንያቱም የዘመናችን ልብን የማይሰብር፣ በአፈ ቀላጤነት የተደገፈ፣ በጥቅስ የተሞላና አእምሮ የወለደው "ወንጌል" የማይማርካቸው በአእምሯቸው ብቃት ያየሉ ወገኖች አሉና።

ይህንን ማለቴ ወንጌል ሃይል የለውም ለማለት እንዳልሆነ ግልፅ መሆን አለበት። ሆኖም ግን <u>**አብዛኛው**</u> "ክርስትያን ነን" የሚሉት **ወንጌል በቅጡ እና በትክክል እንደ ኤሎሂም ቃል** ተነግሯቸው ወደ ክርስቶስ የተጨመሩ ሳይሆኑ፣ ሴት ፍለጋ ሂደው የዋዘዙ፣ መዝሙር አድንቀው የሰመጡ፣ ጨዋ ወንድ ፍለጋ ሂደው የተቁለጨለጩ፣ ሰው ሊያደርሱ ሂደው የዋለሉ....ወ.ዘ.ተ. ጥርቅም እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህንን ስል ግን ያለ ሰው ወንጌል ነጋሪነት ወደ ክርስቶስ አንጨመርም ማለቴ አይደለም።

ለምሳሌ፣ ሃዋርያው ጳውሎስን ስናስበው በሰዎች ስብከትና ምሪት ሊለወጥና ሊዘረር የማይችል መሆኑን ሁላችንም የምናውቀው ታሪክ ነበር።

ሃዋርያው ጳውሎስ በኖረበት ወቅት በሃዋርያው ጴጥሮስ ስብከት መለወጥ የማይችል ሃይማኖተኛ ነበር። ሆኖም ግን ይህንን የተረዳና ያወቀ አምላክ ራሱን

በመግለጥ በደማስቆ ላይ ተገናኘው። ጳውሎስ ሊክደውና ሊቃወመው የሚችለው ስላልነበረና ከሚተማመንበት የአእምሮው እውቀት በላይ ስለሆነበት፣ በፊቱ የተገለጠበትን "ጌታ ሆይ፣ አንተ ማነህ?" በማለት እጁንና ልቡን ሰጠ (ሐዋ 9)።

በተመሳሳይ መልኩም የአንዳንድ ወንድሞቼና እህቶቼም ፅዋ ከሃዋርያው ጳውሎስ ባይተካከልም፣ ከጠሪው እይታ አንፃር ተምሳላዊነት እንዳለው አምናለሁ።

በኬንያ ምድር ካኩማ በሚባል ከተማ በሚገኝ የስደት ካምፕ ውስጥ ወደ አሜሪካ ምድር ለመምጣት የሚያስችለኝን ጉዳይ ለማስፈፀም በትንሹ ለስድስት ወር በካምፑ ተቀምጬ ነበር።

በስደት ካምፑ መኖሬ የማንነቴና የሕልውናዬ ግዛት በምርኮ ተወስዶ፣ በስጋ ለተገለጠው፣ በመንፈስ ለፀደቀው፣ በመላእክት ለታየው፣ በአህዛብ ዘንድ ለተሰበከው፣ በአለም ሁሉ ለታመነው፣ በክብር ላረገውና በክብር ለሚመለሰው ጌታዬ ባርያው ለመሆን በቅቻለሁ።



በፊደል የተቀመረ፣ ህይወት አልባ የሆነ፣ የኤሎሂም መንፈስ የሌለበት የ"ደህንነት" ትምህርት የሚባል ትምህርት ለሁለት ሳምንት በነፍስ ቀመር በካኩማ የስደት ካምፕ እንደተማርኩኝ አውቃለሁ። ከዚህ ባሻገር አንድም ሰው ጊዜውን ወስዶ ያስተማረኝ፣ የገሰፀኝና የመከረኝ የለም። ይልቁንስ በጴንጤ ሹማምንቶች "አሳች" በመባል ኑሮዬን እገፋለሁ።

"አሳች" ልባል እንጂ፣ "ስህተቴን" ቀርቦ "ስህተት ነው" ያለኝ አንድም ሰው የለም!!

የሃሰተኛነት መለኪያው እውነተኛነት፣ የኤሎሂም ቅባት ማፅኛው "ጥንቆላ"፣ የኤሎሂም መንፈስ መለኪያው መውደቅና መነሳት፣ ለእድገታችን መመዘኛው ስሜታችንና ጥቅስ ማወቃችን በሆነበት በዚህ በመጨረሻ ዘመን፣ እውነተኛ ለመባል የምቀበለው ሹመትና ከሃይማኖተኞች የሚፀድቅልኝ ማዕረግ ፍፁም አይኖርም። ምክንያቱም፣ በኤሎሂም ላይ ዘብቼ፣ ያለተሰጠኝን ተሰጠኝ ብዬና ወንድሞችን ሊያይቼ ልኖር የምችለው ኑሮ፣ እየሱስን አሳልፎ በሰላሳ ብር ከሸጠው ከአስቆርቱ ይሁዳ የማይተናነስ ይሆንብኛል።

"የተቀባን ነን" በሚሉት ዘንድ፣ በክርስቶስ እውነት ፅናቴ አሳች አስብሎኝ በመደሰት እኖራለሁ። አምላኬ ኤሎሂም ግን እያሳዘንኩትና እያመፅኩበትም ያለመተው አሳደገኝ፣ አምላኬም አንዲት መልካም ነገር ከእኔ ማግኘት እንደማይችል አስረግጬ እናገራለሁ።

በዘንድሮ ክርስትና መዋቅር በሃይማኖተኞች ዘንድ ብቁ ሆኜ ለመገኘት አልቻልኩም፣ ምክንያቱም እንደዘመነኞቹ በሃይማኖት ትብታብ ሰውን ለመሸንገል ብችልም፣ በኤሎሂም ፊት ግን አልችልም፣ ምክንያቱም ኑሮዬ የሚመራው የሃይማኖተኞች ጠላት በሆነው በጌታዬ በክርስቶስ ነውና።

ኤሎሂም ሃይማኖተኞች እንድንሆን አይፈልግም። ኤሎሂም አስቀድሞ ያወቃቸውን የወሰነባቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ ነው፣ ምክንያቱም ከብዙ ወንድሞች መካከል ክርስቶስ በኩር እንዲሆን ነው (ሮሜ 8፡30)።

የትኛውንም ያክል የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ቢኖረንም ሃይማኖተኛ ከሆንን በኤሎሂም እቅድ ውስጥ እንደማንገባ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ።



ለምሳሌ፣ በንጉስ ሄሮድስ ዘመን እየሱስ በቤተልሄም ከተወለደ በኋላ ጠቢባን ከምስራቅ ወደ እየሩሳሌም መጥተው "የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነው? በምስራቅ ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና" ሲሉ ጠየቁ። ንጉስ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፣ እንዲሁም መላይቱ እየሩሳሌም አብራ ታወከች።

ሄሮድስም የካህናት አለቆችንና የአይሁድ ሃይማኖት <u>መምህራንን</u> በሙሉ ሰብስቦ ክርስቶስ የት እንደሚወለድ ጠየቃቸው። እነርሱም "በቤተልሄም" በማለት <u>መጽሐፍ</u> ጠቅሰው አስረገጡለት (ማቴ 2)። እነዚህ ሃይማኖተኞች ክርስቶስ ቤተልሄም መወለዱን <u>በማንበብ</u> አወቁ እንጂ፣ <u>በዚያን ወቅት</u> ክርስቶስ <u>እንደተወለደ</u> የተገለጠላቸው ነገር አልነበረም።

በወቅቱ ክርስቶስ ተወልዶ፣ እነርሱ ግን <u>በማንበብ</u> የተረዱትንና ራሳቸው በራሳቸው የሳሉትን <u>ሌላ</u> "ክርስቶስ" በጨለመ ተስፋ ይጠባበቁ ነበር። ይህ ማለት እውቀታቸው፣ ፀሎታቸው፣ ፆማቸው፣ አምልኳቸው.... ወ.ዘ.ተ. መለኮታዊ እውቅና የሌለበት የሃይማኖት ትብታብ ብቻ ነበር ማለት ነው።

ብዙዎቻችን እንደምናውቀው እየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ቀንደኛ ጠላቶቹና የሰቀሉትም ሃይማኖተኞች ነበሩ (ማቴ 23)። አሁንም ቢሆን የክርስቶስ ወንጌል በትክክል እንዳይነገር እንቅፋት የሆኑት "እናውቃለን" የሚሉት ሃይማኖተኞች ናቸው።

እነዚህ ሃይማኖተኞች አንድን ሰው ወደ ሃይማኖታቸው ለማስገባት የማይፈጥሩት ሃተታና ታሪክ የለም። የዚህ አይነት ክንውን እየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ተፈፅሞም ነበር (ማቴ 23፡15)። እየሱስ ግን "ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማይ እንዳይገቡ በሰዎች ላይ በሩን ስለምትዘጉባቸው ወዮላችሁ" በማለት ነቀፋቸው (ማቴ 23፡13)።

ሃይማኖተኛ የሆነውንና ያልሆነውን የምንለይበት መንገድ እጅግ ቀላል ነው። ሃይማኖተኛ ሰው ፍቅር አልባ ሲሆን፣ "ትክክል ነኝ" የሚልና ስርዐትን የሚያበዛ ነው። ለምሳሌ፣ በየትኛውም መሰብሰቢያ ስፍራ ብንሄድ የስርዐቱ ብዛት እንቅልፍ የሚያመጣ ነው።

ሃይማኖተኛ ሰው ያለውን ነገር ሁሉ ከሌላው ጋር ማመሳከር ይፈልጋል፣ ሩጫውና ፍላጎቱ ሰውን



ለማስደሰት ሲሆን፣ የውጤቱ መለኪያው ውጫዊነት እና ድርጅታዊነትም የተጠናወተው ነው።

የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ ሃይማኖተኞችን ለመለየት የሚያስችል ውብ ቃል እንዲህ በማለትም አስቀመጠልን፣ "ወዮውላቸው፣ **በቃየን** መንገድ ሄደዋል፣ ለገንዘብ ሲስገበገቡ **በበለዓም** ስህተት ውስጥ ወድቀዋል፣ **በቆሬም** ዐመፅ ጠፍተዋል" (11)።

ቃየንን በደበልጥ የምናውቀው ወንድሙን በመግደሉ እንጂ "ሃይማኖተኛ" እንደሆነ ብዙዎቻችን እንገምት ይሆናል። ሆኖም ግን አቤልና ቃየን በኤሎሂም ፊት መስዋዕት ባቀረቡ ወቅት **የቃየን** መስዋዕት **ውጫዊነት** የገዛውና ሃይማኖታዊ መልክ የነበረው ሲሆን፣ **የአቤል** መስዋዕት ግን **ውስጣዊና ሃይል ያቀፈው** ነበር (ዘፍ 4)።

ቃየንን የሚመስሉ ብዙዎች "በቤተ ክርስትያን" ውስጥ አሉን፣ እነዚህም የሚመለከቱት መስዋዕት መሰዋታቸውን እንጂ የመስዋዕቱን ሃይልና መንፈስ አይደለም።

መስዋዕትና የመስዋዕቱ መንፈስ እጅግ ይለያያሉ። መስዋዕት የተደነገገና የተቀመረ ሂደት ሲሆን፣ የመስዋዕት መንፈስ ግን ከድንጋጌ ገበታ ውጭ ሆኖ፣ ፍቅርና ምህረትን የሚይዝ የመለኮት ሙዳይ ነው።

እየሱስ የሰቀሉትን ሃይማኖተኞች "ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁ፣ የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ብታውቁ ኖሮ ባልፈረዳችሁብኝ ነበር" ማለቱን እናስታውሳለን (ማቴ 12፡7)።

እንደምናውቀው አቤልና ቃየን **(ሁለቱም)** ለኤሎሂም እንደ ሙያቸው አኳያ መስዋዕት አቀረቡ። እንደ ዘመናችን የክርስትና ሂደት ስመዝነው፣ በዚያን ወቅት የነበሩት ሰዎች የአቤልንና የቃየንን መስዋዕት ሲመለከቱ ያዩት **አራት** ነገሮችን እንደሆነ ብገምትም፣ ኤሎሂም ግን የተመለከተው **ሁለት** ነገሮችን ብቻ ነበር።

ሰዎቹ በወቅቱ የተመለከቱት የአቤልን አምልኮ፣ የቃየንን "አምልኮ"፣ የአቤልን መስዋዕትና የቃየንን "መስዋዕት" ሲሆን፣ ኤሎሂም ግን የተመለከተው የአቤልን **ልብ** እና የቃየንን **ልብ** ብቻ ነበር። ከአቤል ልብ ንፅህና የተነሳም ኤሎሂም የአቤልን መስዋዕት



ለማየት በቃ። ምክንያቱም ኤሎሂም የሚቀበለው መስዋዕት የተሰበረ መንፈስንና የተሰበረ ልብን ነውና (መዝ 51፡17)።

ብዙ መለኮታዊ እውነትን ያላስተዋሉት አስተማሪዎቻችን "አቤል የከብት ደም ስላፈሰሰ ኤሎሂም መስዋዕቱን ተቀበለው" በማለት በሰዎች እምነት ላይ በመሰልጠን ያስተምራሉ። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱም "መስዋዕት" ማቅረባቸውን እንጂ፣ ምን አይነት የመስዋዕት ስርዐት እንደ ተከናወነ በግልፅ አይናገርም።

የሚቃጠል መስዋዕት እንዳለ ሁሉ የእህል ቁርባንም መስዋዕት አለና። እውነቱ ግን ቃየን እጅግ ያማረ ወይፈን ይዞ ቢቀርብም፣ በኤሎሂም ፊት ተቀባይነት አይኖረውም ነበር፣ ምክንያቱም ቃየን የተሰበረ መንፈስና ልብ አልነበረውምና።

ብዙዎቻችን በሰው ፊት ብቁ መስለን ለመታየት መለኮታዊ ክንውኖችን እያስመሰልን እንወራጫለን። መዝሙርን፣ ስበካን፣ ስጦታን፣ አገልግሎትንና ኑሯችንን በውጫዊነት እያስመሰልነው እንኖራለ። ሆኖም ግን የሚታይንና የሚለካን የድል ኑሮ ማስመሰል

አይቻልም። <u>የድልን ኑሮ የሚኖር ሰው ራሱን የካደ ሰው ብቻ ነው!</u>

በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ፊት መላዕክት ልንመስል እንችላለን፣ ከንውኖቻችን ከአደናይ ካልተወለዱ ግን ከቃየን የማይተናነስ ነው።

<u>ራሱን የካደ ማንነት ያለው ሰው ሊያስመስል ፍፁም አይችልም።</u> የእየሱስን ሕይወት በሰውነቱ እንዲገለጥ፣ የእየሱስን ሞት ዘወትር በሰውነቱ ተሸክሞ ይዞራል።

ወገኖቼ፣ በይሁዳ መልዕክት ላይ እንዳየነው፡ **ስለ በለዓም ባናወራ ይሻለናል!!** በዘመናችን የክርስቶስን ሳይሆን የራሳቸውን ፍላጎት ለሟሟላት የሚባዝኑ ብዙ በገንዘብ የተለከፉ በለዓሞች አሉን።

በለዓም "ባላቅ በብርና በወርቅ የተሞላ ቤተ መንግስቱን ቢሰጠኝ እንኳ፣ የኤሎሂምን ትዕዛዝ በመጣስ ከዚህ ያለፈ ወይም ያነሰ ማንኛውንም ነገር ማድረግ አልችልም" ማለቱ **<u>ቃል</u>** ብቻ ከመሆኑ አልፎ፣ ባላቅ እንደጠየቀው ሊያድረግ **<u>ከልቡ</u>** ሲወስን ኤሎሂምን በጣም እንዳስቆጣ እናነባለን (ዘኁ 22-24)።



**<u>በዘመናችን የኤሎሂም "አገልግሎት" ገንዘብ ማግኛ ዘዴ እንደሆነ በድፍረት እናገራለሁ። በለዓም ስህተቱ ለገንዘብ መስገብገቡ ነበር።</u>**

ሌላው ደግሞ **የሌዊ ልጅ**፣ የቀዓት ልጅ፣ የይስዓር ልጅ የሆነው **ቆሬ** ከቢጤዎቹ ጋር ሆኖ ኤሎሂም በቀባውን በሙሴ ላይ ተቃወሞ አነሱ።

ቆሬ የሌዊ ነገድ ስለሆነ ያህዌ የክህነት አገልግሎት ሰጥቶት ነበር (ዘኁ 3)፣ ሆኖም ግን ያህዌ የሰጠውን ሳይሆን **<u>ነፍሱ</u>** <u>የተመኘችውን</u> አገልግሎት በመጠማት ያህዌ በቀባው በሙሴ ላይ አመፀ።

የቆሬና ግብራበሮቹ አመፃ የያህዌን ቁጣ አስነስቶ ከነሕይወታቸው ወደ መቃብር ወረዱ (ዘኁ 16)።

ኤሎሂም **በቀባው** ላይ ማመፅ የኤሎሂምን ቁጣ ያወርዳል። ለመሆኑ እነማን ናቸው በኢትዮጵያ ግዛት **በእውነት** ኤሎሂም **በሃይሉ** የቀባቸው?

<u>አንድ አስረግጬ በትህትና የምናገረው ቁም ነገር ቢኖር፣ በአሜሪካ ምድር በኖርኩበት ዘመኔ በአሜሪካ ክልል በሚገኙ "የኢትዮጵያ አብያተ ክርስትያናት" ውስጥ ኤሎሂም የቀባው አንድም አገልጋይ እንዳልተመለከትኩ ነው።</u>

"አገልጋይ ነኝ" የሚለው ሁሉ የሰው አገልጋይና የገንዘብ ባሪያዎች ለመሆናቸው የክርስቶስ ደቀ መዛምርቶች የሆንነው ብቻ ሳንሆን የማይከተሉትም ምስክሮች ናቸው!

በአዲሱ ኪዳን የኤሎሂም ቅባት (ስጦታ) በጅምርት የሚያከናውነው የተቀቢውን ማንነት በክርስቶስ ማንነት መለወጥ ብቻ ነው።

ይህም ማንነት በትህትና የተሞላ፣ ራስን የሚያስክድ፣ መስቀልን የሚያሸክም፣ አለምን የሚያስንቅ፣ ገንዘብን የማያፈቅር፣ የሰውን ጭብጨባ የማይሻ፣ በምላስ ሳይሆን በልብ የዋህ የሚያደርግ፣ በመንፈስ ቅዱስ የታቀፈ፣ በወሬ ሳይሆን በሃይል የሚገለጥ፣ የአምባገነንነት ባህሪን ሳይሆን የአባትነት ባህሪ ያለው፣ በፍቅር የተሞላ፣ ምህረትን አድራጊና የማያስዋሽ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ኤሎሂምን አስደስቶ ክርስቶስን የሚያከብር ማንነት ነው።

አብዛኛዎቹ "ተቀብተናል" በማለት በሙክራባቸ የመጀመሪያ መቀመጫ የያዙት ሹማምንቶች፣ የመኖሪያ ፍቃዶቻቸውን እንኳ ያገኙት የአሜሪካንን መንግስት በመዋሸትና የኢትዮጵያን መንግስት ስም በማጥፋት



እንደሆነ ስም ዝርዝራቸውን ከነ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። ለመሆኑ ኤሎሂም ይዘበትበታልን? ይህንን ጥያቄ ህሊናቸው ይመልሰው!

እነዚህ "ተቀባን" ባዮች ግልጋሎታቸው የሚያተኩረው በነፍሳዊ ዕይታ ላይ ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን "የመለኮት ትምህርት" ድግሪያቸው የሕይወታቸው ማዕከል ነው።

ከዚህ የተነሳ ጌታ ሳይሆን ነፍስ የምትደሰትበትን ምሪት ብቻ ታቅራራለች። "ትንቢታቸው" እንኳ ሳይቀር እንደ ኤልዛቤል ከራሳቸው የመነጨ ነው። ይህንን ተመልክተናል፣ ምስክርም ነን!

ሃይማኖተኛ ያልሆነ ሰው ዘወትር የሚመለከተው ክርስቶስን ብቻ ነው፣ ለድርጅታዊነት ስፍራ ሳይኖረው አትኩሮቱ የሚያርፈውም በክርስቶስ አካልነት ላይ ሲሆን፣ ለውጫዊነትም ስፍራ የለውም።

ከሃይማኖት ትብታብ ለመውጣት ቀላል የሆነ ጉዳይ አይደለም፣ ምክንያቱም መለኮታዊ ፅናት ሳይኖረው፣ "ትክክል ነን" በሚል የኩነኔ ትያትር እጃችንን አጣምረን የምንቀመጠበት ጎራ ነውና።

ወገኖቼ፣ ለመማርና ለመቀበል የሚችል ማንነት ካለን፣ ይህ መጽሐፍ የሕይወት ፈውስ ከመሆኑም ባሻገር ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ክርስቶስን ከሞት ያስነሳውንና በሰማያዊ ስፍራ በኤሎሂም ቀኝ ያስቀመጠውን ሃይል እንድናውቅ ይረዳናል ብዬ አምናለሁ።

ለሁሉም መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ አምላክ ይርዳን። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስን በማይጠፋ ፍቅር ለሚወዱ ሁሉ ፀጋ ይሁን!

ኤሎሂምን የማያስደስትና ክርስቶስን የማያከብር ትዳር፣ ገንዘብ፣ ሙያ፣ ስልጣን፣ አገልግሎትና ማንነት ሁሉ የብዔል ዜቡል ወዳጅነት መግለጫ ነው!

ዙፋኑን ከምንም ሳይቆጥር፣ ስጋን በመልበስ፣ ከድንግል የተወለደው፣ በስጋ ወገኖቹ በሆኑት መከራን የተቀበለው፣ በጳንጥዮስ ጲላጦስ እጅ ለመስቀል ሞት የተዳረገው፣ በዮሴፍ መቃብር የተቀበረው፣ በመንፈስ ወደ ጥልቁ የሄደውና በሶስተኛው ቀን ከሞት የተነሳው እየሱስ ጌታም ክርስቶስም ነው!



ከክርስቶስ ውጭ የሆነ በአለም ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ነገር ሁሉ ከንቱ ነው!

በሁለተኛው ሞት የማይጎዱ የተባረኩ ይሁኑ! አሜን! ማራናታ፣ ጌታ ሆይ ቶሎ ና!

**እየሱስን የማይወድ የተረገመ ይሁን!**

ለጥያቄ፣ ለአስተያየት፣ ለምክር ..ወ.ዘ.ተ

ደራሲውን ለመገናኘት ቢፈልጉ፣

Email:

thecrossway@gmail.com

በስልክ፡

814 218 6676

**እየሱስን የማይወድ የተረገመ ይሁን!**